# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

## የ1993 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናት

## የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ

አዲስ አበባ
የካቲት 1993

# ምዕራፍ 1

## ሀ. መግቢያ

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በርካታ ልጆች የሥራ ዕድሜአቸው ከመድረሱ አስቀድሞ በተለያዩ የሥራ መስኮች እንደሚሰማሩ ይታወቃል፡፡ በተለይም በታዳጊ ሀገሮች ልጆች ከቤት ውስጥ ሥራ (domestic activities) አንስቶ በተለያዩ ቀላልና ከባድ የሥራ መስኮች ልዩ ልዩ ምርትና አገልግሎት በሚሰጡ የቤተሰብ ድርጅቶች እንዲሁም በቅጥር በአምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ እንደሚሠማሩ በተለያዩ አገሮች የተካሄዱ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ በዚህ ረገድ በተለያየ የዓለም ክፍል የተካሄዱ ጥናቶች ልጆች የአካልና የአዕምሮ ጤንነታቸውንና ዕድገታቸውን በሚጎዱ ከባድ ሥራዎች ለምሳሌ በጎጆ ኢንዱስትሪዎች፣ የንግድ (ኮሜርሻል) እርሻዎች አልፎም የማዕድን ማውጫ ድርጅቶች ጭምር እንደሚሰማሩ መረጃዎቹ ይጠቁማሉ፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በተለያዩ ወቅቶች የህፃናት መብቶችን በሚመለከት ደንቦችን አውጥቷል፡፡ ዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅትም (ILO) ዝቅተኛ የሥራ ስምሪት ዕድሜን እና አደገኛ/አስቸጋሪ የልጆች ሥራዎችን በመለየት የሚወገዱበትን ስምምነቶች አጽድቋል፡፡

በኢትዮጵያ ቁጥሩ በትክክል ባይታወቅም በርካታ ልጆች ከአቅማቸው በላይ የሆኑ ከባድ ሥራዎችን በመሥራት ላይ መሆናቸው ይገመታል፡፡ በኢትዮጵያ አብዛኛው ህብረተሰብ የሚተዳደረው በግብርና እንደመሆኑ መጠን ብዙ ልጆች ትምህርት ቤት ገብቶ መማር በሚገባቸው ዕድሜ በተለያዩ የግብርና ሥራዎች (አረም በማረም፣ ከብት በመጠበቅ፣ የግብርና ምርቶችን በመሰብሰብ፣ ... ወዘተ) መሳተፋቸው የተለመደ ነው፡፡ በከተማም በርካታ ልጆች መደበኛ ባልሆኑ የሥራ መስኮች (በመንገድ ዳር እና በጉልት ንግድ፣ በቤት ሠራተኝነት፣ ...) ውስጥ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም ልጆች ከባድና አድካሚ የሆኑ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ያከናውናሉ፡፡ ከዚህም በላይ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች በጎዳና ተዳዳሪነት እና በሴተኛ አዳሪነት የተሰማሩ ልጆች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡

እንደሚታወቀው የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን በ1991 ዓ.ም ካካሄደው አገር አቀፍ የሰው ኃይል ናሙና ጥናት ጋር በማያያዝ ውሱን የልጆች የሥራ ሥምሪት መረጃዎችን ሰብስቧል፡፡ በዚህም ጥናት የተሰበሰበው መረጃ ውጤት በጥናቱ ስታትስቲካዊ ሪፖርት አንድ ምዕራፍ ይዞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡ ነገር ግን የተሰበሰበው መረጃ በልጆች ላይ ያተኮረ የሥራ ስምሪት ጥናት ባለመሆኑና መረጃውም ውሱን በመሆኑ የችግሩን ስፋትና ስርጭት ለመገመት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ዓለም አቀፉ የሥራ ድርጅት (ILO) ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለመጀመሪያ ጊዜ አገር አቀፍ የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናት እንዲደረግ በተስማሙት መሠረት የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን ጥናቱን በመጋቢት ወር 1993 ዓ.ም ለማካሄድ የቅደመ ዝግጅት ሥራው ተጠናቆአል፡፡ በመጋቢት ወር 1993 ዓ.ም ሊካሄድ የታሰበው ሀገር አቀፍ የልጆች የሥራ ስምሪት ናሙና ጥናት ቤተሰብን መሠረት አድርጎ ራሱን ችሎ (Stand-alone) የሚካሄድን የአጠናን ስልት የተከተለ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የሚያገለግለው መጠይቅ የዓለም አቀፉን የሥራ ድርጅት (ILO) መደበኛ (Standard) የልጆች የሥራ ስምሪት ጥናት መጠይቅን መነሻና መሠረት በማድረግና የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ በሚያካትት መልኩ በማቀናበር ተዘጋጅቷል፡፡ መጠይቁ ለዚህ ደረጃ ከመድረሱ በፊት ከመረጃ ተጠቃሚዎች ጋር በተደረገ ውይይት አንዳንድ ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ በተጨማሪም መስክ ላይ በተደረገው የሙከራ ጥናት የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ አስፈላጊ እርማቶችና ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡

## ለ. የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች

1. በአገር አቀፍ ደረጃ አጠቃላይ የልጆችን የሥራ ስምሪት ሁኔታ በሚመለከት ስታትስቲካዊ መረጃ ለማስገኘት፣
2. አብዛኛውን ጊዜ ልጆች በምን ዓይነት የሥራ መስኮች እንደሚሰማሩ እና ምን አይነት ስራዎችን እንደሚከናወኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለተጠቃሚዎች ለማሠራጨት፣
3. በኢትዮጵያ በቀጣይነት በመስኩ ለሚካሄዱ ጥናቶች በመነሻነት የሚያገለግል መሠረታዊ መረጃ (Baseline) ለማቅረብ፣
4. በአገሪቱ በተለያዩ ሥራዎች የተሰማሩ ልጆችን ብዛት እና በሥራ ለመሰማራት ያበቋቸውን ወይም የሚያበቋቸውን ምክንያቶች ለማወቅ፣
5. የልጆች የሥራ ስምሪት በልጆች የትምህርት ተሳትፎ ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ ለማጥናት፣
6. ልጆች በሚሠሯቸው ሥራዎች ምክንያት የሚደርሱባቸውን የአካል ጉዳት/ህመም ዓይነትና መጠን ለማወቅ፣

7.

በአስቸጋሪ/አደገኛ ስራዎች የተሠማሩ ልጆችን ብዛትና የሥራ አካባቢ በማጥናት ለፖሊሲ ቀረፃ የሚያገለግል መረጃ ለማስገኘት፣

8.

በአጠቃላይ ህብረተሰቡ በልጆች የሥራ ስምሪትና ተጊዳኝ መሠረታዊ መብቶች መጓደል ላይ ያለ ውን ግንዛቤ ለማዳበር የሚያግዙ መረጃዎችን ለመሰብሰብና ለማሰራጨት፣

9.

በአገሪቱ ወደፊት በቀጣይነት ተመሣሣይ ጥናቶችን ለማካሄድ የሚያስችል ልምድ ለማግኘት፣ . . . ናቸው።

## ሐ. <u>በጥናቱ የሚሰበሰቡ መረጃዎች አይነት</u>

*በዚህ ጥናት የሚከተሉት መረጃዎች ይሰበሰባሉ፣*

-

የቤተሰቦች የሥነ-ህዝብ እና ማህበራዊ መረጃዎች፡- ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸውን የዝ ምድና ሁኔታ፣ ጾታ፣ ዕድሜ፣ ሃይማኖት፣ ብሄረሰብ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የትምህርት ደረጃ እና የስል ጠና ሁኔታ፣

-

ያለፉት 12 ወራት እና ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ስምሪት ሁኔታ (ዕድሜአቸው 5 ዓመ ትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት)

-

ከጥናቱ ቀን በፊት ባሉት 7 ቀናት በስራ ለተሰማሩ የሠሩት የሥራ ሰዓት ብዛት፣ የሥ ራ አይነት፣ የድርጅት ምርት ወይም አገልግሎት አይነት፣ የቅጥር ሁኔታ፣

- በሥራ ላልተሰማሩ ያልተሠማሩበት ምክንያት፡ ስለ ሥራ አጥነትና የሥራ አጥነት ባህርያት፣
- በክፍያ ለተቀጠሩ የክፍያው አይነትና መጠን እንዲሁም የሥራ ፈረቃ ሁኔታ፣

-

ስለ ቤተሰቦች የፍልሰት ሁኔታ፣ የመኖሪያ ቤት ዓይነትና ይዞታ፣ የአገልግሎቶች አቅርቦ ት እንዲሁም ቤተሰቡ የገቢ እና የወጪ መጠን፣

*<u>ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት ስለሆኑ ልጆች ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች፣</u>*

- ስለልጆች የፍልሰት ሁኔታ፣
- ስለልጆች የትምህርት ሁኔታ፣
- ልጆች በቤት ውስጥ የሚሰሯቸው ሥራዎችን ዓይነትና መጠን፣
- ወላጆች/አሳዳጊዎች በስራ ላይ ስላሉ ልጆች ያላቸውን አመለካከት፣
- ከወላጆቻቸው/ከአሳዳጊዎቻቸው ውጭ ለሌላ ሰው ተቀጥረው ስለሚሰሩ ልጆች ከአሰሪዎቻቸው ጋር ስላላቸው ግንኙነት፣

*<u>ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት የሆኑ ልጆች ስለራሳቸው የሚሰጡት መረጃ፣</u>*

- ስለትምህርትና ስልጠና መከታተል ሁኔታ፣
- ከጥናቱ በፊት ባሉት 7 ቀናት ስለሰሩአቸው ሥራዎች አይነትና መጠን፣
- የሚሰሩት ሥራ በትምህርታቸው ላይ ስላለው ተፅዕኖ ሁኔታ፣
- ከአሠሪዎቻቸው ጋር ስለአላቸው ግንኙነት፣
- ለሰሩት ሥራ ስለሚሰጣቸው የክፍያ አይነትና መጠን፣
- የሚያገኙትን ክፍያ ለቤተሰብ ይሰጡ ወይም ይቆጥቡ እንደሆነ፣
- በሚሰሩአቸው ሥራዎች ምክንያት የደረሰባቸው የህመም/ የአካል ጉዳት መኖር አለመኖሩን፣ ካለ የህመሙን/የጉዳቱን ዓይነትና መጠን፣

ከላይ በተመለከተው መሠረት የሚገኘው መረጃ ከሌሎች መረጃ ምንጮች ጋር በመዛመድ በሥራ የተሠማሩ ልጆችን ብ ዛትና ሌሎች ባህርያት፣ በየጊዜው የሚታዩትን ለውጦች ጭምር ለማወቅ እንዲያስችሉ ይደረጋል። ከዚህም በመነሳት በ

መጪ.ዎቹ ዓመታት መንግሥትና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት የልጆች በሥራ የመሠማራት ሁኔታን በተመለከተ ተገ ቢ ዕቅዶችን ለማውጣትና በሥራ ለማዋል ይችላሉ።

## መ. የጥናቱ መጠይቆች አቀራረብ

ለዚህ ጥናት የሚያገለግሉ የተለያዩ ቅጾች ተዘጋጅተዋል። እነርሱም፦
1) በምዝገባ ጊዜ የሚያገለግሉ ቅጾች እና 2) በዋናው ጥናት የሚያገለግሉ ቅጾች ተብለው ሊለዩ ይችላሉ።

<u>በምዝገባ ጊዜ የሚያገለግሉ ቅጾች</u>

1) ቅጽ 93/0 - የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ
2) ቅጽ 93/1 - የተመረጡ ቤተሰቦች ማስተላለፊያ ቅጽ

<u>በዋናው ጥናት የሚያገለግሉ ቅጾች</u>

ቅጽ 1 - የቤተሰብን አባላት መጠይቅና የቤተሰብ መጠይቅ
ቅጽ 2 - የልጆች የሥራ ሥምሪት መጠይቅ - በወላጆች/በአሳዳጊ የሚመለሱ
ቅጽ 3 - የልጆች የሥራ ሥምሪት መጠይቅ - በልጆች በራሳቸው የሚመለሱ ናቸው።

የመጠይቆቹ አቀራረብ፣ መጠይቆቹ በማን እንደሚመለሱ፣ ማንን እንደሚመለከቱ እና በመጠይቆቹ ውስጥ የተካተቱ ክፍሎችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

### <u>የመጠይቆች አወቃቀር</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቅጽ 1- የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ እና የአባላት የዲሞግራፊ፣ የሥራ ስምሪትና የማህበራዊ መረጃ | የቤተሰብ አባላት መጠይቅ<br>ለሁሉም የቤተሰብ አባላት፣<br>ከቤተሰብ ኃላፊ ወይም ሌላ አዋቂ የቤተሰብ አባል | ክፍል 1 | የአካባቢ መለያ<br>ለሁሉም የቤተሰቡ ኃላፊ |
| | | ክፍል 2 | ስለቤተሰቡ አባላት ዝርዝር መረጃ<br>ስለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባላት |
| | | ክፍል 3 | ያለፉት 7 ቀናት የሠራ ሁኔታ<br>ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ስለሆኑ የቤተሰብ አባላት |
| | | ክፍል 4 | ያለፉት 12 ወራት የሥራ ሁኔታ<br>ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ስለሆኑ የቤተሰብ አባላት |
| | የቤተሰብ መጠይቅ<br>ከቤተሰብ ኃላፊ ወይም ሌላ አዋቂ የቤተሰብ አባል | ክፍል 5 | ስለ ቤተሰቡ እና ቤተሰቡ ስለሚኖርበት ቤት መረጃ |

| | | |
|---|---|---|
| ቅጽ 2- የልጆች የሥራ ስምሪት መጠይቅ በወቀጆች/አሳዳጊ የሚመለሱ<br>ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት ስለሆኑ ልጆች | ክፍል 1 | የአካባቢ መለያ |
| | ክፍል 6 | የልጆች የፍልሰት ሁኔታ |
| | ክፍል 7 | የልጆች የትምህርት ሁኔታ |
| | ክፍል 8 | ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ሁኔታ እና ምንም አለመሥራት |
| | ክፍል 9 | ባለፋት በማናቸውም ጊዜያት በሥራ ተሰማርተው የሚያውቁ ልጆች ከሠሩት ወይም ከሚሠሩት ሥራ ጋር በተያያዘ የጤና እና የደህንነት ሁኔታን የተመለከቱ ጥያቄዎች |
| | ክፍል 10 | ቤተሰብ/አሳዳጊ ላልሆነ ለሌላ ሰው በክፍያ ወይም ያለ ክፍያ ተቀጥረው ስለሚሠሩ ለጆች |
| | ክፍል 11 | በምርታማ ሥራ የተሠማራ/ች ልጅ አብራቸው በመደበኛነት የሚኖሩ ወላጆች ስለ ልጆቹ ያላቸው አመለካከት |
| ቅጽ 3- የልጆች የሥራ ሥምሪት በልጆች የሚመለሱ<br>ዕድሜአቸው ከ10-17 ስለሆኑ ልጆች | ክፍል 12 | የልጆች የትምህርት፣ የሥራ ሁኔታና በሥራ ላይ ስለሚደርሱ ጉዳቶችና ህመሞች<br>ዕድሜአቸው ከ10-17 የሆኑ ልጆች |

## ሠ. ጥናቱ የሚሸፍነው አካባቢና ከጥናቱ የሚገኘው መረጃ ውጤት የሚዘጋጅበት የአስተዳደር እርከን (Coverage and Reporting Level)

የ1993 የልጆች የሥራ ሥምሪት ናሙና ጥናት መላውን የሀገሪቱን ክልል እንደሚሸፍን ይጠበቃል። ከየክልሉ በጥናቱ የሚሸፈኑ የቆጠራ ቦታዎች እና ቤተሰቦች በሳይንሳዊ መንገድ በናሙና ይመረጣሉ። በዚህም መሠረት በገጠር ለተቀ ናጀ የቤተሰብ ጥናት የተመረጡ 723 የቆጠራ ቦታዎች በጥናቱ የሚሸፈኑ ሲሆን በከተማ ደግሞ 535 ቆጠራ ቦታዎች ይመረጣሉ። ከእያንዳንዱ ከተመረጡት ቆጠራ ቦታዎች 35 ቤተሰቦች በዚህ ጥናት ይሸፈናሉ። ይህ የናሙና መጠን ( Sample Size) ከጥናቱ የሚገኘውን መረጃ ውጤት በሁሉም ክልሎች በገጠርና በከተማ ለይቶ ለማዘጋጀት የሚያስችል ሲሆን በተጨማሪም በትልልቅ ከተሞች ማለትም የሕዝብ ብዛታቸው 100,000 አካባቢና በላይ ለሆኑ የመረጃውን ሪፖርት ለ ማዘጋጀት እንደሚያስችል ታቅዷል። በአጠቃላይ ከላይ በተያዘው የናሙና መጠን መሠረት በገጠርና በከተማ እስከ 43,000 ቤተሰቦች የሚሸፈኑ ሲሆን በነዚህም ቤተሰቦች ውስጥ እስከ 110 ሺ ያህል ልጆች በጥናቱ ይካተታሉ የሚል ግ ምት አለ።

## ረ. ጥናቱ የሚካሄድበት ጊዜ

የ1993 የልጆች የሥራ ሥምሪት ናሙና ጥናት በመጋቢት ወር 1993፤ በጥናቱ የሚገኙትን መረጃዎች በጠቅላላ በአን ድ ላይ ለማጣመር እንዲቻልና ከየሥፍራው የሚገኙትንም መረጃዎች ለማስተያየት/ለማወዳደር እንዲያመች ጥናቶቹ በተመረጡት የቆጠራ ቦታዎች በተመሳሳይ ወቅት እንዲካሄዱ ይደረጋል። ዋናው ጥናት ከመካሄዱ በፊት በሁሉም የቆ ጠራ ቦታዎች የቤቶችና ቤተሰቦች ምዝገባ በሁለት ቀን ውስጥ ተጠናቆ ጥናቱ የሚመለከታቸው ቤተሰቦች ምርጫ ይከ ናወናል። ለዋናው ጥናት የተዘጋጁት መጠይቆች ጥናቱ ከተጀመረ በኋላ ባሉት ስምንት ቀናት ውስጥ መረጃዎች ሁሉ ተሰብስበው መጠናቀቅ ይኖርባቸዋል። በስምንቱ ቀናት ውስጥ መረጃው ተሰብስቦ ካላለቀ፤ በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ በተቻለ ፍጥነት ተሰብስበው እንዲጠናቀቁ ያስፈልጋል። ነገር ግን በመጠይቁ ግርጌ ላይ ለምን መጠይቁ በተ ጠቀሱት ስምንት ቀናት ውስጥ ሊጠናቀቅ እንዳልቻለ ምርመራ በሚለው ሥፍራ ላይ መገለጽ ይኖርበታል። የቤተሰብ አመዘጋገብ ናሙና አመራረጡ ዘዴና አሠራሩ በዚህ መመሪያ ይገለፃል። _

## ሸ. የመረጃ ሰብሳቢዎች ኃላፊነት

በዚህ ጥናት የመረጃ ሰብሳቢው ዋና ኃላፊነት በተመደበበት ቆጠራ ቦታ የሚገኙ ቤተሰቦችን መመዝገብና ለጥናቱ ከ ሚመረጡ 35 ቤተሰቦች ለጥናቱ በተዘጋጀው ቅጽ ላይ ተፈላጊውን መረጃ በጥራት መሙላት ነው። መረጃ ሰብሳቢው ለጥናቱ ስራ መሳካት ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ይታወቃል። ስለሆነም

1. የመረጃ መሰብሰቡን ተግባር በቅንነት፤ በታማኝነትና በታታሪነት ማከናወን ይገባዋል። መረጃ ሰብሳቢው ለጥናቱ መረጃ ለመሰብሰብ ሥራ ወደ ተመረጠው ቤተሰብ በሚደርስበት ወቅት ለቤተሰቡ ሰላምታ በመስጠ ትና ስለመጣበት አላማ በመግለጽ የመረጃ መሰብሰቡን ተግባር መጀመር ይኖርበታል። መረጃው ተሰብስቦ ካለቀ በኋላ ከቤተሰቡ ከመሰናበት በፊት ቤተሰቡን ስላደረገው ትብብር ምስጋና ማቅረብ ተገቢ ነው።

2. መረጃ ሰጭዎችን በሚቀርብበት ጊዜ ወደ መጠይቁ ከመግባት አስቀድሞ ስለተለያዩ ጉዳዮች /ስለወቅቱ ሁኔታ፤ ስለእርሻው፤ ስለጤናቸው፤ ስለልጆቻቸው ... ወዘተ/ መጠያየቅ ከመረጃ ሰጪዎች ጋር መቀራረብንና መግባባትን ስለሚፈጥር በዚህ መልክ የመረጃ መሰብሰቡን ሥራ መጀመር ያስፈልጋል። ይኸም መረጃ ሰጪ ዎች መልሶችን ለመስጠት የበለጠ ዝግጁ ስለሚያደርጋቸው መጠይቁን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመሙላት ይረዳ ል።

3. ትክክለኛ መረጃ የሚገኘው መልስ ሰጪዎችን አግባብ ባለው መንገድ በመቅረብ፤ አስነዋሪ ከሆኑ ድርጊቶ ች በመቆጠብ፤ መረጃ ሰጪዎችን ከማመናጨቅ፤ ንቀት ከማሳየት፤ ከመጸየፍ ... ወዘተ በመታቀብና ረጋ ብሎ ና ሳያቻኩሉ በማዳመጥ እና በመሳሰሉት ድርጊቶች ነው።

4. የልጆች የሥራ ሥምሪት ጥናት የሚሰበሰቡ መረጃዎች የሚጠበቀውን ጥቅም እንዲያስገኙ ለማድረግ በከ ፍተኛ ጥንቃቄና ጥራት ባለው ሁኔታ መረጃዎችን መሰብሰብ ከመረጃ ሰብሳቢዎች ይጠበቃል። ጥራት ባለው መረጃ ላይ የተመረኮዙ ዕቅዶች በትክክል በተግባር መፈጸም ሲቻል በአንፃሩ የመረጃው ጥራት የማያስተማ ምን በሚሆንበት ጊዜ ዕቅዶችን ተግባራዊ በማደረግ ረገድ ችግር ይገጥማል። ለምሳሌ ፕሮጀክቶች ተቀይሰው

በሥራ ላይ ለማዋል በሚያስፈልግበት ጊዜ እንደየፕሮጀክቶቹ አይነት አስፈላጊና ተገቢውን የሰው ኃይል ለማግኘት በጥናት የሚገኙ መረጃዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። በመሆኑም ለየፕሮጀክቶቹ በቦታ፣ በዕድሜ፣በፆታና በመሳሰሉት ባህርያት ላይ የተመሠረተ ትክክለኛ መረጃ ከሌለ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ ከማዳገት አልፎ የተሳሳቱና የታዛቡ አሠራሮችን ይፈጥራል። ስለዚህ ጥናቱ በሚካሄድበት ወቅት ለመልስ ሰጪዎች የሚቀርቡትን ጥያቄዎች በመመሪያው መሠረት በማቅረብና ከዚያም የሚገኘውን ትክክለኛ መልስ በተገቢው ሥፍራ/ዓምድ/ በጥንቃቄና ጥራት ባለው ጽሑፍ በማስፈር መጠይቁን ለመሙላት ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል።

በዚህ ናሙና ጥናት የተካተቱ መረጃዎች በአብዛኛው የቤተሰብ አባላትን ግላዊ ህይወት የሚመለከቱ እና አስቀድሞ ስለተከናወኑ ወይም እየተከናወኑ ስላሉ ክስተቶች የሚጠይቁ በመሆኑ በተቻለ መጠን መረጃዎችን የሚመለከታቸው የቤተሰብ አባላት ባሉበት መሰብሰቡ የመረጃውን ጥራት ከፍ እንደሚያደርገው ይታመናል። በተለይም በቅጽ 3 ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች ከልጆቹ ከራሳቸው ብቻ መሰብሰብ ይገባቸዋል።

በመሆኑም የሚሰበሰቡት መረጃዎች የበለጠ ጥራት እንዲኖራቸው አብዛኞቹ የቤተሰብ አባላት ባሉበት፣ በቤተሰብ ኃላፊው አማካይነት መረጃ መሰብሰብ አለበት። ኃላፊው ካልተገኘ እሱ በሚገኝበት ሌላ ጊዜ ተመልሶ በመምጣት መጠይቁን መሙላት የሚያስፈልግ ሲሆን ኃላፊውን ማግኘት ካልተቻለ ግን መልስ ሊሰጥ የሚችል አዋቂ የሆነ የቤተሰብ አባልን በማነጋገርና ጥያቄዎቹን በማቅረብ መጠይቁ ይሞላል። <u>የአንድን ቤተሰብ መረጃ በምንም ዓይነት መንገድ ጎረቤት የሆኑ ግለሰቦችን ብቻ በማነጋገር መጠይቁ መሞላት የለበትም</u> ።
በሌላ በኩል በቅጽ 3 ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች መመለስ የሚገባቸው በልጆች በራሳቸው ብቻ ስለሆነ በመጀመሪያው ጉብኝት ወቅት ልጆች ቤት ያለተገኙ ከሆነ መረጃ ሰብሳቢው ልጆች የሚገኙበትን ቀንና ስዓት አጣርቶ ተደጋጋሚ ጉብኝት በማድረግ ተፈላጊውን መረጃ መሙላት አለበት። ቅጽ 3 በምንም ዓይነት ሁኔታ ከልጆቹ ከራሳቸው ውጪ ሌላ የቤተሰብ አባልም ሆነ ጎረቤት በማነጋገር አይሞላም። ቅጽ 3 በሚሞላበት ወቅት በተቻለ መጠን ሌሎች ሰዎች እንዳይገኙ ማድረግ ይገባል። በተጨማሪም መጠይቁ በሚሞላበት ጊዜ አንዳንድ መረጃዎችን ለማግኘት ካልተቻለ ወደ ቤተሰቡ በሌላ ጊዜ በመመለስ መረጃውን የመሰብሰብ ተግባር መጠናቀቅ ይኖርበታል።

መረጃው ተሰብስቦ ካለቀ በኋላ ከቤተሰቡ ከመሰናበት አስቀድሞ ስለቤተሰቡ አስፈላጊው መረጃዎች በትክክል ተሰብስቦ መጠናቀቁን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው። መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ተፈጽመው የነበሩ ስሕተቶች እዚያው ከታረሙ በኋላ መረጃ ሰጭዎችን ከመሰናበት በፊት ማመስገንም መዘንጋት የለበትም። በዚያው ቀን የመረጃው ጥራት እንደገና ታይቶ ከተረጋገጠ በኋላ ቀንና ስም ተጽፎ መፈረም ይኖርበታል። የመረጃው ጥራት በዚያው ቀን መረጋገጥ የሚኖርበት ብዙ ቀናት ካለፉ መረጃውን ተመልሶ ከቤተሰቡ ለማግኘት ስለሚያስቸግር ነው። በተጨማሪም የተደረገው ቃለ መጠይቅ ስለሚረሳ መረጃዎቹን ለማረም አዳጋች ይሆናል።

## ቀ. <u>የመረጃ ሰብሳቢዎች ተግባር</u>

በዚህ ጥናት ለመሰብሰብ የታቀደውን መረጃ በትክክል ለመሰብሰብ መረጃ ሰብሳቢዎች የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም ይጠበቅባቸዋል።

1. የሚሰጣቸውን ስልጠና በትጋት መከታተል፣ ለመረጃ ሰብሳቢዎች የተዘጋጀውን መመሪያ አንብቦ መረዳትና የመጠይቆቹን ቅርጽ እና ይዘት ሙሉ በሙሉ ማወቅ፤
2. ወደ መስክ ከመውጣታቸው በፊት አስፈላጊ ቅጾቹንና ማቴሪያሎችን ሁሉ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤
3. በተለይ በከተማ ቆጠራ ቦታ ለሚሠሩ የተመደቡበትን ቆጠራ ቦታ ካርታ በማንበብ ድንበሩን በትክክል መለየት፤
4. በቆጠራ ቦታ ውስጥ የሚገኙ ቤቶችና ቤተሰቦችን እየዞሩ በቅጽ 93/0 መመዝገብ፣ በምዝገባ ወቅት የቤተሰቦች መዘለል ወይም ተደግሞ መመዝገብ እንዳይኖር ጥብቅ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፤
5. <u>በቅጽ 93/0</u> ከተመዘገቡት ቤተሰቦች መካከል ጥናቱ የሚሸፍናቸውን ቤተሰቦች ስለአመራረጡ በተሰጠው መመሪያ
   መሠረት በትክክል መምረጥ፣ የተመረጡትን ቤተሰቦችም <u>በቅጽ 93/1</u> ማስተላለፍ፤
6. ለጥናቱ ወደተመረጡ ቤተሰቦች ተራ በተራ በመሄድ

   ሀ)

   ለጥናቱ ከተዘጋጁ መጠይቆች ውስጥ ቅጽ 1ን አስቀድሞ መሙላት፣ መጠይቆቹ የሚሞሉት በተሰጠው መመሪያ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ በቅጽ 1 ዓምድ 53 ላይ ዕድሜአቸው 5-17 የሆኑ ልጆች መለየት ለሚቀጥሉት ቅጾች አሞላል ወሳኝ በመሆኑ መረጃ ሰብሳቢዎች ይህን ዓምድ በከፍተኛ ጥንቃቄ ሊሞሉት ይገባል።

ለ)

የቤተሰብ አባላት መጠይቅ ከተጠናቀቀ በኋላ በቤተሰቡ ውስጥ ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት የሆናቸው ልጆች ካሉ ተራ በተራ ቅጽ 2 ይሞላላቸዋል ይህም የሚሆነው ስለነዚህ ልጆች ቅጽ 3 ከመሞላቱ አስቀድሞ ነው። በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት ለሆናቸው ልጆች ቅጽ 2 ከተጠናቀቀ በኋላ በቅጽ 3 ስለእያንዳንዳቸው ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት ለሆናቸው ልጆች መረጃ ይሰበሰባል። ቅጽ 3 ላይ ያሉ ጥያቄዎች መመለስ ያለባቸው ከልጆቹ ከራሳቸው በመሆኑ ልጆቹ በመጀመሪያ ጉብኝት ወቅት እቤት የሌሉ ከሆነ ቀጠሮ በመስጠት ሌላ ጊዜ ወደ እዛ ቤተሰብ ተመልሶ በመምጣት ልጆቹን ራሳቸውን በማነጋገር ቅጹ መሞላት አለበት።ጉብኝት ስለሚደረግባቸው ልጆች ማስታወሻ ለመያዝ እንዲቻል በመጠይቁ መጨረሻ ገጽ ላይ ፎርም ተዘጋጅቷል።

ሐ)

ቅጽ 1 የቤተሰብ አባላት መጠይቅ፣ ቅጽ 2፣ እና ቅጽ 3 ከተሞሉ በኋላ ስለቤተሰቡ እና ቤተሰቡ ስለሚኖርበት ቤት በቤተሰብ መጠይቅ ላይ የቤተሰቡን ኃላፊ ወይም ሌላ አዋቂ የሆነ ሰው በማነጋገር የቤተሰብ መጠይቅ ይሞላል። ነገር ግን አንድ ወይም ከዛ በላይ ልጆች ለጊዜው እቤት ሳይኖሩ ቀርተው ቀጠሮ ተይዞ ከሆነ መረጃ ሰብሳቢው ከቤተሰቡ ጋር ከመሰናበቱ በፊት የቤተሰብ መጠይቅን መሙላት አለበት።

7. ለአንድ ቤተሰብ እና ቤተሰቡ ውስጥ ስለሚገኙ ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት የሆናቸው ልጆች መሞላት የሚገባቸው መረጃዎች ተሞልተው ከተጠናቀቁ መረጃ ሰብሳቢው ለመጨረሻ ጊዜ መጠይቆቹን መመርመር አለበት። ስህተት ከተገኘም ወዲያውኑ እርማት ማድረግ ያሻል።
8. የተሞሉ መጠይቆች ያንዱ ቤተሰብ ከሌላው ሳይደባለቅ በጥንቃቄ መያዝ አለባቸው።
9. መረጃ ሰብሳቢው በተቆጣጣሪው አማካይነት የሚሰጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል።

# ምዕራፍ 2

## ቅጽ 1 - የክፍል 1 እና ክፍል 2 አሞላል መመሪያ

ለጥናቱ የተዘጋጁት መጠይቆች ቅጽ 1፣ ቅጽ 2 እና ቅጽ 3 በመባል ይለያሉ። ቅጽ 1 የቤተሰብ አባላትና የቤተሰብ መጠይቅን ይዟል። ቅጽ 1 በአምስት ክፍሎች ተከፍሏል። በዚህ ምዕራፍ የክፍል 1 እና የክፍል 2 የአሞላል መመሪያ ይቀርባል።

### ክፍል 1 የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ

ይህ ክፍል ለተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ መለያ መመዝገቢያ የሚያገለግል ሲሆን በእያንዳንዱ የመጠይቁ ገጽ ላይም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚሞላ ነው። ይህ ክፍል ለአሠራር ቀለል ያለ ቢሆንም ስህተቶችና ግድፈቶች ስለሚታዩ በጥንቃቄ መሞላት አለበት።

ስለዚህ፡-

ሀ. የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የመሳሰሉትን ስሞች በግልጽ በሚነበብ ሁኔታ መመዝገብ ያስፈልጋል። ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ።

ለ. በቁጥር የሚታወቁ ዞኖች ወይም ወረዳዎች ወይም ገበሬ ማህበራት ቁጥሮቹ እንደ ኮድ እንዳይወሰዱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

**ዓምድ 1** **<u>የጥናቱ መለያ</u>**

የጥናቱ መለያ በቢሮ የሚሞላ ስለሆነ በካርድ ኮለሞቹ ምንም አይሞላም።

**ዓምድ 2** **<u>ክልል</u>፡-**

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም የሚመዘገብበት ነው። ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ።

**ዓምድ 3 እና 4** **<u>ዞንና ወረዳ</u>፡-**

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞንና ወረዳ ስሞች በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ይመዘገባሉ። ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ።

**ዓምድ 5** **<u>ከተማ</u>፡-**

ለከተማ መጠይቅ ጥናቱ የሚመለከተው ከተማ ስም የሚሞላ ሲሆን ለገጠር ግን በሰረዝ ይታለፋል። ካርድ ኮለሙ ባዶ ይተዋል።

**ዓምድ 6** **<u>ከፍተኛ/ወረዳ</u>፡-**

ለከተማ መጠይቅ ጥናቱ የሚመለከተው ከፍተኛ/ወረዳ ስም ወይም የወረዳ ቁጥር ሲሞላ ለገጠር ግን በሰረዝ ይታለፋል። ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ።

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- አብዛኛው ከተሞች በወረዳ ሥር ስለሚሆኑ በዓምድ 4 የሚገኙበት ወረዳ ስም ሲሞላላቸው በዓምድ 6 ደግሞ የ«ከፍተኛው» ስም/ቁጥር ይሞላል። ነገር ግን አንዳንድ ከተሞች በወረዳ ውስጥ ሳይሆኑ የራሳቸው አስተዳደር ያላቸው ሆነው የተሸነሸኑት ደግሞ በከፍተኛ ሳይሆን በወረዳ ይሆናል (ለምሳሌ አዲስ አበባ)። በዚህን ጊዜ ዓምድ 4 በሰረዝ ይታለፍና በዓምድ 6 በከፍተኛው ምትክ የወረዳው ቁጥር/ስም ይመዘገባል ማለት ነው።

**ዓምድ 7** **<u>ቀበሌ/ገበሬ ማህበር</u>፡-**

በዚህ ዓምድ ለከተማ የቀበሌው ቁጥር/ስም ሲሞላ ለገጠር ደግሞ የገበሬ ማህበሩ/የጣቢያው ስም/ቁጥር ይሞላል። ካርድ ኮለሞቹ ባዶ ይተዋሉ።

**ዓምድ 8** **<u>የቆጠራ ቦታ ኮድ</u>፡-**

በዚህ ዓምድ ሥር በሚገኙ ካርድ ኮለሞች ለጥናቱ ለተመረጠው የቆጠራ ቦታ የተሰጠው የመለያ ኮድ ይሞላል።

**ዓምድ 9** **<u>የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር</u>፡-**

በዚህ ዓምድ ሥር በሚገኙ ካርድ ኮለሞች ጥናቱ የሚመለከተው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር ይሞላል። ይህ ተራ ቁጥር የሚገኘው በቤቶችና ቤተሰቦች በመመዝገቢያ ቅጽ 93/0 ክፍል 2 ለከተማ ዓምድ 13፣ ለገጠር ደግሞ ዓምድ 9 ነው።

## ዓምድ 10 የቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም፡-

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ የቤተሰቡ ኃላፊ ማን እንደሆኑ አጣርቶ በመጠየቅ የኃላፊው ስም ፣ የአባት ስምና የአያት ስም ጭምር መመዝገብ ይኖርበታል።

## ዓምድ 11 የመልስ ሰጪ የመስመር ቁጥር፡-

በዚህ ዓምድ ስር ባሉት ካርድ ኮለሞች በዚህ ቅጽ ስለቤተሰቡ አባላትና በአጠቃላይ ስለቤተሰቡ ዝርዝር መረጃ የሰጠው ግለሰብ ተራ ቁጥር ከክፍል 2 ከዓምድ 12 ተወስዶ የሚሞላበት ነው። በተጨማሪም ይህ ዓምድ የሚሞላው ቅጽ 1 ተሞልቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ስለሆነ እንዳይዘነጋ ማስታወስ ያስፈልጋል።

# ክፍል 2 ስለቤተሰቡ መደበኛ አባላት ዝርዝር መረጃዎች (ከዓምድ 12-23)

በዚህ ክፍል ውስጥ የሁሉም መደበኛ ቤተሰብ አባላት ስም ዝርዝር፣ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና፣ ጾታቸው፣ ዕድሜያቸው፣ ኃይማኖት፣ ብሔረሰብ፣ እንዲሁም ዕድሜያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የትምህርት ሁኔታ እና ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው ደግሞ የስልጠናና የጋብቻ ሁኔታ ዝርዝር መረጃ ይሰበሰባል።

## ዓምድ 12 የቤተሰብ መደበኛ አባላት ተራ ቁጥር

ይህ ዓምድ በቅድሚያ ለአስራ አንድ ወይም ከዚያ ላነሰ የቤተሰብ አባላት ለመመዝገብ እነደሚበቃ ተደርጎ ተዘጋጅቷል። ነገር ግን የቤተሰብ አባላት ብዛት ከአስራ አንድ በላይ ከሆነ ሌላ ተጨማሪ መጠይቅ መጠቀም ይስፈልጋል። እንዲሁም በተጨማሪው መጠይቅ በዓምድ 12 ከ01-11 ያሉትን ቁጥሮች በመሠረዝ በምትካቸው 12፣ 13፣ . . . ወዘተ በማለት የቤተሰቡ መደበኛ አባላት በሙሉ እስከተመዘገቡ ድረስ ተከታታይ ተራ ቁጥር በዓምድ 12 ይሰጣል። በመጠይቁ አናት ላይም የቀጠለ ተብሎ ይፃፋል።

## ዓምድ 13 የቤተሰብ መደበኛ አባላት ሙሉ ስም፡-

በዚህ ዓምድ ላይ በተመረጠው ቤተሰብ ውስጥ በመደበኛነት የሚኖሩ የቤተሰብ አባላት በጠቅላላ ይመዘገባሉ። በምዝገባው ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር ያሉ መደበኛ የቤተሰብ አባላትና ለጊዜው እቤት ውስጥ ያልተገኙ መደበኛ አባላት ስም በዓምዱ ውስጥ ሲመዘገብ፣ በወቅቱ ከቤተሰቡ ጋር የሚገኙ እንግዶች ግን አይመዘገቡም።

የቤተሰቡ አባላትን ስም በትክክል ከመመዝገብ በፊት የቤተሰብ መደበኛ አባላት የሚባሉት እነማን እንደሆኑ በቅድሚያ ጠንቅቆ መረዳት እንዲቻል ማብራሪያው ከዚህ በታች ቀርቧል። እንዲሁም በቅጽ 93/0 አሞላል መመሪያ ላይ የተገለጸውን የቤተሰብና የቤተሰብ ኃላፊ ትርጉም ማስታወስ ያስፈልጋል።

<u>መደበኛ የቤተሰብ አባል፡-</u> አንድ ሰው መደበኛ የቤተሰብ አባል ነው የሚባለው ቢያንስ ስድስት ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ከቤተሰቡ ጋር የኖረ እንደሆነ ነው። ከቤተሰቡ ጋር ለዘለቄታው ለመኖር የመጡ ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል ይቆጠራሉ። ከስድስት ወር በታች ከቤተሰቡ ለጊዜው ተለይተው የቆዩ የቤተሰብ አባላት እንደመደበኛ የቤተሰቡ አባል መቆጠር አለባቸው፣ ነገር ግን ከቤተሰቡ ተለይተው ከሄዱ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው፣ ወይም ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት አቅደው የሄዱ ከቤተሰቡ ከወጡ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል አይቆጠሩም።

<u>የሚከተሉት የቤተሰብ አባላት እንደ መደበኛ የቤተሰብ አባል መቆጠር ይኖርባቸዋል።</u>

1. በጥናቱ ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር ቢያንስ ለስድስት ወር የቆዩ።
2. ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም ከቤተሰቡ ጋር ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ለመቆየት ዕቅድ ያላቸው ሁሉ፡- <u>ለምሣሌ</u>፡- ባል አግብታ ከወላጆችዋ ቤት ወደ ባልዋ የሄደች ሴት ስድስት ወር ባይሞላትም የባሏ ቤተሰብ መደበኛ አባል ትሆናለች ማለት ነው። እንዲሁም ሥራ አግኝቶ/ታ ለዘለቄታው ለመኖር ወደ ሌላ ቤተሰብ የሄደ/ች ስድስት ወር ባይሞላው/ትም በጥናቱ ወቅት የተገኘበት/ችበት ቤተሰብ አባል ይሆናል/ትሆናለች።
3. የቤት ሠራተኞች አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር የሚያድሩና ሌላ መኖሪያ የሌላቸው ሁሉ።

4. በጥናቱ ጊዜ ከስድስት ወር ላነሰ ከቤተሰቡ ለጊዜው የተለዩ፣ <u>ለምሣሌ</u>፡- በዕረፍት ላይ ያሉ፣ በዓመት በዓል ወደ ሌላ ቦታ የሄዱ፣ ሆስፒታል የገቡ፣ ዘመድ ለመጠየቅ የሄዱና ከሥራቸው ጋር በተያያዘ ጉዳይ ለጊዜው ከቤተሰቡ የተለዩ አባላትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

5. ሌላ መኖሪያ ሥፍራ የሌላቸውና በጥናቱ ወቅት ከቤተሰቡ ጋር የሚኖሩ አባላት ሁሉ፣ <u>ለምሣሌ</u>፡- በተለያዩ ቤቶች እያቀያየሩ ለሚኖሩና መደበኛ መኖሪያ የሌላቸው ግለሰቦች በጥናቱ ወቅት በሚገኙበት ቤተሰብ እንደ መደበኛ አባል ተቆጥረው ይመዘገባሉ፡፡

6. **<u>ተማሪዎች</u>**፡- ከቤተሰቦቻቸው፣ ከወላጆቻቸው፣ ከመደበኛ የመኖሪያ ሥፍራቸው ተለይተው በመደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ በኮሌጆች፣ በዩኒቨርስቲዎች ... ወዘተ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት አካባቢ መደበኛ ነዋሪዎች ሆነው መመዝገብ አለባቸው፡፡ በአዳሪ ት/ቤት የሚማሩ ተማሪዎች እንዲሁም ከወላጆቻቸው ተለይተው ቤት ተከራይተው ወይም ከዘመድ ተጠግተው እየኖሩ የሚማሩ ተማሪዎች ምንም እንኳን በየሳምንቱ ወይም በየአሥራ አምስት ቀን ስንቅ ለማምጣት ወይም ወላጆቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ቤተሰቦቻቸው ቢሄዱም እንደ መደበኛ የቤተሰብ አባል የሚታሰቡት በሚኖሩበት አካባቢ እንጂ በወላጆቻቸው ቤት አይደለም፡፡ ነገር ግን ከመደበኛ መኖሪያቸው (ከቤታቸው) በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤቶች እየተመላለሱ የሚማሩ ተማሪዎች ሁሉ የሚኖሩበት ቤተሰብ መደበኛ አባል ሆነው መመዝገብ አለባቸው፡፡

የቤተሰብ አባላት የምዝገባ ቅደም ተከተል በሚከተለው መልክ መሆን ይኖርበታል፡፡

- የቤተሰብ ኃላፊ
- የኃላፊው ሚስት ወይም ባል
- ያላገቡ ልጆች በዕድሜ ቅደም ተከተል
- ያገቡ ልጆች እና እዚሁ ቤት አብረው የሚኖሩ የቤተሰባቸው አባላት
- ሌሎች ዘመዶች
- ዘመድ ያልሆኑ አባላት (ከኃላፊው ጋር ምንም የስጋም ሆነ የጋብቻ ዝምድና የሌላቸው)

መልስ ሰጭዎች የቤተሰብ አባላትን ዘርዝረው በሚያስመዘግቡበት ጊዜ ስም፣ ዝምድናና ጾታቸውን በአንድ ላይ ሊያስመዘግቡ ይችላሉ፡፡ በመጨረሻም የተመዘገቡትን የቤተሰብ አባላት ስም ለመልስ ሰጪው ማንበብና የተዘነጉ አባላት እንዳይኖሩ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በምዝገባው ወቅት ሕጻናት፣ አዛውንቶችና ሠራተኞች እንዳይዘነጉ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ዓምድ 14 <u>ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና</u>፡-

የቤተሰብ አባላት አመዘጋገብ ቅደም ተከተል ሲዘረዘር ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ የቤተሰቡ ኃላፊ ሁልጊዜ በመጀመሪያው መሥመር ላይ ይመዘገባል /ትመዘገባለች/፡፡ አንድ ሰው ብቻ በሚኖርበት ቤተሰብ ግለሰቡ ኃላፊ ተብሎ ይጠቀሳል፡፡ ከአንድ በላይ የሆኑ አባላት በሚኖሩበት ቤተሰብ ውስጥ በኃላፊነት የሚጠቀሰው/የምትጠቀሰው የቤተሰቡ አባላት ቤተሰቡን በኃላፊነት ይመራል/ትመራለች/ ብለው የሚያምኑበት /የሚያምኑባት/ ግለሰብ ነው/ናት/፡፡ የሌሎቹ የቤተሰብ አባላት ዝምድና ከኃላፊው/ከኃላፊዋ/ወይም ከሚስትየዋ ወይም ከባልየው ጋር ባላቸው ዝምድና መሠረት በካርድ ኮለሙ ይሞላል፡፡

| | |
|---|---|
| 01 = ኃላፊ | 07 = የኃላፊ/የባለቤት ወንድም/እህት |
| 02 = ሚስት/ባል | 08 = የማደጎ ልጅ |
| 03 = የኃላፊና የባለቤት ልጅ | 09 = የጡት/የክርስትና ልጅ |
| 04 = የኃላፊ ልጅ | 10 = የልጅ ልጅ |
| 05 = የባለቤት ልጅ | 11 = ሌሎች ዘመዶች |
| 06 = የኃላፊ/የባለቤት አባት/እናት | 12 = ዝምድና የሌላቸው (ከኃላፊው ጋር ምንም የሥጋም ሆነ የጋብቻ ዝምድና የሌላቸው) |

## ዓምድ 15 <u>ጾታ</u>፡-

በዚህ ዓምድ በተሰጠው ክፍት ቦታ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ጾታ በመጠየቅ የሚሞላ ሲሆን በካርድ ኮለሙ ደግሞ ጾታው ወንድ ከሆነ ኮድ 1፣ ሴት ከሆነች ኮድ 2 ይሞላል፡፡ በስም ብቻ ጾታው ምን እንደ ሆነ ማወቅ ስለማይቻል የእያንዳንዱን አባል ጾታ ጠይቆ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡ የአንዳንድ ሰዎች ስም ለሁለቱም ጾታዎች ሊያገለግል ሰለሚችል የአባላቱን ስም ብቻ መሠረት በማድረግ ጾታቸውን በግምት መሙላት ስህተት ያስከትላል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ወንዶች በሴት ስም እንዲሁም ሴቶች በወንድ ስም ስለሚጠሩ ጾታ በሚሞላበት ጊዜ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ዓምድ 16 <u>ዕድሜ</u>፡-

___ እድሜዎ ስንት ዓመት ነው? ብሎ በመጠየቅ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ይህ ጥናት በሚካሄድበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት (በጨረሱት ዓመት) በዚህ ዓምድ ስር ባሉ ካርድ ኮለሞች ይመዘገባል፡፡ ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችና ቀኖች በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው፡፡ <u>ለምሳሌ</u>፡- የአንድ ሰው ዕድሜ 15 ዓመት ከ 11 ወር ከ10 ቀን ቢሆን መመዝገብ ያለበት 15 ዓመት ብቻ ይሆናል እንጂ 16 ዓመት ሊሞላው 20 ቀን ስለቀረው 16 ዓመት ተብሎ መሞላት የለበትም፡፡ የአንድ ህፃን ዕድሜ ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ በዓምድ 16 ኮድ «00» ይመዘገባል፡፡ እንዲሁም የአንድ ሰው ዕድሜ 97 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ ኮድ «97» ብቻ በካርድ ኮለሙ ይመዘገባል፡፡

ዕድሜያቸውን በትክክል የማያውቁ ወይም ዕድሜያቸውን ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች እንደሚያጋጥሙ ይገመታል፡፡ ስለዚህ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ትክክለኛ ዕድሜ በተቻለ መጠን ለማግኘት ባለመሰልቸት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከሚያስችሉት ዘዴዎች መካከል ቀጥሎ የተመለከቱትን ማጤን ይገባል፡፡

ሀ. መልስ ሰጪው በተወለደበት ጊዜ/አካባቢ በብሄራዊ ደረጃ ወይም በሚኖርበት አካባቢ የተፈፀመ ታሪካዊ ድርጊት እንዳለና ቀጥሎም መልስ ሰጪው ድርጊቱ በተፈፀመ ጊዜ ዕድሜው ምን ያህል እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ እንደተወለደ በመጠየቅና ከዚያም ይህንን መረጃ መሠረት በማድረግ የግለሰቡን ዕድሜ ለመገመት መሞከር ያስፈልጋል፡፡

<u>**ለምሳሌ**</u>፡- ግለሰቡ የ1966 አብዮት ከመፈንዳቱ 10 ዓመት ቀድሞ የተወለደ እንደሆነ የግለሰቡ ዕድሜ በ1993 ዓ.ም. ከሞላ ጎደል (1993-1966)+10=
37 ዓመት ይሆናል፡፡ ስለዚህ የአንድን ግለሰብ ዕድሜ ታሪካዊ ድርጊቶች ከተፈፀሙበት ዓመተ ምሕረት ጋር በማዛመድ ለመገመት ስለሚቻል ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈፀሙበት ዓመተ ምሕረት ዝርዝር በዚህ መመሪያ መጨረሻ ገጽ <u>በእዝል 1</u> ተያይዞ ይገኛል፡፡

ለ. አንዳንድ የቤተሰብ አባላት ወይም በአካባቢው የሚኖሩ ግለሰቦች ዕድሜያቸውን በትክክል ሊያውቁና ሊናገሩ ይችሉ ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ ዕድሜያቸውን የማያውቁትን ሰዎች ዕድሜ ከነዚህ ዕድሜያቸውን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል፡፡

ከቤተሰቡ አባላት መካከል የአንዱ ዕድሜ በትክክል ከታወቀ፣ የሌሎችን ዕድሜ ለመገመት ይቻል ይሆናል፡፡ <u>ለምሳሌ</u>፡- የአንድ ቤተሰብ የመጀመሪያው ልጅ ዕድሜው 13 ዓመት መሆኑ ከታወቀና የእናቱን ዕድሜ ለማወቅ ቢፈለግ የእናቱ ዕድሜ ቢያንስ 29 ዓመት ብሎ ለመገመት ይቻላል፡፡ ይህም ሊገኝ የሚችለው እናቶች አብዛኛውን ጊዜ በ16 ዓመት የመጀመሪያውን ልጅ ይወልዳሉ ተብሎ ስለሚገመት የእናትየዋ ዕድሜ 16+13 =
29 ይሆናል፡፡ የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የአንዱን ዕድሜ ከሌላው በማነፃፀር ዕድሜያቸውን ለመገመት ይቻላል፡፡ <u>ለምሳሌ</u>፡- አብዛኛውን ጊዜ እናቶች በየሁለት ዓመት ይወልዳሉ፤ የትንሹ ልጅ ዕድሜ 7 ዓመት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ የታላቁ ልጅ ዕድሜ 9 ዓመት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም አንድ አባል ባገባበት ጊዜ ዕድሜው ስንት እንደነበረና በጋብቻ ስንት ዓመት እንደቆየ ከታወቀ ዕድሜውን ለመገመት ይቻላል፡፡ ዕድሜያቸው የገፉ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ዕድሜያቸውን በጣም ከፍ ያደርጉታል፡፡ የነኚህን ሰዎች ዕድሜ ከመጀመሪያው ልጃቸውና ከልጅ ልጆቻቸው ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የአንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ ከታወቀ ከሌላው አባል ጋር በማዛመድ በተቻለ መጠን ትክክለኛ የሆነውን ገምቶ መፃፍ ያስፈልጋል፡፡

ሐ. አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሃዞች ለመናገር ይፈልጋሉ ወይም ይቀላቸዋል፡፡ ስለዚህ ዕድሜያቸውን መግለፅ የሚገባቸው ለመናገር በሚቀላቸው ወይም በሚፈልጉት ሳይሆን፣ ትክክለኛውን ዕድሜ ለማግኘት መሞከር ያስፈልጋል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በእርግጥ ዕድሜያቸው 10፣ 15፣ 20፣ 25፣ ... ወዘተ ሊሆን ስለሚችል ይህንንም ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

መ. ዕድሜያቸው ከ10 ዓመት ያላለፉ ሕፃናት ልጆች የተወለዱበትን ጊዜ ወላጆቹ ሊያስታውሱት ስለሚችሉ የሕፃናትና ትናንሽ ልጆች ዕድሜ በሙሉ ዓመት በትክክል መፃፍ አለበት፡፡ አልፎ አልፎ የሕፃናትን ትክክለኛ ዕድሜ ለማግኘት ቀላል የማይሆንበት ሁኔታ ካጋጠመም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ትክክለኛውን ዕድሜ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ በላይ የተሰጡትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ዕድሜ ለማግኘት ትክክለኛ መልሶችን ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማቅረብና በማስላት በቂ ጥረት ከተደረገ በኋላ ትክክለኛው ዕድሜ በሙሉ ዓመት ይፃፋል፡፡

## ዓምድ 17 ሃይማኖት፤ ............................ ሃይማኖትዎ ምንድን ነው?

ሃይማኖት አንድ ግለሰብ የሚከተለው እምነት ወይም የመንፈሳዊ ድርጅት አባልነት ነው፡፡ የሃይማኖትን ዓይነት የሚመለከት ጥያቄ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በማቅረብ ይህን ዓምድ መሙላት ያስፈልጋል፡፡ ሃይማኖት በሚጠየቅበት ጊዜ ክርስቲያን የሚል መልስ ከተገኘ በዚህ ዓምድ ከኮድ 1-3 ከተሰጣቸው ውስጥ የትኛው መሆኑ ተጣርቶ ይሞላል፡፡

1= ኦርቶዶክስ (ተዋህዶ፣ ቅባት፣ ፀጋ)

2= ፕሮቴስታንት (ሰባት ቀን አድቬንቲስት፣ ጴንጤቆስጤ፣ ሎተሪያን መካነየሱስ፣ ባፐቲስት፣ መነናይት፣ እንግሊካን፣ ፕረስፒተርያን፣ መሰረተ ክርስቶስ፣ ሙሉ ወንጌል፣ ቃለ ሕይወት፣ ...ወዘተ)

3= ካቶሊክ

4= እስላም (ሙስሊም ነኝ ካሉም «እስላም» መሆኑ ይታወቅ)

5= ባህላዊ አምልኮ

6= ሌላ (<u>ለምሳሌ</u>፡- ሂንዱ፣ ይሁዳ፣ ብሃይ፣ ጆአቫ፣ ኤቲስት፣ .... ወዘተ)

አንዳንድ ጊዜ የቤተሰቡን ኃላፊ ሃይማኖት በመውሰድ የሌሎችን የቤተሰቡን አባላት ሃይማኖት ለመገመት ይሞከር ይሆናል፡፡ ይህ ትክክል ሊሆን ስለማይችል የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ሃይማኖት በመጠየቅ የተገኘውን መልስ መሠረት በማድረግ የግለሰቡን የሃይማኖት ዓይነት በትክክል የሚወክለው ኮድ በዓምዱ ስር ባለው ካርድ ኮለም መሞላት አለበት፡፡ ባልና ሚስት የተለያየ ሃይማኖት ሊኖራቸው ይችላል፡፡

ለሕፃናት የሚሞላው የሃይማኖት ዓይነት ወላጆቻቸው የሚከተሉት ሃይማኖት ይሆናል፡፡ የተለያዩ ሃይማኖት ከሚከተሉ ወላጆች ለተወለደ ሕፃን ወደፊት ሊከተለው ይችላል ብለው ወላጆቹ የሚያስቡትን ሃይማኖት በመውሰድ በዓምዱ ስር ባለው ካርድ ኮለም ይሞላል፡፡

## ዓምድ 18 ብሄረሰብ ........ ብሄረሰብዎ ምንድን ነው?

የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ብሄረሰብ ምን እንደሆነ ተጠይቆ በዓምድ 18 በተሰጠው ክፍት ቦታ ተፅፎ ትክክለኛው ኮድ በካርድ ኮለሞቹ ይመዘገባል፡፡ ግለሰቡ ብሄረሰብህ ምንድነው ተብሎ ሲጠየቅ ትርጉሙን ባለመረዳት ጥያቄውን በትክክል ለመመለስ ከተቸገረ ዘርህ፣ ትውልድህ፣ ነገድህ፣ ጎሳህ፣ በማለት በማብራራት ማስረዳት ያስፈልጋል፡፡ የብሄረሰቦችን ስምና ኮድ በቀላሉ ለማግኘት እንዲያመች ሁለት ዝርዝሮች ማለትም የዋና ዋና ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር እና የቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ሥምና ኮድ <u>ዝርዝር በሚከተሉት ገፆች ቀርበዋል</u>፡፡ ይኸን በመገንዘብ የብሄረሰብ ስምና ኮድ አመዘጋገብ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1. ለብሄረሰብ መፃፊያ በተሰጠው ቦታ መልስ ሰጪው የሰጠው የብሄረሰብ ስም ይመዘገባል፡፡ የብሄረሰባቸውን ስም ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ግለሰቦች ካጋጠሙ በተቻለ መጠን አግባብቶ ትክክለኛውን መልስ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

2. መልስ ሰጭው ላስመዘገበው ብሄረሰብ የተሰጠው ትክክለኛ ኮድ የዋና ዋና ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝርን በመመልከት በካርድ ኮለሞች ይመዘገባል፡፡ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ብሄረሰቡን ለማግኘት አስቸጋሪ ከሆነ የቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝርን በመመልከት ለማግኘት ይቻላል፡፡

3. መልስ ሰጪው የሰጠው መልስ ዋናው/ግንድ ብሄረሰብ ወይም የግንድ ቅርንጫፍ ብሄረሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ የተሰጠው መልስ ቅርንጫፍ ብሄረሰብ ከሆነ ቅርንጫፍ ብሄረሰቡ የየትኛው ዋና ወይም ግንድ ብሄረሰብ አካል እንደሆነ በመለየት የሚሰጠው ኮድ የዋናው ወይም የግንድ ብሄረሰብ ኮድ ይሆናል፡፡ <u>ለምሳሌ</u>፡- በዓምዱ የተመዘገበው ብሄረሰብ ስም ጋይንቴ ቢሆን ግንዱ አማራ ስለሆነ በካርድ ኮለሙ የሚሞላው «04» ነው፡፡ ይኸውም የአማራ ብሄረሰብ መለያ ኮድ ነው፡፡ በዓምዱ የተመዘገበው የብሄረሰብ ስም እነቆር ቢሆን ግንዱ ጉራጌ ስለሆነ በካርድ ኮለሙ «25» ... ወዘተ ይሞላል፡፡

### ሀ. <u>የዋና ዋና ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር</u>

በዚህ ዝርዝር ውስጥ ሁሉም ብሄረሰቦች የቀረቡ ሲሆን አቀማመጣቸውም ዋና ዋና ብሄረሰቦችን በመጠቀም ነው፡፡ የዋናው ብሔረሰብ ሞክሼ ስሞችና ቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ከዋናው ብሄረሰብ ጋር

ተመሣሣይ ኮድ ስለሚሰጣቸው በቅንፍ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ኤርቦሬ፣ ኡልዴ፣ ሙርሴ፣ የ
ሚባሉ ቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ሁሉ አርቦሬ በሚባል ዋና ብሔረሰብ ስር የሚጠቃለሉ በመሆናቸው
በዝርዝሩም ውስጥ አርቦሬ እንደ ዋና ብሄረሰብ ተፅፎ ሌሎቹ በቅንፍ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ የብሄረሰ
ብን መረጃ በትክክል ለመመዝገብ እንዲያመች ተመሣሣይነት ያላቸው ብሄረሰቦች ሁሉ ዋነኛውን
ብሄረሰብ ተከትለው በዝርዝሩ ላይ ትንሽ ገባ እየተደረጉ የቀረቡ ሲሆን ለነዚህም የራሳቸው የተለ
የ ኮድ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ዶርዜ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ኮንታ፣ ኩሎ፣ መሎ የሚባሉ ብሔረሰቦች ከ
ወላይታ ብሔረሰብ ጋር በጣም ስለሚቀራረቡ በዝርዝሩም ውስጥ ከወላይታ ቀጥሎ በተከታታይ ቀ
ርበዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ብሔረሰቦች ሁሉ ራሳቸውን የቻሉ የተለያየዩ ብሄረሰቦች ስለሆኑ የየራሳ
ቸው ኮድ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ዋና ዋና ብሔረሰቦችን በቀላሉ ከዝርዝሩ ለማግኘት እንዲቻል አቀማመ
ጣቸው የተዘጋጀው የእንግሊዘኛውን ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት በማድረግ ነው፡፡

## ለ. የቅርንጫፍ ብሄረሰቦች ስምና ኮድ ዝርዝር፤

ይህ ዝርዝር የተዘጋጀው በዋና ዋና ብሄረሰቦች ሥምና ኮድ ዝርዝር ውስጥ በቅንፍ ውስጥ የቀረበ
-ትን ሞክሼ ስሞች ወይም ቅርንጫፍ ብሄረሰቦችን (ለምሳሌ፡-ኤርቦ፣ አልዴ፣ ሙርሴ፣) እንዲሁም
በዝርዝሩ ላይ ትንሽ ገባ ብለው የቀረቡትን ብሔረሰቦች (ለምሳሌ፡- ዶርዜ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ኮንታ፣ ኩ
ሎ፣ መሎ) በእንግሊዘኛ ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት በማቅረብ ነው፡፡ በዋና ዋና ብሄረሰብ ሥ
ምና ኮድ ዝርዝር ውስጥ ትንሽ ወጣ ብለው በእንግሊዝኛ ፊደል ቅደም ተከተል መሠረት የቀረቡ
ት ዋና ዋና ብሔረሰቦች ግን (ለምሳሌ፡- አርቦሬ፣ ወላይታ) በዚህኛው ዝርዝር ውስጥ በድጋሚ አ
ልቀረቡም፡፡

4. ከተጠቀሱት ዋና ዋና ብሄረሰቦችና ቅርንጫፍ ብሔረሰቦች ውጭ ካጋጠሙ የብሄረሰቡ ስም በዓምዱ
ተጽፎ የሚሰጠው ኮድ ግን ለሌሎች የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች የሚሰጥ ኮድ «90» ይሆናል፡፡

5. ከሁለት የተለያዩ ኢትዮጵያውያን ብሔረሰቦች ወይም ከኢትዮጵያዊያንና ከውጭ አገር ዜጎች የተወ
ለዱ ግለሰቦች ዕድሜያቸው 18 ዓመትና በላይ ከሆነ እነሱ የመረጡት የብሄረሰብ ስም በዓምዱ ይ
መዘገባል፡፡ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ከሆነ ግን ወላጅ ወይም አሳዳጊ የወሰነው የብሄረሰብ
ስም በዓምዱ እንዲፃፍ ያስፈልጋል፡፡

6. ከተለያዩ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ለተወለደና ከአባቱና ከእናቱ ብሄረሰብ አንዱን ለይቶ ለመናገር ለ
ማይፈልግ የሁለት ብሄረሰቦች ስም ተጽፎ ከተለያዩ ብሄረሰቦች የተወለዱ የሚለው ኮድ «91» ይ
ሞላል፡፡ ከእናታቸው ወይም ከአባታቸው ብሄረሰብ አንዱን መርጠው ለመናገር ፈቃደኛ ለሆኑ ግን
የመረጡት ብሄረሰብ ስም ተመዝግቦ የብሄረሰቡ ኮድ ይሞላላቸዋል፡፡

7. ኤርትራዊያን ለሆኑ ሁሉ በዓምዱ «ኤርትራዊ» ተብሎ ተመዝግቦ ኮድ «93» በካርድ ኮለሞቹ ይ
መዘገባል፡፡ እንዲሁም ለጅቡቲያውያን ኮድ «94» ይሰጣቸዋል፡፡ ለሱማሊያ አገር ዜጎች «ሶማሊያ
ዊ» ተብሎ ተመዝግቦ ኮድ «95» በካርድ ኮለሞቹ ይመዘገባል፡፡ ይህ ኮድ ግን የሚመዘገበው ኢት
ዮጵያውያን ላልሆኑ ብቻ እነደሆነ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን ለኢትዮጵያዊያን ሶማሌዎች የ
ሚመዘገበው «ሶማሌ» የሚል መልስ ሲሆን የሚሰጣቸውም ኮድ «68» ነው፡፡ ለኬንያውያን ኮድ
96 ለሱዳናዊያን ኮድ 97 የሚመዘገብ ሲሆን ለሌሎች የውጭ አገር ዜጎች ሁሉ የአገራቸው ስም
ተመዝግቦ ኮድ 98 ይሰጣቸዋል፡፡

**ዓምድ 19-20 <u>የትምህርት ሁኔታ</u>** (ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ የሚጠየቅ)

**ዓምድ 19 <u>ማንበብና መፃፍ ይችላሉ</u>?**

በዚህ ዓምድ ዕድሜኤአቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ማንበብና መፃፍ መቻላቸውን ይጠየቃሉ:: መልስ ሰጪው ማንበብና መፃፍ እችላለሁ (አዎን) ካሉ ኮድ «1» ይመዘገባል:: አንድ ግለሰብ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ አለው የሚባለው ቢያንስ በአንድ ቋንቋ አንብቦ መረዳትና እንዲሁም መፃፍ ሲችል ነው:: የራሳቸውን ስም ወይም ቁጥሮችን ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም:: እንዲሁም ሃይማኖት ነክ የሆኑና ቀደም ብለው በቃል የተጠኑ ዓረፍተ ነገሮች ብቻ መድገም የሚችሉ የማንበብና የመፃፍ ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም:: መልስ ሰጪው ማንበብና መፃፍ «አልችልም» ካሉ ኮድ «2» ይመዘገብና ወደ ዓምድ 21 ይታለፋል::

**ዓምድ 20 <u>የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ስንተኛ ነው?</u>**

ዕድሜያቸው 5 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ የቤተሰቡ አባላት (በዓምድ 19 ኮድ 1 ለተሞላላቸው) በመጀመሪያ የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል ተጠይቆ መልሱ በዓምዱ ውስጥ ተመዝግቦ በካርድ ኮለሞቹ ከታች በተገለፀው መሠረት ተስማሚው ኮድ ይሞላል::

የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል ሲባል ግለሰቡ በሃገሪቱ ባለው የትምህርት ሥርዓት በመደበኛ ትምህርት ቤት፣ በዩኒቨርስቲ፣ በማሰልጠኛ ተቋምና በመሳሰሉት በመማር ላይ ያሉትን ወይም ከዚህ በፊት ተምረው ያጠናቀቁትን ከፍተኛ የትምህርት ክፍል የሚያመለክት ነው:: ከ1ኛ እስከ 11ኛ ክፍል ያሉትን ክፍሎች ማጠናቀቅ ማለት ለክፍሉ የተሰጠውን ፈተና ተፈትኖ ማለፍ ማለት ሲሆን ለ12ኛ ክፍል ግን ለብሔራዊ ፈተና ከተቀመጡ እንዳጠናቀቁ ይቆጠራል:: በዚህ መሰረት

**<u>የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል</u>**

| <u>ኮድ</u> | <u>በፊደል</u> | <u>የክፍል ደረጃ</u> |
|---|---|---|
| 01 = | አንደኛ | የአንደኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ፣ |
| 02 = | ሁለተኛ | የሁለተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ፣ |
| 03 = | ሶስተኛ | የሶስተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ፣ |
| 04 = | አራተኛ | የአራተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ፣ |
| 05 = | አምስተኛ | የአምስተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ፣ |
| 06 = | ስድስተኛ | የስድስተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፣ |
| 07 = | ሰባተኛ | የሰባተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፣ |
| 08 = | ስምንተኛ | የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፣ |
| 09 = | ዘጠነኛ | የዘጠነኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፣ |
| 10 = | አሥረኛ | የአስረኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፣ |
| 11 = | አሥራ አንደኛ | የአስራ አንደኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፣ |
| 12 = | አሥራ ሁለተኛ | የአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ፣ |

20 =

<u>ሰርተፊኬት፣</u> ከ12ኛ ክፍል በላይ ከመደበኛ ትምህርት ቤቶች ወይም በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ከታወቁ ተቋሞች (ኮሌጆች) ዩኒቨርስቲዎች ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ወይም ዲግሪ ለማስገኘት ባልታቀደ ፕሮግራም ቢያንስ የአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ትምህርት ለፈፀሙ ሁሉ ፕሮግራሙን አጠናቀው ሰርተፊኬት የተቀበሉ ሁሉ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ:: ከታች ከሀ-ጀ ከተዘረዘሩት ውጭ የተከታተሉት ትምህርት ወይም ያገኙት ሰርተፊኬት በዚህ ዓምድ በኮድ 20 ይመዘገባል::

21 =

<u>ዲፕሎም ያልጨረሰ፣</u> ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ከታወቀ ተቋም ወይም ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ለማስገኘት በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም የአንድ ዓመትና ከዚያ በላይ ትምህርት ያጠናቀቁ ግን ዲፕሎም ላላገኙ ሁሉ::

22 =

<u>ዲግሪ ያልጨረሰ፣</u> ከአሥራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ የመጀመሪያ ዲግሪ (ቢ.ኤ፣ ቢ.አ

ሲ.ሲ) ያስገኛል ተብሎ በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርስቲ (በሚቀጥለው ገጽ ከ «ሀ-ጀ» በተዘረዘሩት ውስጥ) የአንድ ዓመት ወይም የበለጠ ትምህርት ላጠናቀቁ ግን ዲግሪ ላላገኙ ሁሉ፣

23 =

**ዲፕሎም፣** በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ተቋም (ኮሌጅ) ዩኒቨርስቲ ወይም ተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ከታች ከ«ሀ-ደ» በተዘረዘሩት ውስጥ) ዲፕሎም ላገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ላላቸው ሁሉ፣

24 = **ዲግሪ፣**

የመጀመሪያ ዲግሪ (የሕክምና ዲግሪ፣ ቢ.ኤ፣ ቢ.ኤስ.ሲ፣ ቢ.ኢ.ዲ፣ ኤል.ኤል.ቢ) ላገኙና ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ላላቸው ሁሉ።

25 =

**ከዲግሪ በላይ፣** በዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪ ካገኙ በኋላ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም የማስተርስ ወይም የዶክትሬት ዲግሪ ላገኙ በድህረ ምረቃ ፕሮግራም አጠናቀው ቢያንስ የአንድ ዓመት ትምህርት ላጠናቀቁ፣

95 =

**መሠረተ ትምህርት፣** በመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ማንበብና መፃፍ ችለው በሌላ ቦታ ትምህርት ላልቀጠሉ ሁሉ፣

96 =

**መደበኛ ያልሆኑ፣** በቄስ፣ በቁርዓንና በመሳሰሉት ትምህርት ቤቶች በመማር ማንበብና መፃፍ የሚችሉ (ትምህርታቸው ወደ መደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሊተረጎም የማይችል)። እንደዚሁም በራሳቸው ጥረት የግለሰቦችን ዕርዳታ እየጠየቁ ማንበብና መፃፍ የቻሉ ምንም እንኳን በዓምድ 19 ኮድ 1 ቢሞላላቸውም እዚህ ይመደባሉ። በተጨማሪም በመደበኛ ት/ቤት አንደኛ ክፍል ያላጠናቀቁ ሆነው ወይም በመዋዕለ ህፃናት እየተማሩ ያሉ ነገር ግን ማንበብና መፃፍ የሚችሉ በዚህ ክፍል ይካተታሉ። እንዲሁም የመሠረተ ትምህርት በመከታተል ላይ የሚገኙ (ፕሮግራሙን ያላጠናቀቁ) ሆነው ማንበብና መፃፍ የሚችሉትንም ያጠቃልላል።

**ማስታወሻ፣** በሀገሪቱ የታወቁ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም (ኮሌጅ/ ዩኒቨርስቲ) የሚባሉት፡-

ሀ/ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ (ሳይንስ ፋክልቲ፣ የቋንቋ ጥናት ኢንስቲተዩት፣ ሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ፥ ቴክኖሎጂ ፋክልቲ፣ ፋርማሲ፣ የትምህርት ፋክልቲ፣ ሕግ ፋክልቲ፡የከብት ሕክምና ፋኩልቲ፣ የሕክምና ፋክልቲ፣ ላይብረሪ ሳይንስ፣ ድህረ ምረቃ፣ ...ወዘተ)
ለ/ ጎንደር ሕክምና ኮሌጅ፣
ሐ/ ባህር ዳር መምህራን ማሠልጠኛ ኮሌጅ፣
መ/ አዋሳ እርሻ ኮሌጅ
ሠ/ አለማያ ዩኒቨርስቲ (የእርሻ ፋክልቲ፣ የደን ጥናት ፋኩልቲ እና የግብርና ሳይንስ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም)
ረ/ አምቦ እርሻ ኮሌጅ
ሰ/ አዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ
ሸ/ ጅማ እርሻ ኮሌጅ
ቀ/ ባህር ዳር ፖሊቴክኒክ ኢንስቲትዩት፣
በ/ ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ፣
ተ/ ወንዶ ገነት ደን ጥናት ኮሌጅ፣
ቸ/ አርባ ምንጭ ውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስትትዩት፣
ኀ/ መቀሌ ቢዝነስ ኮሌጅ፣
ነ/ ኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ፣
ኘ/ ጅማ ጤና ሳይንስ ኢንስትቲዩት፣
አ/ ናዝሬት ቴክኒክ ኮሌጅ፣
ወ/ መቀሌ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ፣
ገ/ ዲላ ጤናና ትምህርት ኮሌጅ፣
ደ/ ጎንደር መምህራን ኮሌጅ?
ጀ/ ዩኒቲ ኮሌጅ?

ከነዚህ ተቋሞች ውጭ የሚሰጡ ዲፕሎማዎች (የምስክር ወረቀቶች) በኮድ «20» ይመዘገባሉ:: (ለምሳሌ፡- የካቲት 66 ፖለቲካ ት/ቤት፣ ተግባረዕድ፣ መምህራን ማሰልጠኛ ተቋም፣ እንጦጦ አጠቃላይ ት/ቤት ... ወዘተ)

## ዓምድ 21-22 የስልጠና ሁኔታ (ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆኑ ብቻ)፡-

እነዚህ ዓምዶች የሚመለከቱት ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላትን ብቻ ሲሆን በዓምዶቹም አማካይነት በጥናቱ ወቅት የሙያ (ቴክኒካል) ስልጠና አግኝተው/ወስደው ያውቁ እንደሆነ በዓምድ 21 ተጠይቀው ስልጠና ወስደው የሚያውቁ ከሆነ በዓምድ 22 የሰለጠኑበት የሙያ አይነት ተ ጠይቆ ይሞላል:: ዕድሜያቸው 10 ዓመት ላልሞላቸው የቤተሰብ አባላት በዓምዶቹ ላይ «-» ይደረጋል::

## ዓምድ 21 የሙያ ስልጠና ወስደው ያውቃሉ?

-

በዚህ ዓምድ ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ የሆናቸው የቤተሰብ አባላት በሙሉ የሙያ (የቴክኒ ክ) ስልጠና ወስደው አጠናቀው እንደሆነ ይጠየቃሉ::

- ለዚህ ጥናት ስልጠና ማለት በአሰልጣኙ ድርጅት ስልጠናውን ለመስጠት ጊዜ ተመድቦለት በክፍል ውስጥ ወይም ከክፍል ውጭ /PRACTICE/ ወይም ሁለቱን በማጣመር የተሰጠ እንደሆነ ነው:: በዚህ ጥናት ስልጠና ሲባል መነሻ የመደበኛ ትምህርት ደረጃ የማይጠይቁትን ሁሉ ያጠቃልላል:: ማለትም አንድ ሰው ትምህርት ሳይኖረውም በአንድ ሙያ ቢሰለጥን በሙያ እንደሰለጠነ ይቆጠራል:: የስልጠናው መስክም በማናቸውም ትምህርት በሚጠይቅ ወይም በማይጠይቅ የሙያ መ ስክ ሊሆን ይችላል:: ለምሳሌ፡- አናፂ፣ ሽክላ ሥራ፣ ሕክምና፣ ምህንድስና ...ወዘተ:: ለጥያቄው አ ዎን ለመለሱ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 ይሞላል:: የለም ለመለሱ ኮድ 2 ተሞልቶ ወደ ዓምድ 23 ይታለፋል::

ስልጠናው የምስክር ወረቀት ያስገኘ መሆን ስላለበት ስልጠና ለመውሰድ ጀምረው ስልጠናውን ያቋረጡ ወይም ለምስክር ወረቀት የሚያበቃ ውጤት ለማግኘታቸው ማረጋገጫ ላላገኙ ስልጠና እንዳልወሰዱ ተቆጥሮ የሚሞላላቸው ኮድ 2 ነው::

ይህ ዓምድ ሲሞላ ከታች የተመለከቱትን ነጥቦች መረዳት ያስፈልጋል::

- እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ የቀለም ትምህርት የተማሩ በሙያ እንደሰለጠኑ አይቆጠርም፣
- በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሙያ ትምህርት ተምረው ያጠናቀቁና የምስክር ወረቀት ያገ ኙ በሙያ እንደሰለጠኑ ይቆጠራል፣
- የምስክር ወረቀት እስካገኙ ድረስ በመንግስታዊም ሆነ በግል ድርጅቶች የሚሰጡ ማናቸውም የአ ጭርም ሆነ የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች እንደሙያ ስልጠና ይቆጠራሉ::

**ማሳሰቢያ፡** በኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ የሚሠጡ የአጠቃላይ ትምህርት በመሆናቸው እንደ ሙያ ስልጠና አ ይወሰድም:: ነገር ግን በነዚሁ ተቋማት የሚገኝ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎች እንደ ሙያ ስልጠና ይቆጠ ራሉ::

## ዓምድ 22 የሰለጠኑበት የሙያ /የቴክኒክ ስልጠና ዓይነት ምንድነው?

በዓምድ 21 ላይ ስልጠና እንዳላቸው የገለፁ /ኮድ 1 የተሞላላቸው/ ሰዎች በዚህ ዓምድ የሰለጠኑበት ዋ ነኛ የሙያ (የቴክኒክ) ዓይነት ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል:: በካርድ ኮለሞቹም ከታች ከ ተዘረዘሩት ውስጥ ተገቢው /ተቀራራቢው/ ኮድ ይሞላል:: ከአንድ በላይ ስልጠና ለወሰዱ ረጅም ጊዜ የ ወሰደውና ከፍተኛው የስልጠና ዓይነት ይመዘገብላቸዋል::

01= ሸክላ ስራ
02= ሽመና
03= እንጨት ሥራ (የአናጢነት ስልጠናን ይጨምራል)
04= ኤሌክትሪክ ሥራ
05= ብረታ ብረት
06= መካኒክ (የመኪና፣ የሞተር ሳይክል፣ የአውሮፕላን ጥገናን ጨምራል)
07= ግንበኝነት
08= ታይፕ
09= ልብስ ስፌት
10= ሹፌርነት
11= የልማት ተጠሪ /DA/
12= ልምድ አዋላጅ

13=
ኮምፒውተር ሳይንስ (ፕሮግራመር)
14= ኮምፒውተር አጠቃቀም
15= በግብርና አነስተኛ ስልጠና ሙያ
(ከአጋርፋ፣ አርዳይታ ባኮ፣ ወዘተ)
16= ሆቴልና ቱሪዝም
17= ፖሊስ
18=
መምህርነት (ከመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ፣ከቴክኒክ ማሰልጠኛ ኮሌጅ፣ ከመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም፣)
19= ውትድርና
20= ሌላ (ይገለጽ)

## ዓምድ 23 <u>የጋብቻ ሁኔታ</u>፡-

ይህ ዓምድ ዕድሜያቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ሁሉ መሞላት አለበት። ጋብቻ ማለት አንድ ወንድና ሴት በሕጋዊ፣ በሃይማኖታዊ ወይም በባሕላዊ መንገድ የጋብቻ ስነ ስርዓት ፈፅመው እንደ ባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ነው።

የጋብቻውን ሁኔታ ለማመልከት ከዚህ በታች የተመለከቱት የጋብቻ ዓይነቶችና ኮዶቻቸው ተሰጥተዋል።

### 1= አግብተው የማያውቁ

ፈፅሞ ያላገባ ወይም ያላገባች እስከ ጥናቱ ቀን ድረስ አግብቶ ወይም አግብታ የማታውቅ ወይም የማያውቅ፣

### 2 = ባለትዳር

በጥናቱ ቀን በጋብቻ ላይ ያለ ወይም ያለች፣

### 3 = የተፋቱ

ከጥናቱ ቀን በፊት አግብቶ ወይም አግብታ የነበረ ነገር ግን ከጥናቱ ቀን በፊት በሕጋዊ ወይም በባሕላዊ መንገድ የተፋታ ወይም የተፋታች፣

### 4 = የሞቱባቸው

ባል የሞተባት ወይም ሚስት የሞተችበት ሆነው ከሞተባቸው በኋላ እስከ ጥናቱ ቀን ድረስ ያላገቡ፣

### 5 = የተለያዩ

ባልና ሚሰት ባለመግባባት ምክንያት ጉዳያቸው በሽማግሌዎች በመታየት ላይ ያለ ወይም ፍርድ ቤት በቀጠሮ ላይ የሚገኙ፣

# ምዕራፍ 3

## በቅጽ 1 የክፍል 3 እና 4 አሞላል መምሪያ

በምዕራፍ 2 የቅጽ 1 ክፍል 1 እና 2 አሞላል መመሪያ ተብራርቷል። በዚህ ምዕራፍ የቅጽ 1 ክፍል 3 እና ክፍል 4 አሞላል መመሪያ ይቀርባል። በክፍል 3 እድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ የሆኑ የቤተሰብ አ ባላት ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሥምሪት መረጃ የሚጠይቅ ሲሆን በክፍል 4 ደግሞ ዕድሜአቸው 10 ዓ መትና በላይ የሆኑ የቤተሰብ አባላት የአለፉት 12 ወራት የሥራ ስምሪት መረጃ የሚሰበሰብበት ነው።

**ክፍል 3 ያለፉት 7 ቀናት የሥራ ሁኔታ** (ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ብቻ)

ማስታወሻ፡- የዚህ ክፍል መረጃዎች ከመሞላታቸው አስቀድሞ በመጠይቁ ራስጌ ላይ በተዘጋጀው ሥፍራ የተመረጠውን ቤተሰብ አድራሻና የአካባቢ መለያ ከገፅ 1 ክፍል 1 ማወራረስ ያስፈልጋል።

በዚህ ክፍል የሚሰበሰቡ መረጃዎች ከጥናቱ ቀን በፊት በነበሩት 7 ቀናት ውስጥ ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ በሆናቸው የቤተሰቡ አባላት የተከናወኑ የኢኮኖሚ ተግባሮችን የሚመለከቱ ይሆናሉ።

ዓምድ 13፣ 12 እና 16፡- ዓምድ 13 "ሙሉ ስም"፣ ዓምድ 12 "የመስመር ቁጥር" እና ዓምድ 16 ዕድሜ የሚለ ው ከገፅ 1 ዓምድ 13፣ ዓምድ 12 እና ዓምድ 16 ሁሉም የቤተሰብ አባላት ቅደም ተከተላቸውን እና የመስመር ቁጥራቸውን እንደጠበቁ የሚዛወሩበት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በሚቀጥሉት የመጠይቁ ገጸ ችም ዓምድ 13፣ ዓምድ 12 እና ዓምድ 16 ላይ የሁሉም የቤተሰብ አባላት ስም፣ የመስመር ቁጥርና ዕ ድሜ ከገጽ 1 ዓምድ 13፣ ዓምድ 12 እና ዓምድ 16 ይገለበጣል።

በክፍል 3 የሚቀርቡት ጥያቄዎች ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ የሆናቸውን የቤተሰብ አባላት ብቻ ስለ ሚመለከቱ ዕድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት ከስምና መስመር ቁጥር በስተቀር ከዓምድ 24-46 ያሉት ዓምዶች በ "__" ይታለፋሉ። በዓምድ 16 ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ የሆ ናቸውን የቤተሰብ አባላት በመለየት ሁሉም በዚህ ክፍል ሳይጠይቁ እንዳይዘለሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። በተመሣሣይ ሁኔታ ከዓምድ 47-48 ዕድሜአቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው፣ እንዲሁም ከዓምድ 49-51 ዕድሜአቸው 18 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት የሚሞሉ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 24 **ለመረጃ ሰብሳቢ ፡- ለመልስ ሰጭዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ አቅርበህ/ሽ ቢያንስ በአንዱ የሥራ ዓይነት ከተሰማሩ በካርድ ኮለሙ ኮድ «1» ይሞላል። በአንፃሩም በአንዱም ሥራ እንኳን ካልተሰማሩ በካርድ ኮለሙ ኮድ «2» ይሞላል።**

በዚህ ዓምድ እያንዳንዱ ዕድሜው 5 ዓመትና በላይ የሆነ የቤተሰቡ አባል ከጥናቱ ቀን በፊት ባለት 7 ቀ ናት ውስጥ በቅጥር/በክፍያ ወይም ነግዶ ለማትረፍ ወይም በግብርና ወይም በሌላ የማምረት ተግባር ወ ይም አገልግሎት በመስጠት ተግባር ተሰማርቶ እንደሆነ ይጠየቃል። በዚህ ጥያቄ ለማወቅ የተፈለገው አ ባሉ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ተግባር ላይ መሠማራት አለመሠማራታቸውን ነው።

የሥራ ሁኔታ መረጃን ለመሙላት ቀጥሎ የተሰጠውን የምርታማ ሥራን አጠቃላይ ትርጉምና በዝርዝር የተሰጡትን የሥራ ዘርፎች ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል።

ምርታማ ሥራ ማለት የሥራውን ውጤት የሆነውን ሸቀጣ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት በከፊል ወይም በጠ ቅላላ በገንዘብም ሆነ በዓይነት (በዕቃ) በመለወጥ ገቢ ለማግኘት ለገበያ ለማቅረብ ሲቻል ነው። በራስ፣ በ ቤተሰብ ይዞታ፣ በመንግሥታዊ፣ በሕዝባዊ ወይም በግለሰብ ቤት ወይም ድርጅት በቀን፣ በሳምንት፣ በ ወር ወይም በሥራት መጠን ክፍያ ወይም ገቢ ለማግኘት ሥራ ከሠሩ እንደ ምርታማ ሥራ ይቆጠራል። በሌላ አገላለጽ ምርታማ ሥራ በግል ወይም በመንግስት ተቀጥሮ ወይም የግል ሥራ መስራት፣ መነገድ፣ የግብርና ሥራ፣ ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎችን ማምረት በቤተሰብ ድርጅት/እርሻ ውስጥ ያለክፍያ መስራ ት በምርታማ ሥራነት ይቆጠራሉ ማለት ነው።

በምርታማ ሥራ ውስጥ የሚጠቃለሉ የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባራት እንደሚከተው ተዘርዝረዋል።

ሀ. ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎችን ማምረት ለምሳሌ፡- የፋብሪካ ውጤቶች፣ ሸክላ ማምረት ... ወዘተ ወይ ም በክፍያ አገልግሎቶችን ማቅረብ ለምሳሌ፡- ፀጉር ማስተካከል፣ የሽመና ሥራ፣ የጠላና የአረቄ ንግድ፣ ድለላ ... ወዘተ

ለ. ለመንግሥት፥ ለሌላ ድርጅት ወይም ለግለሰብ በክፍያ የሚሠሩ ሥራዎች (ለምሳሌ:- ሐኪም፥ መም ህር፥ ተቀጣሪ ገበሬ፥ እረኛ፥ .. ወዘተ)፥ በተጨማሪ ያለክፍያ ለመረዳዳት የሚሠሩ (ለምሳሌ:- ም ግብ ለሥራ፥ የደቦ ሥራ፥ ... ወዘተ)

ሐ. ለራስ የምግብ ፍጆታ ወይም ለሽያጭ ወይም ቋሚ ንብረት ለማከማቸት ሲባል የማምረት ተግባር፣ እነርሱም:-

1. ለራስ መሠረታዊ ፍላጎት ፍጆታ ሲባል የምርት ቀዳሚ ውጤቶችን (Primery Products) የማምረት ተግባር

ለምሳሌ:- ሰብሎች/ጥራጥሬ፥ አትክልትና ፍራፍሬ፥ ጥጥ፥ እና የመሣሰሉትን የግብርና ቀዳሚ የም ርት ውጤቶችን (እንደ ኑግ፣ በቆሎ፣ ጥሮ፣ ወይንና ተመሣሣዮችን) የማምረት ወይም ከመስክ መሠብ ሰብ፣ ወተት፣ እንቁላልና የመሣሰሉትን የከብት/ዶሮ እርባታ ውጤቶችን ማምረት፣ እንስሳትን ወፎች ን ማደን፣ ዓሣና የመሣሰሉትን ማጥመድ፣ ከመስክ ለማገዶነት ወይንም ለሌሎች ተግባራት የሚውል እንጨት መቁረጥ፣ ለሽመና ሥራ ለማስሪያነት/ለስፌት የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎችን ከመስክ መሠብሰ ብ፣ ከሠል ማክሰል፣ ጨውና ሌሎች ማዕድናትን ማውጣት፣ የኖራ አፈር መቆፈር፣ ለቤት ቁሳቁስ መ ስሪያነትና ለተለያዩ ጥቅም የሚውል የአፈር ዓይነቶችን መቆፈር፣ ድንጋይና አሸዋ ከመስክ ቆፍሮ ወ ይም ፈልፍሎ ማውጣት ወይም መሠብሰብ፣ እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል::

2. ከላይ በተራ ቁጥር 1 ያመረቱትን ምርት ለራስ ፍጆታ በማሰብ ወደ ሌላ ዓይነት ምርት የመለወጥ ተ ግባር፥ ለምሳሌ:- ፈትል መፍተል፣ ቅቤ/አይብ ማውጣት፣ በቆሎ መፈልፈል፣ እህል መፍጨት፣ የቤት ቁሳቁስ እንደ ወንበር፣ ጠረጴዛ ማዘጋጀት፣ የዕቃ መያዣዎችን መስራት ወዘተ...:: ያመረቱትን ቀዳ ሚ ምርት ለራስ ፍጆታ በማሰብ ወደ ሌላ ዓይነት ምርት መቀየር ምርታማ ተግባር ቢሆንም ይህን የተቀየረውን ምርት ለራስ ፍጆታ በማለት እንደገና ወደ ሌላ ዓይነት ምርት መቀየር ምርታማ አይደ ለም:: በዚህ ዓይነት በቤተሰቡ አባላት የተመረተን ጤፍ ለራስ ፍጆታ በማለት ፈጭቶ ወደ ዱቄት መቀየር እንደምርታማ ተግባር ይቆጠራል:: ነገር ግን ይህን የተፈጨውን ዱቄት ለራስ ፍጆታ በማለ ት ወደ እንጀራ መቀየር ምርታማ ተግባር አይደለም:: በአንጻሩም ለራስ ፍጆታ ለማዋል በሌላ ከቤ ተሰቡ አባል ውጪ በሆነ ሰው የተመረተን ምርት ለምሳሌ:- ጤፍ ወደ ዱቄትም ሆነ እንጀራ ቢቀየ ር እንደምርታማ ተግባር አይቆጠርም::

3. ለራስ የምግብ ፍጆታ የሚመረቱ ዕቃዎችና ግልጋሎቶች ለሽያጭም ጭምር በቤተሰቡ ሲመረቱ፥ ለም ሳሌ:- ጠላ ጠምቀው (ከፊሉን ቢጠጡም) የሚሸጡ ከሆነ እንደምርታማ ስራ ይቆጠራል::

4. ቋሚ ንብረቶችን (ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል ግልጋሎት መስጠት የሚችሉ) ለራስ ጥቅም ሲባል ማ ምረት፥ ለምሳሌ የራስን ግቢ ወይም አካባቢ ግንባታ፥ የእርሻ ውጤት ማከማቻ ጎተራ፣ መጋዘኖችንና የእርሻ መሣሪያዎችን መሥራት፥ ሌሎች መሣሪያዎችን ማምረት ናቸው::

ማሳሰቢያ:- የሚከተሉትን ተግባራት ሙሉ በሙሉ ለራስ መሠረታዊ ፍጆታ እንዲውሉ በማሰብ ማ ከናወን እነደ ምርታማ ተግባር አይቆጠርም:- ለምሣሌ፣

- ውሃ መቅዳት ወይም ቀድቶ ተሸክሞ ወደ ቤት ማድረስ
- ከጫካ/ከሜዳ እንጨት/ኩበት መልቀም
- በቤተሰቡ ካልተመረተ ወይም በግዥ ከተገኘ ጥጥ ፈትል መፍተል

ከላይ የተሠጠው የምርታማ ስራ ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት በማከናወን ላይ የ ተሠማሩ ሰዎች ሥራቸው ምርታማ ካልሆኑ ሥራዎች ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው::

ሀ. ያለ ክፍያ ለቤተሰቡ ግልጋሎት ወይም ፍጆታ የቤት ውስጥ ስራ ለምሳሌ ልጆችን ማስተማር፥ ማሣደ ግ፥ ቤተሰቡ የሚመገበውን ምግብ ማዘጋጀት፣ የቤተሰቡን አጥርና ቤት ... ወዘተ በአነስተኛ ደረጃ የ መጠገን ወይም የማደስ ተግባርን ማከናወን፣ በበጎ ፈቃደኝነት (Volentery) በተለያዩ ማህበራት (አለ ም አቀፍ፣ አገር አቀፍ፣ እንዲሁም የአካባቢ የበጎ አድራጎት ማህበራት) ውስጥ የተለያዩ አገልግሎቶ ችን የመስጠት ተግባር::

ለ. ገቢ ቢገኝበትም
- በልመና ተግባር የሚተዳደሩ
- በሴተኛ አዳሪነት (መጠጥ ደርድረውም ሆነ ሳይደረድሩ) የሚተዳደሩ
- ቤት በማከራየት ብቻ ወይም በጡረታ ብቻ የሚተዳደሩ

ሐ. በቅጥርም ሆነ ያለቅጥር

- ሴተኛ አዳሪነትን የሚከለክል ህግ በሌላቸው ቡና ቤቶችና ሆቴሎች በአሻሻጭነት (አስተናጋጅነት) የሚሠሩ በተጨማሪነት በሴተኛ አዳሪነት የተሰማሩ ከሆነ

መ. ሌሎች

- በተለያዩ ቢሮዎች፥ በጋራዦች፥... ወዘተ እና በሌሎች የሥራ መስኮች በተለማማጅነት የሚገኙ በ ልምምዳቸው ወቅት ከሚለማመዱበት ቢሮ፥ ጋራዥ፥ ... ወዘተ እና ከሥራ መስክ ጋር በተያያዙ በሥራው ምንም ዓይነት ተሳትፎ ሳያደርጉ የሚለማመዱትን (<u>ለምሳሌ</u>፡- ልምምዳቸውን በማየት ብቻ የሚያከናውኑ) በልምምዳቸው ወቅት በምርታማ ተግባር እንደተሠማሩ አይቆጠሩም።

በዚህ ዓምድ ስር ሰዎች ሊሰማሩ የሚችሉባቸው 8 ዋና ዋና የሥራ ዘርፎች የተዘረዘሩ ሲሆን እያንዳንዱ ዕድሜው 5 ዓመትና በላይ የሆነ የቤተሰብ አባል በነኚህ የሥራ ዘርፎች ተሰማርቶ እንደሆነ ለማወቅ ጥ ያቄዎች ከመጀመሪያው ጀምሮ አንድ በአንድ ይቀርቡለታል። ከተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች በአንዱ እንኳ ን ከተሳተፈ በምርታማ ተግባር እንደተሰማራ ተቆጥሮ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 ይሞላል። ነገር ግን ከተዘ ረዘሩት የሥራ ዘርፎች ውስጥ በአንዱም እንኳ አልተሰማራሁም ካለ ኮድ 2 ይሞላል። በመጠይቁ ላይ የ ሠፈረው ጥያቄ እንዳለ ለመልስ ሰጪው መነበብ ይኖርበታል። ቀጥሎ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ማብራሪያ ተሰ ጥቷል።

### <u>በመንግሥት ወይም መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ተቀጥረው ሠርተዋል?</u>

ጥያቄው እንደሚያመለክተው መንግስት በሚያስተዳድራቸው መ/ቤቶች/ድርጅቶች፣ ወይም የግል ( መንግስታዊ ያልሆኑ) አምራች ወይም አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ሰዎች ን ያጠቃልላል። የግል ድርጅት ተቀጣሪዎች ሲባል በግለሰብ ቤት በቤት ሠራተኝነት የተቀጠሩትን፣ በአነስተኛ የንግድ ወይም የአገልግሎት ሰጪ ድርጅት <u>ለምሳሌ</u>፡- ሱቅ ውስጥ አሻሻጭ እንዲሁም በ ትላልቅ ድርጅቶች (ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች) ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩትን ይጨምራል። ለት ርፍ በማይሰሩ መንግሥታዊ ባልሆኑ ግብረሰናይ ድርጅቶች /NGO/ ውስጥ የሚሰሩትን በሕዝባዊ ማ ህበራት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ፣ በሕዝባዊ ማህበራት በክፍያ የሚያገለግሉ ተመራጮች ፣ ከቀበሌ እስከ ማዕከል ባሉት የአስተዳደር እርከኖች ውስጥ በክፊያ የሚሠሩ ተመራጮች ... ወዘተ ተቀጥረ ው እንደሚሠሩ እንቆጥራቸዋለን።

### <u>በንግድ ሥራ ተሰማርተው ነበር?</u>

ንግድ ማለት ትርፍ ለማግኘት ዕቃዎችን ገዝቶ በጅምላም ይሁን በችርቻሮ መሸጥ ነው። የገዙትን ዕቃ ወደ ሌላ መልክ ቀይሮም ይሁን ሳይቀይሩ መሸጥ ንግድ ይባላል። ይህም ከትናንሽ ንግድ ማለ ትም ከቆሎ ሻጭነት እስከ ትላልቅ ንግድ ያለውን ያካትታል። የመነገጃ ቦታውም ጉልት፣ ገበያ ቦ ታ፣ ወይም በየቦታው እየተዟዟሩ ወይም በተወሰነ ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀምጦ ሊሆን ይችላል።

### <u>በቅጥርም ሆነ በግል/በራስ ድርጅት አገልግሎት በመስጠት ተግባር ተሰማርተው ነበር?</u>

በክፍያ የሚሠሩ ሥራዎችን ለሌሎች ሰዎች መሥራት /ማገልገል አገልግሎት መስጠት ይባላል። በ ምሳሌነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ሊስትሮ፣ ፀጉር ማስተካከል፣ ልብስ መስፋት፣ ድለላ፣ በክፍያ ማስተማር ፣ የጥገና አገልግሎት፣ የፅዳት አገልግሎት፣ ጉዳይ ማስፈፀም፣ የታክሲ ወይም የትራንስፖርት አገልግለ ት፣ የሆቴል አገልግሎት መስጠት ናቸው።

### <u>በግብርና ስራ ተሰማርተው ነበር?</u>

የግብርና ሥራ እርሻ፣ ከብት እርባታ፣ የአሳማ እርባታ፣ የዶሮ እርባታን የንብ እርባታን ... ወ ዘተ ያጠቃልላል። ያመረቱትን ቀዳሚ ምርት /እህል፣ ጣውላ የመሳሰሉት/ ለሽያጭም ሆነ ለራስ ፍ ጆታ ወደ ሌላ ዓይነት ምርት መቀየር በዚህ ስር ይጠቃለላል። የእርሻ ሥራ የሚባለው ከዝግጅት ጀምሮ ምርቱ ከደረሰ በኋላ ሰብስቦ እስከ ማከማቸት ያለው ተግባር ነው። ብቻቸውን ወይም ከቤተሰ ብ አባላት ጋር ወይም ለሌላ ሰው /ድርጅት/ ተቀጥረው ወይም በምግብ ለሥራ ፕሮግራም በግብር ና ስራ ላይ የተሰማሩ ሁሉ ለዚህ ጥያቄ አዎን የሚል መልስ እንዲመልሱ ይጠበቃል።

### <u>ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎችን አምርተው ነበር?</u>

ራሳቸው /ቤተሰቡ/ ያመረቱትን ምርት በመጠቀምም ሆነ በሌላ ሰው የተመረቱ ምርቶችን በመጠቀ ም ለገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ ተግባር የተሰማሩ፣ ከፊሉን ተጠቅመው ቀሪውን በመሸጥ ተግባር የ

ተሠማሩ ... ወዘተ ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎች እንዳመረቱ ይቆጠራል፡፡ <u>ለምሳሌ፡</u>- አሸዋ፣ ደንጋይ፣
ጣውላ ማምረት ለሽያጭ እንጀራ፣ ጠላ፣ አረቄ፣ ወንበር የመሳሰሉ ቁሳቁሶችን መስራት፣ ጫማ መስራ
ት፣ ጥጥ መፍተል፣ እንጨት ለቅሞ መሸጥ፡፡ ነገር ግን በሌላ ሰው የተመረተን ምርት ገዝቶ ለራስ
ፍጆታ በማሰብ ወደ ሌላ መልክ በመቀየር መስራት እንደ ምርታማ ስራ አይቆጠርም፡፡ ሆኖም የተመ
ረተው ለሽያጭ ከቀረበ ምርታማ ተግባር ነው፡፡

<u>ለቤተሰቡ ቋሚ ንብረት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ሰርተው ነበር?</u>

ቋሚ ንብረት ማለት ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል ግልጋሎት መሰጠት የሚችሉ ግንባታዎችን ይመለ
ከታል፡፡ <u>ለምሳሌ፡</u>- አጥር፣ ቤት መስራት፣ ለዚሁ መሥሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን መሰብሰብ፣ ማዘጋጀት
ና መሥራት፣ የእርሻ መሣሪያዎች መሥራት፣ እንዲሁም ሌሎች መሣሪያዎችን መሥራትን ያጠቃልላ
ል፡፡

<u>ያለክፍያ ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር?</u>

በቤተሰባቸው ድርጅት ማለትም የንግድ፣ የአገልግሎት ሰጪ ወይም እርሻ ውስጥ ክፍያ ሳያገኙ የሠ
ሩ ናቸው፡፡ የቤት ውስጥ ሥራ እንደምርታማ ሥራ ስለማይቆጠር ለቤተሰባቸው የቤት ውስጥ አገል
ግሎት የሰጡ በምርታማ ሥራ ከተሳተፉት ተለይተው መታየት አለባቸው፡፡ ያለክፍያ ከቤተሰባቸው
ጋር በምርታማ ተግባር ሲሳተፉ የነበሩ ነገር ግን በጥናቱ ሳምንት ሳይሠሩ የቀሩ ሥራ እንዳላቸው አ
ይቆጠሩም፡፡

<u>ከላይ ከተጠቀሱት ውጪ ሌላ ሥራ ሠርተዋል ለምሳሌ በተለማማጅነት?</u>

በጥናቱ ወቅት ከላይ ከተዘረዘሩት የምርታማ ሥራ ዘርፎች ውጪ ሌላ ስራ እየሠሩ ያሉም በዚህ ዓ
ምድ ኮድ 1 ይሞላላቸዋል፤ <u>ለምሳሌ</u> በቤት ሠራተኝነት፤ ሥራ በመለማመድ ላይ የሚገኙ ... ወዘተ፡፡
ሥራ ተለማማጅ ሰዎች በተለማማጅነት በሚሰሩበት ወቅት የተወሰነ ክፍያ ሊኖራቸውም ላይኖራ
ቸውም ይችላል እንዲያውም እየከፈሉ የሚሠሩም ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ በተለማማጅነት ገብተው ነ
ገር ግን በሥራው ሂደት ላይ ምንም ተሳትፎ (አስተዋፅኦ) የሌላቸው ምርታማ ሥራ እንደሠሩ አይ
ቆጠርም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሥራ ባይኖራቸውም ለምሳሌ፡- የግል ሥራ ለመጀመር ከማሰብ አል
ፈው ቦታ በማፅዳት፣ ዕቃ በመግዛት ወይንም ንግድ ፈቃድ በማውጣት ላይ በጥናቱ ሳምንት ያሳለፉ
በምርታማ ሥራ ተግባር ላይ እንደተሠማሩ ይቆጠራል፡፡ እንዲሁም ከላይ ከተዘረዘሩት የሥራ ዘር
ፎች ውጭ ሌላ ምርታማ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሁሉ በዚህ ዓምድ ኮድ 1 ይሞላላቸዋል፡፡

ዓምድ 25 <u>ባለፉት 7 ቀናት በቤተሰብ ሥራ/ንግድ ወይም እርሻ ለቤተሰብ ገቢ ለማስገኘት ማንኛ
ውንም ዓይነት ሥራ ሠርተዋል?</u>

ይህ ዓምድ ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ሆኖ በዓምድ 24 ኮድ 2 ለተሞላላቸው የቤተሰብ አባላት ባለ
ፉት 7 ቀናት ምርታማ ስራ መስራት አለመስራታቸውን ለማጣራት የሚያገለግል ጥያቄ የሚቀርብበት ነ
ው፡፡ በአብዛኛው በቤተሰብ ድርጅት (ንግድ፣ እርሻ፣ ወዘተ...) ውስጥ በክፍያም ሆነ ያለክፍያ የሚሰ
ሩ ሰዎች እራሳቸውን ምርታማ ስራ እንደሰሩ ስለማይቆጥሩ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በቤተሰብ ሥራ/ንግ
ድ ወይም እርሻ ላይ ለቤተሰብ ገቢ በሚያስገኝ ማንኛውም አይነት ሥራ ሰርተው እንደሆነ ተጠይቆ ለሠ
ሩና «አዎን» ለመለሱ በዓምዱ «አዎን» ተጽፎ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 ይሞላል፡፡ ላልሰሩና («የለም» ለ
መለሱ) ደግሞ በዓምዱ «የለም» ተጽፎ በካርድ ኮለሙ ኮድ 2 ተሞልቶ ወደ ዓምድ 28 ይታለፋል፡፡

ዓምድ 26 <u>የምሣና የጉዞ ሰዓትን ሳይጨምር ባለፉት 7 ቀናት በሰሯቸው በሁሉም ስራዎችዎ ለስን
ት ሰዓት ሰርተዋል? (በሙሉ ሰዓት)</u>

በዚህ ዓምድ እያንዳንዱ በምርታማ ስራ ላይ ተሰማርቶ የነበረ ግለሰብ (በዓምድ 24 ወይም ዓምድ 25 ኮ
ድ 1 የተሞላለት) በጥናቱ ሳምንት ባሉት 7 ቀናት ውስጥ በድምሩ ስንት ሰዓት በምርታማ ሥራ እንደተ
ሠማሩ ይጠየቃል፡፡ ይህ ጥያቄ በተቻለ መጠን መረጃው ከሚመለከተው ሰው መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡ መ
ልሱ የሚሞላው በሳምንት በጠቅላላው የሠሩት የሥራ ሰዓት ቢሆንም መረጃ ሰጪዉ ለማስታወስ እንዲች
ል ጥያቄው የሚቀርበው ከቅርቡ ቀን ጀምሮ ተራ በተራ ወደኋ-
ላ ያሉትን እያንዳንዱን 7 ቀናት በመጥቀስ ይሆናል፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሞላው የሣምንቱ የሥራ
ሰዓት ድምር ቢሆንም ይህ ጥያቄ የሚቀርበው የቀኑን ስም እየጠሩ ግለሰቡ ከጠዋት እስከ ምሽት በምን
ተግባር ላይ እንደዋሉ በመጠየቅ መሆን ይገባዋል፡፡ <u>ለምሳሌ</u> መረጃ ሰብሳቢው መልስ ሰጪው ቤት ደር
ሶ የሚጠይቀው ረቡዕ ዕለት ከሆነ ከትላንት ማክሰኞ ጀምሮ ወደኋላ ላሉት ሰባት ቀናት እስከ ረቡዕ ድረ
ስ ተራ በተራ በየቀኑ በስራ ያሳለፉትን ሰዓት በመጠየቅና የሰባቱን ቀናት በመደመር መረጃውን ይሞላል፡

፡ የበዓልን፣ የስብሰባንና የገበያ ቀናትን በስም መጥራት በዛን ሰሞን የነበሩ ሁኔታዎችን በቶሎ እንዲያስታውሱ ይረዳል፡፡ ለአንድ የቤተሰብ አባል የተሞላ መረጃ ለሌላኛው በማነፃፀሪያነት ሊጠቅም ስለሚችል መረጃው ሲሞላ እያነጻጸሩ መጠየቅ ለመረጃ ሰጪው ሁኔታዎችን ለማስታወስ ይረዳል፡፡ እንዲሁም መረጃው በሚሰበሰብበት ቤተሰብ አካባቢ የተከናወኑ ድርጊቶች (ለምሳሌ፡- ለቅሶ፣ ስብሰባ፣ ሰርግ፣ በዓል ...ወዘተ) መኖራቸው ከታወቀ ይህንን በማነፃፀሪያነት መጠቀም ጥሩ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች በየዕለቱ/በየቀኑ ከአንድ በላይ ሥራ ሊሠሩ እንደሚችሉ በመገንዘብ የሥራ ሰዓት አጠያየቁ በሁሉም ሥራዎች የዋለውን የሥራ ሰዓት ብዛት መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በፈረቃም ሆነ በሥራ ባሕሪያቸው የተነሣ በቀንና በምሽት ወይም በምሽት ብቻ የሚሠሩ ሰዎች ስላሉ ይኸም ተጣርቶ መረጃው ሁለቱን ወቅቶች በማካተት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡

## በቀን ውስጥ እንደሥራ ሰዓት የሚያዙት የሚከተሉት ናቸው፤

ሀ. ዋነኛ ሥራቸውንና ሌላ ሥራ ካላቸውም በተጠቀሰው ቀን በሥራ ቦታው ተገኝተው ሥራ የሠሩበት ሰዓት፣

ለ. ከስራ ቦታቸው በተለየ ሥፍራ ቢሆንም ለምሳሌ፡- ለሥራው የሚሆኑ ዕቃዎችን በማዘጋጀት፣ በመጠገን፣ በማጽዳትና ስለ ሥራው ሪፖርት በማዘጋጀት የሚጠፉ ሰዓቶች፣

ሐ. ዕቃ ለሽያጭ የሚያመርቱ ሰዎች ጥሬ ዕቃውን ለመግዛት የሚያጠፉት ሰዓትና ገዝተው እቤት ያደረሱበት ሰዓት እንዲሁም ያመረቱትን ምርት ለመሸጥ ገበያ የሄዱ ሰዎች ምርቱን ይዘው ከቤት ከወጡ ጀምሮ ሸጠው እስካበቁ ድረስ ያለው ሰዓት እንደስራ ሰዓት ይያዝላቸዋል፡፡ በገበያ ውስጥ ለራስ ፍጆታ የሚሆኑ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን ለመግዛት የባከነው ሰዓት እንዳይደመር መጠንቀቅ ይገባል፡፡

መ. በስራ ቦታ ተገኝተው ለመሥራት ዝግጁ እስከሆኑ ድረስ በተለያየ ምክንያት ወይም ችግር ስራው ባይሰራም እዛ ቦታ የተገኙበት ሰዓት እንደሠሩ ይያዛል፡፡ እንዲሁም በስራ መካከል ለአጭር ሰዓት የባከኑ ጊዜዎች ለምሳሌ የሻይ እረፍት እንደ ስራ ሰዓት ይቆጠራሉ፡፡

## የሚከተሉት ከስራ ሰዓት ውስጥ አይደመሩም፤

1. ክፍያ ቢያገኙበትም ባያገኙበትም በስራ ገበታ ላይ ያልተገኙባቸው ጊዜያቶች እንደሥራ ሰዓት አይያዝም፡፡ ሥራ ቢኖራቸውም ሥራ ላይ ሳይገኙ ከቀሩ የሠሩት የሥራ ሰዓት ዜሮ ተብሎ ይመዘገባል፡፡

2. ለምሳ የሚባክን ጊዜ እንደ ስራ ሰዓት አይቆጠርም፡፡

3. ከመኖሪያ ቤት ሥራ ለመጀመር ወደ ስራ ቦታ የሚደረግ የጉዞ ሰዓት እና ከስራ ቦታ ወደ መኖሪያ ቤት ለመመለስ የሚጠይቅ ጊዜ እንደሥራ ሰዓት አይቆጠርም፡፡ ይህም ማለት በአንድ በተወሰነ የሥራ ቦታ ለሚሠሩ ሰዎች እንደ ሥራ ሰዓት የሚቆጠረው የስራ ቦታ ከደረሱበት ጀምሮ በቀኑ ውስጥ የሚሠሩትን ሥራ ጨርሰው ከሥራ ቦታ እስከወጡበት ያለውን ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የሥራ ፀባያቸው ከቦታ ቦታ መዘዋወር የሚያስፈልገው ለምሳሌ ጋዜጣ ሻጭ፡-
ሊስትሮ፣ እቃ ግዢ ሠራተኛ፣ ሾፌር ... ወዘተ ሥራ በማፈላለግ የሚያጠፉትን ጊዜ እንደሥራ ሰዓት ይያዛል፡፡

4. በግል ሥራ በሚተዳደሩና ለቤተሰብ ያለክፍያ ለሚሠሩ ሰዎች በተለይ ሥራው በቤታቸው አካባቢ ከሆነ ከምርታማ ሥራቸው በተጨማሪ እንደ ቤት ውስጥ ሥራ ያሉ ምርታማ ያልሆኑ ሥራዎች የሠሩበት ሰዓት ከስራ ሰዓት ጋር እንዳይደመር ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

5. በተለማማጅነት ያሉ ሰዎች በሚለማመዱት ሙያ ላይ በመስራት ተሳትፎ ሳያደርጉ በማየት ብቻ ያሳለፉት ሰዓት እንደሠሩ አይያዝላቸውም፡፡ ለምሳሌ፡- አንዳንድ በጋራዥ ውስጥ እየተለማመዱ ያሉ ግለሰቦች ከሰዓት በፊት በ"ቲዎሪ" መልክ ከ2-6 ሰዓት ቢማሩና ከሰዓት በኋላ ከ7 እስከ 11 ሰዓት ከጋራዥ ሰራተኞች ጋር ሥራ እየሠሩ (እያገዙ) ቢውሉ እንደስራ ሰዓት የሚመዘገብላቸው ከሰዓት በኋላ የሠሩበት 4 ሰዓት "04" ተብሎ ነው፡፡

6. በግለሰብ ቤት በዘበኝነት ተቀጥረው ቀንም ሆነ ማታ የሠሩት ሥራ እንደ ሥራ ሰዓት የሚወሰድላቸው ቢሆንም በእንቅልፍ የሚያጠፉት ሰዓት ግን እንደሥራ ሰዓት አይያዝም፡፡

ባለፉት 7 ቀናት የተከናወኑ ሥራዎችን የሥራ ሰዓት ጥያቄ የማቅረቡም ሆነ ለመረጃ ሰጪው የየዕለቱን ሁኔታ ወደ ኋላ ተመልሶ በማስታወስ መመለሱ አስቸጋሪ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም በመረጃ ሰብሳቢውም ሆነ በመረጃ ሰጪው በኩል ትዕግሥት ኖሮና ጊዜ ሰጥቶ መልሱን ለማግኘትም ሆነ መልሱን ለመስጠ

ት ቀናነቱ ካለ ጥሩ መረጃ ሊገኝ እንደሚችል ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በተለይ መረጃ ሰብሳቢዎች መረጃ ሰጪዎችን አስቀድሞ ስለመረጃው አስፈላጊነት፣ መረጃውን በመስጠት በኩል ሳይቸኩሉ አስታውሰው መስጠት እንደሚገባቸው ማስረዳትና ማረጋጋት ይጠበቅባቸዋል፡፡

በዚህ መሠረት ለእያንዳንዱ ቀን የተገኘው መረጃ በማስታወሻ ላይ ከተሞላ በኋላ በሳምንቱ ውስጥ የሠሩት የሥራ ሰዓት ተደምሮ የሳምንቱ ድምር በሚለው ሥር መሞላት አለበት፡፡ በሳምንት ውስጥ የሠሩት የሥራ ሰዓት ድምር 97 እና ከዚያ በላይ  ከሆነ 97 በካርድ ኮለሙ ይሞላል፡፡

## ዓምድ 27 መረጃ ሰብሳቢ፡ ------------------- በዓምድ 26 ባለፉት 7 ቀናት የሰሩት የስራ ሰዓት ድምርን ተመልከት/ቺ

በዚህ ዓምድ መረጃ ሰብሳቢው ለመልስ ሰጪው ጥያቄ ሳያቀርብ በዓምድ 26 የተሞላውን  የሳምንቱን የሥራ ሰዓት ድምር በማየት እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ስንት ሰዓት እንደሰራ ያገናዝባል፡፡  4 ሰዓትና በላይ ለሰሩ ኮድ 1 ሞልቶ ወደ ዓምድ 29 ይሻገራል፡፡  ከ4 ሰዓት በታች ለሠሩ ግን ኮድ 2 ሞልቶ በተከታዩ ዓምድ ያለውን ጥያቄ ያቀርብላቸዋል፡፡

## ዓምድ 28 ሥራ እያሎት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በሥራ ላይ ያልተሰማሩት? (ከአራት ሰዓት በታች የሰሩት?)

ይህ ጥያቄ የሚመለከታቸው ባለፉት 7 ቀናት ሥራ ላልሠሩ /በዓምድ 24 ላይ ኮድ 2 ለተሞላላቸው/ እና በዓምድ 27 ኮድ 2 ማለትም ባለፉት 7 ቀናት ከ4 ሰዓት በታች ለሠሩ) የቤተሰብ አባላት ነው፡፡  እነኚህ ሰዎች ሥራ እያላቸው ከስራቸው ለጊዜው ቀርተው እንደሆነ ለማወቅ «ሥራ እያለዎት ነበር ባለፉት 7 ቀናት በሥራ ላይ ያልተሰማሩት?» ተብለው ተጠይቀው አዎን ካሉ ከኮድ 1-3 ካሉት ኮዶች መካከል ተስማሚው ኮድ ይሞላላቸዋል፣ የለም ካሉ ደግሞ ኮድ 4 ተሞልቶ ወደ ዓምድ 44 ይሻገራሉ፡፡

ከስራቸው ቀሩ የሚባሉ ሰዎች ባለፉት 7 ቀናት በዓመት ፈቃድ፣ በወሊድ ፈቃድ፣ በሕመም፣ በትምህርት ወይም በስልጠና ላይ ስለሆኑ፣ ለጊዜው ሥራው በተለያየ  ምክንያት ስላቆመ (ለምሳሌ፡- ዕድሳት፣ የጥሬ ዕቃ እጦት፣ የመብራት አለመኖር ... የመሳሰሉት) ያልሠሩ ግን ሁኔታው/ችግሩ ሲቃለል ወይም ጉዳያቸው ሲያበቃ ወደ ስራቸው የሚመለሱ መሆን አለባቸው፡፡

ሥራ አጥ(ፈላጊ) የነበሩ ግን ከጥናቱ ሳምንት በኋላ የሚጀምሩት ሥራ ያገኙ ሰዎች ከሥራ እንደቀሩ አይቆጠርም፡፡  ነገር ግን ያገኙትን ሥራ በጥናቱ ሳምንት ውስጥ መጀመር ኖሮባቸው በተለያየ እክል ምክንያት ሳይጀምሩ የቆዩ ከሥራ እንደቀሩ ይቆጠራል፡፡

አንድ ሰው ከሥራ ቀረ የሚባለው ከሚከተሉት ቢያንስ አንዱን ካሟላ ነው፣

1. በቅጥር ለሚሠሩ በቀሩበት ወቅት ሙሉ ወይም ከፊል ክፍያ የሚያገኙ፣ ወይም
2. በቅጥር ለሚሠሩ ከሥራ ያስቀራቸው ምክንያት ሲቃለል ወደ ቀድሞ ሥራቸው የሚመለሱ፣ ወይም
3. በቅጥር ለሚሠሩ ከሥራ ከቀሩ 2 ወር ያለሞላቸው መሆን አለባቸው፡፡
4. በግል ሥራ ለሚተዳደሩ እነሱ ከሥራ ቢቀሩም ድርጅታቸው ያልተዘጋ (ተመልሶ የሚከፈት) መሆን አለበት፡፡
5. ለተለማማጆች በልምምዳቸው ወቅት በገንዘብ/በዓይነት ክፍያ የሚያገኙ ከሆነ ለዚህ ጥያቄ በቅጥር እንደሚሠሩ ተቆጥረው ከላይ በቅጥር ለሚሠሩ ከ 1 እስከ 3 የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ ሥራ እያላቸው እንደቀሩ ይቆጠራሉ፡፡

ማስታወሻ፡- ተባራሪ ስራ (የቀን ጉልበት ሠራተኞች ለምሳሌ የተገኘውን ሥራ ሸክም መሸከም፥ እንጨት መፍለጥ፥ ውሃ መሸከም መደለል የመሳሰሉት እየሠሩ የሚውሉ) ለሚሠሩ በጥናቱ ሳምንት ስራ ካልሠሩ ከስራቸው እንደቀሩ አይቆጠርም፣ ያለክፍያ ለቤተሰቡ ሲሰራ የነበረ ነገር ግን በጥናቱ ሳምንት ያልሠራ ግለሰብ «ሥራ እያላቸው ከስራ የቀሩ» ተብሎ አይቆጠርም፡፡  እንዲሁም በልምምዳቸው ወቅት ምንም አይነት የገንዘብ/የዓይነት ክፍያ የማያገኙ ተለማማጆች ነገር ግን በድርጅቱ ምርታማ ተግባር የሚሳተፉ በጥናቱ ሳምንት ካልሰሩ «ሥራ እያላቸው ከሥራ የቀሩ» ተብሎ አይቆጠርም፡፡

በዚህ መሠረት አማራጭ መልሶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. አዎን የግል ሥራዬ/ድርጅቴ አልተዘጋም
2. አዎን ለቀረሁበት ጊዜ እየተከፈለኝ ነው
3. አዎን ወደ ስራ ለመመለስ ቃል ተገብቶልኛል
4. የለም በግልም ይሁን በቅጥር የማከናውነው ምርታማ ሥራ የለኝም፡፡

## ዓምድ 29 <u>ባለፉት 7 ቀናት የሰሩት የዋነኛ ስራዎ ዓይነት ምንድነው?</u>

በዚህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ተግባር ላይ ሲሳተፉ የነበሩ ሰዎች /በዓምድ 27 ኮድ 1 የተሞላላቸው/ እና ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ተግባር ላይ ባይሳተፉም ሥራ የነበራቸው /በዓምድ 28 ከኮድ 1-3 የተሞላላቸው/፣ ስለ ዋነኛ ሥራቸው ዓይነት ይጠየቃሉ:: ከአንድ በላይ ሥራ ለነበራቸው አባላት የሚጠየቅላቸው ስለ ዋናው ሥራቸው ማለትም ከሌሎቹ የበለጠ ጊዜ የወሰደውን/የሚወስደውን ይሆናል:: የሥራ ዓይነትም የሚገለጸው በአብዛኛው ጊዜ ግለሰቡ ምን በማድረግ እንደሚውል በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ በዝርዝር በመመዝገብ ይሆናል:: የሥራ ዓይነት በእርሻ ሥራ ላይ ለተሠማሩ ግለሰቦች በሚገለጽበት ጊዜ እውቀት ያለው ገበሬ፣ የእርሻ ሠራተኛ፣ እረኛ፣ ቅጥር እረኛ፣ አዳኝ፣ ዓሣ አጥማጅ ... ወዘተ እየተባለ ይሆናል::

የሥራ ዓይነት ተብሎ የሚመዘገበው ግለሰቡ በአብዛኛው ሲያከናውን የነበረው የሥራ ዓይነት ነው እንጂ የሚሠራበት ድርጅት የሚያመርተውን የምርት ዓይነት መሆን የለበትም:: <u>ለምሳሌ</u>፡- ለአንድ በታይፒስትነት ለምታገለግል ሠራተኛ የሥራ ቦታዋ ሆስፒታልም ይሁን ፋብሪካ፥ ትምህርት ቤት፥ ...ወዘተ ሁልጊዜም የሚመዘገብላት «ታይፒስት» የሚለው የሥራ ዓይነት ነው:: የሥራው ዓይነት በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ከተመዘገበ በኋላ ለሥራው ዓይነት ተገቢው ኮድ በዋናው መሥሪያ ቤት ይሰጠዋል:: የሥራው ዓይነት በሚመዘገብበት ወቅትም ተገቢውን ኮድ ለመስጠት በሚያስችል መልክ መሆን ይኖርበታል:: ለዚህም ተግባር ከመልስ ሰጪዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ሁሉ በትክክል የግለሰቡን የሥራ ዓይነት የሚያመለክቱ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: <u>ለምሳሌ</u>፡- ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን፥ ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን፥ ለቄስ ት/ቤት መምህራን፥ ለታይፕ ት/ቤት መምህራን የተለያየ ኮድ ስለሚሰጣቸው የሥራ ዓይነት ሲመዘገብ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: በተመሣሣይ ሁኔታም ለግብርና ሥራ ለተሠማሩ ሁሉ ገበሬ ብሎ መጻፍ ትክክል አይሆንም:: ምክንያቱም የግብርና ሥራ እውቀት ላላቸው ገበሬዎች (ማለትም የማሣ አዘገጃጀት፥ አስተራረስ፥ መቼ እንደሚታረም፥ የሚዘራበትን ሰዓትና ለግብርና አስፈላጊ የሆነውን ዕውቀት ከወላጅ ወይም ከልምድ የቀሰሙ) እና ዝቅተኛ የግብርና ሠራተኞች (የግብርና ዕውቀታቸው ደረጃ የሚታዘዙትን ሥራ ከመሥራት የማያልፈውን) የተለያዩ ኮዶች ስለሚሰጣቸው ነው:: በተጨማሪም የሚሰሩበት መሥሪያ ቤትን ብቻ ጠይቆ መልሱን በዚህ ዓምድ መመዝገብ ትክክል አይደለም:: ምክንያቱም በአንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ስለሚገኙ እነዚህን ማጣራት ስለሚያስፈልግ ነው:: <u>ለምሳሌ፡</u>- በአንድ የማዕድን ማውጫ ድርጅት ውስጥ ዋና ሥራ አስኪያጁ፥ የመምሪያ ኃላፊዎቹ፥ ኬሚስቶቹ፥ ኢንጅነሮቹ፥ አካውንታንቶቹ፥ ቀያሾቹ፥ የአፈር ቴክኒሽያኖቹ፥ ኤክሲኩቲቭ ሴክሬተሪ፥ ታይፒስቶቹ፥ ገንዘብ ከፋዮቹ፥ ቴሌፎን ኦፕሬተር፥ ለማዕድን ማቅለጫ የተተከለ ማሽን ኦፕሬተሮቹ፥ የመኪና ሾፌሮቹ፥ የማዕድን አውጪ ተራ ወዛደሮች፥ ሁሉም የተለያየ ኮድ የሚሰጣቸው የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ስለሆኑ መረጃው በጥንቃቄ እየተጠየቀ ትክክለኛው የግለሰቡ የሥራ ዓይነት ይመዘገባል:: ከዚህ በተጨማሪ ተመሣሣይ የሆኑ ሥራዎችም ቢሆኑ ሥራውን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የትምህርት ደረጃ ወይም የእውቀት ደረጃና ሥራውን ለማካሄድ ሠራተኛው የሚጠቀምበት መሣሪያ ዓይነት የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ያደርጓቸዋል:: ለምሳሌ የሕክምና ዶክተርና ነርስ የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ናቸው:: እንዲሁም የጨርቃ ጨርቅ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተሮችና የማምረቻ ፋብሪካ ተራ ወዛደሮች የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ናቸው:: በንግድ መስክ ከሚገኙ የሥራ ዓይነቶች ውስጥም፥ ገንዘብ ተቀባዮች፥ የሱቅ አሻሻጮች፥ የኪዮስክ አሻሻጮች፥ እንጀራ ጋጋሪዎች፥ ጠላ ጠማቂዎች፥ ቆሎ አዟሪዎች ሁሉም የተለያዩ የሥራ ዓይነቶች ናቸው:: አንዳንድ ግለሰቦች ከአንድ የበለጠ ሥራ ሊኖራቸው ይችላል:: በዚህ ጊዜ በዓምድ 29 መመዝገብ ያለበት የሥራ ዓይነት ግለሰቡ ከሁለቱ ወይም ከሶስቱ ሥራዎች ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ይበልጡን ጊዜ ያጠፋበት ዋነኛ የሥራ ዓይነት ነው:: ሥራ እያላቸው ባለፉት 7 ቀናት ሳልሠሩ (በዓምድ 28 ከኮድ 1-3 የተሞላላቸው) ዋነኛ ሥራ ተብሎ የሚመዘገብላቸው ከሥራ ከመቅረታቸው በፊት ይሠሩት የነበረውን ዋነኛ ሥራ ነው:: በመጠይቁ ላይ የሥራውን ዓይነት በትክክል ለመጻፍ እንዲረዳ ከዚህ በታች የተወሰኑ የሥራ ዓይነቶች እንደምሳሌ ቀርበዋል:: ስለዚህ መልሱ ከነዚህ ውስጥ ወይም ከነዚህ ጋር ተመሣሣይ የሆነ የሥራ ዓይነት ሊሆን ስለሚችል ዝርዝሩን በቅድሚያ ማጥናት ያስፈልጋል:: የመልሱ አጻጻፍም በዝርዝሩ የቀረበው ወይም የሚመሳሰል መሆን አለበት:: የተሰጠው ባዶ ቦታ አነስተኛ ሆኖ ከተገኘ በተቻለ ያህል አብቃቅቶ መጻፍ ያስፈልጋል::

የቢሮ ኃላፊ
የፊዚዮቲራፒ ረዳት
የፋርማሲ ረዳት
የከብት ሕክምና ረዳት
ነርስ
ሳኒቴሪያን
ዘመናዊ አዋላጅ

የ1ኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር
የሕጻናትማሳደጊያ ት/ቤት መምህር
የቄስ ት/ቤት መምህር
የቁርዓን ት/ቤት መምህር
የመኪና መንዳት መምህር
የታይፕ መምህር

ኤክስኪዩቲቭ ሴክሬተሪ
የስታቲስቲክስ ቴክኒሽያን
የፍርድ ቤት ጸሐፊ
የወንጀል ምረመራ ሠራተኛ
የዜና አንባቢ
ዘፋኝ
የመድረክ ተዋናኝ
ስፖርተኛ

ታይፒስት
ፅሐፊ
የሂሣብ ፀሐፊ
ማመልከቻ ፀሐፊ

ገንዘብ ተቀባይ
ገንዘብ ከፋይ
ቴሌፎን ኦፕሬተር

የቡና ቤት አሰተናጋጅ
ባሬስታ
የወጥ ቤት ሠራተኛ
ፀጉር አስተካካይ
የውበት ሣሎን ሠራተኛ
ባህላዊ መድሐኒት አዋቂ
የልምድ አዋላጅ
ቄስ
ሼክ
ፖሊስ
የእሳት አደጋ ተከላካይ

የሱቅ አሻሻጭ
የኪዮስክ አሻሻጭ
የጉልት አሻሻጭ

ጥጥ ለንግድ አምራች
ሻይ ለንግድ አምራች
ወይን ለንግድ አምራች
ሸንኮራ ለንግድ አምራች
ሰብል ለንግድ አምራች
ዶሮ ለንግድ አምራች
ከብት ለንግድ አምራች
የደን ሠራተኛ
ከሰል አክሳይ
ዓሣ ለንግድ አስጋሪ

የግብርና ዕውቀት ያላቸው ገበሬ
ሙያው ያላቸው ዓሣ አጥማጅ
የዞን ባለሥልጣን
የወረዳ ባለሥልጣን
የፖለቲካ ድርጅት ባለሥልጣን
የሙያ ማሕበር ባለሥልጣን
የተራድኦ ድርጅት ባለሥልጣን
የቀበሌ ባለሥልጣን
የጎሣ መሪ

ዋና ሥራ አስኪያጅ

የመምሪያ ኃላፊ
የዋና ክፍል ኃላፊ
የአገልግሎት ኃላፊ

ኬሚስት
የኮምፒዩተር ፕሮግራመር
ኢንጂነር

ባዮሎጂስት
የሕክምና ዶክተር
የከብት ሕክምና ረዳት

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህር
የት/ቤት ዳይሬክተር

አካውንታንት
ዳኛ
ጠበቃ
ኢኮኖሚስት

የምሕንድስና ቴክኒሽያኖች
ቀያሽ
የኮምፒዩተር ኦፕሬተር
ረዳት ፕሮግራመር
የቴሌኮሙኒኬሽን ቴክኒሽያን
የሕክምና መሣሪያ ቴክኒሽያን

የአፈር ቴክኒሽያን
የጤና ረዳት
የጥርስ ሕክምና ረዳት

ድንጋይ ጠራቢ
ድንጋይ አውጪ
አሸዋ አውጪ
ማዕድን አውጪ
ግንበኛ
አናጺ
ለሳኝ
የባንቧ ሠራተኛ
ቀለም ቀቢ

ብረት በያጅ
ቀጥቃጭ
የመኪና ሜካኒክ
የሬዲዮ አዳሽ
የቴሌፎን መስመር ዘርጊ

አንጥረኛ
ሸክላ ሠሪ
የእንጨት እደጥበብ ሠራተኛ
የቀርክሃ እደጥበብ ሠራተኛ
የቃጫ እደጥበብ ሠራተኛ
ፎቶግራፍ አንሺ

የልኳንዳ ሠራተኛ
የእንጀራ ጋጋሪ
ጠላ ጠማቂ
አረቄ አውጪ
ትምባሆ አዘጋጅ
የእንጨት ቁሳቁስ አምራች
ሸማኔ
ፈቃይ
ልብስ ሰፊ
ፋቂ

ጫማ ሰፊ

ለእንጨት መሠንጠቂያ የተተከለ ማሽን ኦፕሬተር
ለማዕድን ማቅለጫ የተተከለ ማሽን ኦፕሬተር
የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ኦፕሬተር

የላስቲክ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የጎማ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የኬሚካል ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር

የሕትመት ማሽኖች ኦፕሬተሮች
የጨርቃ ጨርቅ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የስኳር ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የቢራ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የለስላሳ መጠጥ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተር
የቆዳ ማልፊያ ማሽን ኦፕሬተሮች

ጫማ መስሪያ ማሽን ኦፕሬተሮች
የምግብ ማምረቻ ማሽን ኦፕሬተሮች
የአውቶቡስ ሹፌር
የመኪና ሹፌር
የትራክተር ሹፌር

ቆሎ አዟሪ
የልዋጭ ነጋዴ
ጋዜጣ አዟሪ
በየመንገዱ ዕቃ ሻጭ
ሊስትሮ
የቤት ሠራተኛ
ሹሩባ ሠሪ
ልብስ አጣቢ
የቡና ቤት ሣህን አጣቢ
የቡና ቤት አልጋ አንጣፊ
ዘበኛ
ተላላኪ

የድንጋይ ማውጣት ተራ ወዛደር
የአሸዋ ማውጣት ተራ ወዛደር
የማዕድን ቁፋሮ ተራ ወዛደር
የኮንስትራክሽን ሥራ ተራ ወዛደር
የጥገና ሥራ ተራ ወዛደር
የማምረቻ ፋብሪካ ተራ ወዛደር
የትራንስፖርት ተራ ወዛደሮች

እረኛ
ዝቅተኛ የእርሻ ሥራ ሠራተኛ
ዝቅተኛ የዓሣ ማስገር ሠራተኛ

የጦር ኃይል አባል

## ዓምድ 30 <u>ባለፉት 7 ቀናት የሠሩትን/ያከናወኑትን ዋነኛ ተግባር/ሥራ በዝርዝር ይግለፁልኝ</u>

በዚህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ምርታማ ሥራ ለሰሩ (በዓምድ 27 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ወይም ሥራ እያላቸው ላልሰሩ (በዓምድ 28 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው) ያከናወነቱን/ሲያከናወኑት የነበረውን ዋነኛ የሥራ ዓይነት በዝርዝር/በተብራራ ሁኔታ የሚገለፅበት ነው፡፡ በዓምድ 29 በጥቅል የተገለፀውን ዋነኛ የሥራ ዓይነት መሠረት በማድረግ በዋናው መ/ቤት ተገቢውን የሥራ ምደባ ኮድ ለመስጠት አስቸጋሪ ስለሚሆን የሥራውን ዓይነት በዝርዝር መግለፅ አስፈላጊ ነው፡፡ <u>ለምሳሌ</u>፡- በዓምድ 29 «የዞን ባለስልጣን» ለተሞላላቸው የዞን ሊቀመንበር፣ የዞን አስተዳደር ጸሐፊ፣ የዞን መስተዳድር ሥራ አስፈፃሚ ÷ እንዲሁም «የቢሮ ኃላፊ» ለተሞላላቸው የክልል የጤና ቢሮ ኃላፊ፣ የክልል የግብርና ቢሮ ኃላፊ ...ወዘተ÷ «የሕክምና ዶክተር» ለተሞላላቸው ጠቅላላ ሕክምና ዶክተር፣ የጥርስ ሕክምና ፣ የቆዳ ሕክምና... ወዘተ÷ «ሥራ አስኪያጅ» ለተሞላላቸው የሽያጭ ሥራ አስኪያጅ፣ የምርት ሥራ አስኪያጅ፣ የመንግሥት መ/ቤት ሥራ አስኪያጅ፣ የሆቴል ሥራ አስኪያጅ... ወዘተ በማለት በዝርዝር ሊሞላ ይችላል፡፡ ለፀሐፊዎች በዝርዝር የስቶር ፀሐፊ፣ የአስተዳደር ፀሐፊ፣ የፍርድ ቤት ፀሐፊ፣ ... ወዘተ ተብሎ ሊሞላ ይችላል፡፡ በተለይ

ም መደበኛ ባልሆኑ የሥራ ዘርፎች (የቤት ውስጥና በቤት አካባቢ የማምረት ሥራ፣ የጉልትና የመንገድ ዳር ንግድ፣ በቀን የጉልበት ሥራ…ወዘተ) የተሠማሩ ሰዎች የሚያከናውኑዋቸው የሥራ ዓይነቶች በምርት፣ በንግድ/አገልግሎት ተግባር ለይቶ ለመመደብ በሚያስችል መልኩ በዝርዝር መፃፍ ይኖርበታል። ለምሳሌ:- አረቄ አውጥተው በችርቻሮ የሚሸጡ ሰዎች በማምረትና በችርቻሮ ንግድ የተሰማሩ በመሆናቸው « አረቄ አውጥቶ በችርቻሮ መሸጥ» ተብሎ የሚመዘገብ ሲሆን አረቄ ገዝተው በጅምላ ለሚያከፋፍሉ «አረቄ ገዝቶ በጅምላ መሸጥ» ተብሎ መሞላት ይኖርበታል። እንዲሁም አረቄ ገዝተው ለሚቸረችሩ «አረቄ ገዝተው በችርቻሮ መሸጥ» የሚል ይሞላላቸዋል።

## ዓምድ 31 ዋነኛ ሥራዎን ያከናወኑበት ድርጅት/የሥራ ዘርፍ ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድነው?

ይህን ዓምድ ለመሙላት ግለሰቡ የት ወይም በየትኛው ድርጅት እንደሚሠሩ በመጠየቅና ከዚያም ድርጅቱ ምን እንደሚያመርት፣ እንደሚነግድ /የጅምላ ወይም የችርቻሮ ንግድ/ ወይም ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚሰጥ መጠየቅ ያስፈልጋል። ድርጅት ሲባል  የተለየ ክፍል ወይም ቦታ ሳይኖራቸው በመኖሪያ ቤት ውስጥ፣ በበረንዳ፣ በትናንሽ ገበያዎች /ጉልቶች/፣ በመንገድ ላይ፣ …ወዘተ ከሚከናወኑ ጥቃቅን ሥራዎች አንስቶ የተለየ አድራሻና አደረጃጀት ያላቸውን ፋብሪካዎችና እንዱስትሪዎችን ያጠቃልላል። ለምሳሌ:- በሚኖሩበት ቤት ውስጥ የሽመና፣ የልብስ ስፌት፣ ጠላ ወይም አረቄ ንግድ፣ … ወዘተ ምርታማ ሥራዎችን የሚያከናውኑ ምንም እንኳ የሚያከናውኑት ተግባር ሥርዓት ባለው ሁኔታ ተደራጅቶ ባይገኝም በዚህ ዓምድ እንደ ድርጅት ተቆጥሮ ምርቱ፣ ንግዱ ወይም አገልግሎቱ መገለጽ ይኖርበታል። አንዳንድ አነስተኛ ድርጅቶችን ወይም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን በአምራች፣ በአገልግሎት ወይም በንግድ ዘርፍ ለይቶ ለመመደብ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።  ከአንድ በላይ የሆነ የምርት ዓይነት ያላቸው ወይም አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ሲያጋጥሙ የድርጅቱ ምርት ወይም የአገልግሎት አይነት ተብሎ የሚጠቀሰው ድርጅቱ በአብዛኛው የሚሰጠው የምርት ዓይነት ወይም አገልግሎት አይነት ነው። ለምሳሌ:- አንድ የሲጋራ ፋብሪካ በተጨማሪነት ክብሪት የሚያመርት ቢሆን ድርጅቱ እንደ ሲጋራ አምራች ይመዘገባል። በተጨማሪም የምርት ዓይነቶች ወይም የአገልግሎት ዓይነቶች ተመሣሣይ እስከሆኑ ድረስ የሚመረቱት በግል ድርጅቶችም ሆኑ በመንግሥት ድርጅቶች በተመሣሣይ ክፍል ይመደባሉ። ለምሳሌ:- ከብት እርባታ በግለሰብም ይካሄድ በትልቅ የመንግሥት እርሻ ሁለቱም ተመሳሳይ ክፍል ይመደባሉ። ወይንም አንድን ምርት የሚያመርተው ድርጅት የመንግስት ፋብሪካ ይሁን ወይም የግለሰብ ድርጅት ተመሣሣይ መልስ ይመዘገብላቸዋል። በተጨማሪም አመራረቱ በዘመናዊ መልክ (ዘመናዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም) ይሁን በባሕላዊ ዘዴ (በእጅ በመሥራት) የምርቱ ዓይነት ወይም አገልግሎት ላይ ልዩነት አይፈጥሩም። ለምሳሌ:- በፋብሪካ ጫማ ለሚያመርት ወዛደር እና በእጁ ጫማ ለሚሰፋ ለሁለቱም «ጫማ ማምረት» ይመዘገብላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ድርጅቱ ለሚያመርተው ዋና ምርት ወይም አገልግሎት በአጋዥነት የሚያስፈልጉ ሌሎች ግልጋሎቶች ሁሉ ለየብቻቸው የሚመዘገቡ ሳይሆኑ የሚመዘገበው ዋናው ምርት ብቻ ይሆናል። ለምሳሌ:- የጫማ ምርት በሚያስገኝ ፋብሪካ ውስጥ ጫማ የማምረት ሂደቱን የሚያግዙ የሂሣብ ሥራ፣ የአስተዳደር ሥራ፣ የጽዳት ሥራ፣ የጥበቃ ሥራ፣ ወዘተ. የሚያከናወኑ ቢሆንም ለሁሉም የሚመዘገብላቸው «ጫማ ማምረት» የሚል መልስ ይሆናል። መረጃ በሚመዘገብበት ወቅት ችግር እንዳይፈጥሩ አንዳንድ የምርትና አገልግሎት አይነቶች ሰፋ ያለ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ከዚህ በታች ቀርበዋል።

**የእርሻ ምርት ማምረት:-** ሰብል፣ አትክልት፣ ጫት፣ ቡና፣ …ወዘተ. (የሚያመርቱ ለማምረቻ መሣሪያነት የማረሻ ከብቶችን አጣምረው ሊያረቡ ይችላሉ)

**የከብት እርባታ:-**

በሬ፣ ላም፣ ግመል፣ በግ፣ ፍየል፣ ዶሮ … ወዘተ. የሚያረቡ (የጓሮ ማሣ ሊኖራቸው ይችላል)

**እርሻና ከብት እርባታ:-** የእርሻ ምርትና የከብት እርባታን አጣምረው የሚሠሩ

**የግብርና አገልግሎት:-**

የከብት ማዳቀልና የእርሻ ዘዴ ማስፋፊያ አገልግሎት፣ የትራክተር አገልግሎትና የመሳሰሉት

**የጉልት ንግድ:-**

ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ ወይም ምግብ በሱቅ ሳይሆን በጉልት ወይም በገበያ የሚሸጡ (በሱቅ ውስጥና ከሱቅ ውጭ የሚካሄዱ የንግድ ዓይነቶች የተለያዩ ኮዶች ስለሚሰጧቸው በግልጽ አጣርቶ መጻፍ ተገቢ ይሆናል።)

**ሆቴል፡-** የመኝታ አገልግሎት ያላቸው ድርጅቶች (ምግብና መጠጥም ሊኖራቸው ይችላል)::

**ቡና ቤት፡-** የመኝታ አገልግሎት የሌላቸው

**ጠላ ቤት፡-** ጠላ የሚሸጥባቸው ቤቶች (ጠላው እዚያው ቤት የተጠመቀ ወይም የተገዛ ሊሆን ይችላል)

**ጠጅ ቤት፡-** ጠጅ የሚሸጥባቸው ቤቶች (ጠጁ እዚያው ቤት የተጣለ ወይም የተገዛ ሊሆን ይችላል)

**ጠጅ ማምረት፡-** ጠጅ ጥለው ለሌላ ቸርቻሪ በጅምላ የሚሸጡ

**የትምህርት አስተዳደር፡-** በሚኒስቴር መ/ቤት ወይም በክልል÷ ዞን÷ ... ወዘተ ጽ/ቤት የሚካሄዱ የአስተዳደር ተግባሮች

**የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት፡-** የትምህርት ቤቱ መምህራን÷ አስተዳደር ክፍልና ሌሎችን ይጨምራል::

**የግብርና አስተዳደር፡-** የሚኒስቴር መ/ቤቱና የክልል÷ የዞን÷ ... የአስተዳደር አገልግሎት የሚሰጡ ጽ/ቤቶች:: በወረዳ ደረጃና ሌሎች የግብርና አገልግሎት የሚሰጡ ጽ/ቤቶች ግን በግብርና አገልግሎት ይመደባሉ::

በዓምድ 31 የሚመዘገቡት የድርጅቱ ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነቶች ለምሳሌነት እንዲያገለግሉ የተወሰኑት ከዚህ በታች ቀርበዋል:: በመረጃ ምዝገባው ወቅትም የሚቀርቡት ከነዚህ መካከል ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የተጻፉና በዋናው መሥሪያ ቤት የድርጅት ምርት ወይም አገልግሎት ኮድ ሊያሰጡ በሚችል ሁኔታ የቀረቡ መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል::

እርሻ ምርት ማምረት
የከብት እርባታ
እርሻና ከብት እርባታ
የግብርና አገልግሎት
አደን
ያደን ምርት ማምረት
ዓሣ ማስገር

ድንጋይ ማውጣት
አሸዋ ማውጣት
ወርቅ ማምረት
የምግብ ዘይት ማምረት
የታሸገ ሥጋ ማምረት
የታሸገ ወተት ማምረት
የእህል ዱቄት ማምረት
ዳቦ መጋገር
እንጀራ መጋገር
ስኳር ማምረት
አልኮል መጠጥ ማምረት
አረቄ ማምረት
ቢራ ማምረት
ጠጅ ማምረት
ለስላሳ መጠጥ ማምረት
ሲጋራ ማምረት

ድርና ማግ ማምረት
ጨርቃ ጨርቅ ማምረት
የሽመና አገልግሎት
ገመድ ማምረት
ሥጋጃ ማምረት

የተሰፉ ልብሶች ማምረት
የልብስ ስፌት አገልግሎት
የቆዳ ምርት ማምረት
ኮርቻ ማምረት
ጫማ ማምረት
ጣውላ ማምረት
ሰሌን ማምረት
ዘንቢል ማምረት
ወረቀት ማምረት
የሕትመት አገልግሎት
ቀለም ማምረት

ሣሙና ማምረት
ኅማ ማምረት
ሲሚንቶ ማምረት
ብረት አቅልጦ ማምረት
የብረት በርና መስኮት ማምረት
ማረሻ ቀጥቅጦ ማምረት
ቢላዋ ቀጥቅጦ ማምረት
የኤሌክትሪክ ሽቦ ማምረት
ጋሪ ማምረት
የቤት ዕቃዎች ማምረት
ጌጣጌጥ ማምረት
ኤሌክትሪክ ማምረትና ማሰራጨት
የመጠጥ ውሃ ማምረት

የሕንፃ ግንባታ
የግድግዳ ቀለም መቀባት
የቤት መስታወት ማስገባት

የመኪና ጥገና
ቤንዚን ማከፋፈል
የእህል ጅምላ ንግድ
የጨርቃ ጨርቅ የጅምላ ንግድ
የጫማ የጅምላ ንግድ

የአትክልት ግሮሰሪዎች ንግድ
የምግብ ግሮሰሪዎች ንግድ
የጨርቃ ጨርቅ ሱቅ ንግድ
የተለያዩ ቁሳቁሶች ኪዮስክ ንግድ

የሥጋ ልኳንዳ ቤት
የአሣ መሸጫ ሱቅ
መድሐኒት ቤት
የብረታ ብረት መሸጫ ሱቅ
መጽሐፍ መሸጫ ሱቅ
የጉልት ንግድ
የመንገድ ዳር ሽንኩርት ንግድ

ሆቴል
ቡና ቤት
ምግብ ቤት
ሻይ ቤት
ጠላ ቤት

ጠጅ ቤት
አረቄ ቤት
የባቡር ትራንስፖርት
የጋማ ከብት ማከራየት አገልግሎት
የከተማ አውቶቡስ
የከተማ ታክሲ
ዕቃ በጋማ ከብት ማጓጓዣ
ዕቃ ተሸክሞ መጓጓዝ
ዕቃና ሰው በባሕር ላይ ማጓጓዝ
የአየር ትራንስፖርት
የፖስታ አገልግሎት
ቴሌኮሙኒኬሽን

የባንክ አገልግሎት
የኢንሹራንስ አገልግሎት

የቤት ዕቃዎች ኪራይ
የብስክሌት ኪራይ
የቪዲዮ ካሴት ኪራይ
የጥብቅና አገልግሎት
የሂሳብ ምርመራ አገልግሎት
የሕንፃ ሥራ ምክር አገልግሎት
የፎቶግራፍ አገልግሎት
የአገር አስተዳደር
የግብርና አስተዳደር
የመንግሥት አስተዳደር
የውጭ ጉዳይ አገልግሎት
የአገር መከላከያ
የፖሊስ አገልግሎት

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት
የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት
የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት
መደበኛ ሆስፒታሎች
መደበኛ ክሊኒኮች
የግል ክሊኒኮች
የከብት ሕክምና አገልግሎት
የኃይማኖት ድርጅቶች አገልግሎት
የሬዲዮ ጣቢያዎች
የኪነት አገልግሎት

የሙዚቃ አገልግሎት
የቤተመጻሕፍት አገልግሎት
የልብስ እጥበት አገልግሎት
የፀጉር ስራ አገልግሎት

የሊስትሮ አገልግሎት

የግለሰብ ቤት ዘበኞች
የግለሰብ ቤት የቤት ሠራተኞች

የዓለም አቀፍ ድርጅቶች

## ዓምድ 32 <u>በዋነኛነት የሚሠሩበትን ድርጅት/የሥራ ዘርፍ ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ዓይነት በዝርዝር ይግለፁልኝ</u>?

በዚህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ምርታማ ሥራ ለሰሩ (በዓምድ 27 ኮድ 1 ለተሞላላቸው ወይም ሥራ እያላቸው ባለፉት 7 ቀናት ሳልሠሩ (በዓምድ 28 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው) በዋነኛነት የሚሠሩበት/ይሠሩበት የነበረው ድርጅት/የሥራ ዘርፍ ዋና ምርት ወይም አገልግሎት ዓይነት በዝርዝር የሚገለፅበት ነው:: በዚህ ዓምድ የሚሞላው መረጃ በዋናው መ/ቤት ተገቢውን ኮድ ለመስጠት በሚያመች ሁኔታ ድርጅቱ/የሥራ ዘርፉ የሚያመርተው ወይም የሚሰጠው የአገልግሎት አይነት በዝርዝር በማብራራት ነው:: መረጃ በሚመዘገብበት ወቅት ችግር እንዳይፈጠር አንዳንድ የምርትና አገልግሎት አይነቶች ሰፋ ያለ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ምሣሌዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል:: <u>ለምሣሌ:</u>- "የግብርና አገልግሎት" ለተሞላላቸው (ከብት ማዳቀል አገልግሎት የሚሰጡ፣ የእርሻ ዘዴ ማስፋፊያ/ትራክተርና የእርሻ መሣሪያዎች ያለ ሾፌር ማከራየት፥ ትራክተር ከሾፌር ጋር ማከራየት... ወዘተ)፤ "የመጠጥ ውሃ ማምረት" ለተሞላላቸው (ውሃ ከወንዝ ቀድቶ መሸጥ፣ ውሃ በማጠራቀም በቧንቧ ለሕዝብ መሸጥ፣ ... ወዘተ) እንዲሁም "የግድግዳ ቀለም መቀባት" ለተሞላላቸው (ለግለሰቦች/ድርጅቶች ቀለም የመቀባት አገልግሎት ) እየተባለ በዝርዝር ሊሞላ ይችላል:: ለምሳሌ:- የግብርና ውጤቶችን ለሚያመርቱ ድርጅቶች ወይም የሥራ ዘርፎች የሚያመርቱት የግብርና ውጤት አይነት (ሰብል ማምረት፣ ከብት ማርባት፣ ሰብል ማምረትና ከብት ማርባት፣ ደን ማልማት ... ወዘተ) ተብሎ በዝርዝር መፃፍ ይኖርበታል:: በተመሳሳየ ሁኔታ ከግብርና ውጪ የሆኑ ምርቶችን ለሚያመርቱ የሚያመርቱት ምርት አይነት ተዘርዝሮ መገለፅ ይኖርበታል :: ለምሳሌ:- ከኑግ የምግብ ዘይት ማምረት፣ ፓስታ፣ ሞኮሮኒ ማምረት እና የመሳሰሉት:: በንግድ ሥራ ለተሰማሩት ደግሞ የሚነግዱት የሸቀጥ አይነት እና የንግዱ ደረጃ (ጅምላ/ችርቻሮ) ተብሎ መገለፅ ይኖርበታል::

## ዓምድ 33 <u>ዋነኛ ሥራዎ የቅጥር ሁኔታ ምን ነበር</u>?

1. **ተቀጣሪ የቤት ሠራተኛ**

   በቤት ሠራተኝነት ተቀጥረው በጥሬ ገንዘብ ወይም በአይነት እየተከፈላቸው የቤት ውስጥ ሥራዎችን የሚያከናውኑ <u>ለምሳሌ</u>:- ምግብ ማብሰል፣ ውሃ መቅዳት፣ ልብስ ማጠብ፣ ቤት ማፅዳት፣ ልጆችን መንከባከብ፣ ...ወዘተ የሚሠሩ::

2. **ተቀጣሪ ከቤት ውስጥ ሥራ ውጪ**

   ከቤት ውስጥ ሥራ ውጪ፣ በቋሚነት፣ በኮንትራት/በጊዜያዊነት፣ በየወሩ፣ በሣምንት ወይም በቀን ወይም በሠራው መጠን እና በመሣሰሉት ክፍያ እያገኙ በመንግሥት ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች (NGO) ወይም በግል ድርጅት ወይም በአምራቾች የሕብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩትን ያካትታል::

3. **<u>ቀጣሪ</u>**

   በግል የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ ድርጅታቸው ውስጥ ቢያንስ አንድ ሰው ቀጥረው የሚያሠሩ:: ቀጥረው የሚያሠሩ ሁሉ በሥራው ላይ አብረው ቢሠማሩም እንደ ቀጣሪ ይቆጠራሉ::

4. **<u>በግል ሥራ የሚተዳደሩ</u>**

   በግል ሥራ ወይም ድርጅታቸው ውስጥ የሚሠሩ ነገር ግን ምንም ተቀጣሪ የሌላቸው ናቸው:: የቤተሰብ አባላትን ያለክፍያ በማስተባበር ሥራቸውን የሚያካሂዱ ኃላፊዎች በዚህ ኮድ ይካተታሉ::

5. **<u>ሳይከፈላቸው ለቤተሰብ የሚሠሩ</u>**

   አንድ ግለሰብ የሚኖርበት ቤተሰብ ለሚያካሄደው እርሻ ወይም ሌላ ዓይነት ድርጅት ወይም ምርት የማምረት ተግባር ላይ ያለምንም ክፍያ የሚሠራ ከሆነ በዚህ ክፍል ይመደባል::

6. **<u>ተለማማጅ</u>**

   እነዚህ ግለሰቦች በአንድ መ/ቤት ወይም ድርጅት በተወሰነ የትምህርት ዘርፍ ሰልጥነውም ሆነ ሳይሰለጥኑ በተወሰነ ክፍያ <u>ለምሳሌ:</u>- ምግብ፣ መጠለያ ወይም ልዩ የኪስ ገንዘብ እየተሰጣቸው ወይም ከነጭራሹ ምንም ሳይከፈላቸው ሥራ በመለማመድ ላይ ያሉ ናቸው:: በቀጥታ ሥራ ላይ ምንም ተሳትፎ የሌላቸው በዚህ ኮድ አይካተቱም::

7. ***የአምራቾች የሕብረት ሥራ ማህበር አባላት***

በአምራቾች የሕብረት ሥራ ማህበር አባልነት በመሥራት ከማሕበሩ በሚያገኙት ድርሻ የሚተዳደሩ በዚህ ኮድ ይመዘገባሉ፡፡ ነገር ግን በማህበሩ አባልነት ሳይሆን በማህበሩ በተቀጣሪነት የሚሠሩ ሠራተ ኞች በኮድ 2 ይመዘገባሉ፡፡

8.

<u>ሌሎች</u> ከላይ ከተዘረዘሩት የቅጥር ሁኔታዎች በአንዱም ሊካተት ካልቻለ በዚህ ኮድ ይጠቃ ለላል፡፡ ለምሳሌ ፥ ለሕዝባውያን ድርጅት፥ ለሃይማኖት ድርጅት የሚሠሩና ምንም ክፍያ የገንዘብ/የ ዓይነትየማይሰጣቸው፥

## ዓምድ 34 ***ለሥራዎ በምን ያህል ጊዜ ይከፈልዎታል?***

የዚህ ዓምድ ጥያቄ የሚመለከታቸው ባለፉት 7 ቀናት በቤት ሰራተኝነት ወይም ከቤት ውስጥ ሥራ ው ጪ ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩትን (በዓምድ 33 ኮድ 1 ወይም 2 የተሞላላቸውን) ነው፡፡ በዚህ ዓምድ በ ቅጥር የሚሰሩትን ሥራ በሚመለከት ክፍያው በየስንት ጊዜ እንደሚከፈላቸው ይጠየቃል፡፡ ይኸውም እ ንደአካባቢውና እንደስራው ባህሪ ክፍያ በየወሩ፣ በየሣምንቱ ወይም በተሰራው ስራ መጠን...ወዘተ ሊከፈ ል ይችላል፡፡ እንዲሁም ክፍያው በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት ሊፈፀም ይችላል፡፡ <u>ለምሳሌ</u>፡- አንድ አ ናጺ ለሚሠራው ስራ በየቀኑ ወይም በየሰዓቱ ወይም በስራው መጠን ሊከፈለው ይችላል፡፡ በገጠር አካባ ቢ በእርሻ ሥራ ተቀጥሮ ለሚሠራ ሰው በየዓመቱ (ሰብል በሚሰበሰብበት ጊዜ) በዓይነት ሊከፍለው ይችላ ል፡፡ በዚህ መሠረት በዓምዱ ስር ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ተስማሚውን የአከፋፈል ሁኔታ የያዘ ው ኮድ በካርድ ኮለሙ ይሞላል፡፡ የኮዶቹ አሞላል (አማራጮች) ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

| | |
|---|---|
| 1. በሥራ መጠን | 5. በአሥራ አምስት ቀን |
| 2. በየሰዓቱ | 6. በየወሩ |
| 3. በየቀኑ | 7. በየዓመቱ |
| 4. በየሳምንቱ | 8. ሌላ |

## ዓምድ 35 ***ለሥራዎ የሚከፈልዎት በገንዘብ ነው ወይስ በዓይነት ወይስ በሁለቱም?***

አንድ ሰው ለሰራው ስራ ክፍያ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት (<u>ለምሳሌ</u> በምግብ፣ በልብስ፣ በእህል፣ በዕቃ.. . ወዘተ) ወይም በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ሊከፈለው ይችላል፡፡ በዚህ መሠረት ክፍያው በጥሬ ገንዘብ ብቻ ከሆነ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን በዓይነት ብቻ ከሆነ ኮድ 2 ይሞላል፡፡ ክፍያው በሁለቱም ( በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት) ከሆነ ደግሞ ኮድ 3 ይሞላል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ክፍያ ሲባል በጥሬ ገንዘብ ብ ቻ የሚከፈለውን ስለሚመስላቸው በዓይነት ይከፈላቸው እንደሆነ ማጣራት ተገቢ ነው፡፡ <u>ለምሳሌ</u> በቤት ሠ ራተኝነት ለተቀጠረች አንዲት ሴት ምግብና ልብስ በቅጥር ስምምነቱ ሊካተት ይችላል፡፡ ይኸውም በቅጥ ሩ ስምምነት ምግብና ልብስን ቀጣሪው ሳሟላ በወር ብር 60 የሚከፈላት ሆኖ ምግብና ልብስ በቀጣሪወ ፡ ሲሟላ ግን የወር ክፍያው 30 ብር ብቻ ቢሆን በመጀመሪያው አማራጭ ክፍያው በገንዘብ ብቻ (ኮድ 1 ) ሲሆን በሁለተኛው አማራጭ ግን በገንዘብና በዓይነት (ኮድ 3) ይሆናል፡፡ ነገር ግን በቅጥር ስምምነቱ ወቅት ምግብና፣ ልብስ ከግምት ውስጥ ያልገቡ ከሆነ በዓይነት ይከፈላል ሊባል አይቻልም፡፡

## ዓምድ 36-38 ***በቅርቡ ለሠሩት ሥራ በመጨረሻው ክፍያ ምን ያህል ተከፈለዎት?***

በነዚህ ዓምዶች ሥር ከጥናቱ በፊት በመጨረሻው ክፍያ በገንዘብ፣ በዓይነት እና በድምሩ የተከፈላቸው የ ክፍያ መጠን በብር የሚሞላባቸው ናቸው፡፡ የሶስቱም ዓምዶች አሞላል ከግራ ወደ ቀኝ ከመጨረሻው ዲጂ ት በመጀመር ይሆናል፡፡ <u>ለምሳሌ</u> የብሩ መጠን 653 ቢሆን በአራተኛው (በመጨረሻው) ካርድ ኮለም 3፣ በሶስተኛው ካርድ ኮለም 5፣ በሁለተኛው ካርድ ኮለም 6፣ በመጀመሪያው ካርድ ኮለም ደግሞ 0 ይሞላል፡ ፡

በማንኛም ደረጃ የሚሰጡ ክፍያዎች ወደሚቀርበው ሙሉ ቁጥር (Intiger) ተጠጋግተው ይመዘገባሉ፡፡ ጥ ናቱ እስከተካሄደበት ቀን ድረስ ምንም ክፍያ ላላገኙ ኮድ "9998" ይሞላል፡፡ ብር 9997 እና ከዛ በላይ ክፍያ ለሚያገኙ ኮድ 9997 ይሞላል፡፡

## ዓምድ 36 ***ክፍያ በገንዘብ?***

በዓምድ 35 ኮድ 1 ወይም ኮድ 3 ለተሞላላቸው ከጥናቱ በፊት በተከናወነው የመጨረሻ ክፍያ በጥሬ ገን ዘብ ምን ያህል እንደተከፈላቸው ተጠይቆ በዓምዱ ሥር ባሉት አራት ካርድ ኮለሞች የክፍያው መጠን በ ብር ይሞላል:: በገንዘብ ክፍያ ለማያገኙ ኮድ 'ኘ0000ኘ ይሞላል:: ነገር ግን ጥያቄ እስተካሄደበት ድረ ስ በተለያየ ምክንያት ክፍያ ያላገኙ ኮድ «9998» ይሞላላቸዋል:: ከ«9997» እና በላይ ክፍያ ለሚያገ ኙ ኮደ «9997» ይሞላላቸዋል::

## ዓምድ 37 ክፍያ በዓይነት (ወደ ብር ተቀይሮ)?

በዓምድ 35 ኮድ 2 ወይም ኮድ 3 ለተሞላላቸው ከጥናቱ በፊት በተከናወነው የመጨረሻ ክፍያ በዓይነት የተደረገው ክፍያ በአካባቢው የገበያ ዋጋ በብር ተገምቶ በካርድ ኮለሞቹ መጠኑ በብር ይሞላል:: ለምሳለ ፣ ክፍያ በእህል መልክ የሚያገኝ ገበሬ ከጥናቱ በፊት በተከፈለው ክፍያ 2 ኩንታል በቆሎ፣ 1ኩንታል ጤ ፍ እና 1 ኩንታል ገብስ ቢሰጠው በአካባቢው የገበያ ዋጋ ሲገመት 1 ኩንታል በቆሎ 80 ብር፣ 1 ኩንታ ል ጤፍ 150 ብር ፣ 1 ኩንታል ገብስ ደግሞ 120 ብር ቢገመት በአጠቃላይ ወደ ብር ሲቀየር የክፍያው መጠን 430 ብር ተብሎ ይሞላል:: በዓይነት ክፍያ ለማያገኙ ኮደ '0000' ይሞላል:: በዓይነት ክፍያ እነደሚከፈላቸው የገለፀ ነገር ግን ጥያቄ እሰከተካሄደበት ቀን ድረስ የዓይነት ክፍያ ላልተከፈላቸው ኮድ «9998» ይሞላል::

## ዓምድ 38 በአጠቃላይ የተገኘ ገቢ

ይህ ጥያቄ ለመልስ ሰጪዎች የሚቀርብ ሣይሆን በዓምድ 36 እና ዓምድ 37 የተሞላውን ብር በመደመር የሚሞላ ነው:: ዓምድ 36 እና ዓምድ 37 ኮድ «9998» ለተሞላላቸው በዚህ ዓምድም ኮደ «9998» ይሞላል::

## ዓምድ 39-40 የሥራ ሰዓት ፈረቃ

በነዚህ ዓምዶች ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆናቸውና ባለፉት 7 ቀናት ምርታማ ሥራ የሰሩ (በዓ ምድ 27 ኮድ 1 የተሞላላቸው) ወይም ሥራ ኖሯቸው ላልሰሩ (በዓምድ 28 ከኮድ 1-3 የተሞላላቸው) አ ብዛኛውን ጊዜ የሥራ ፈረቃቸውን እና ለስንት ሰዓት እንደሚሰሩ የሚጠየቁበት ነው::

## ዓምድ 39 አብዛኛውን ጊዜ የሚሰሩት ቀን ነው ወይስ ሌሊት?

ይህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት ምርታማ ስራ ለሰሩ አብዛኛውን ጊዜ ስራቸውን የሚያከናውኑበት በየትኛው ጊዜ (የሥራ ሰዓት ፈረቃ) እንደሆነ የሚጠየቅበት ነው:: ለዚህ ጥናት ከጥዋቱ 1 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ያለው ጊዜ ቀን ሲባል ከምሽቱ 1 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ያለው ጊዜ ደግሞ ምሽት/ሌሊት ይባላል:: በዚህ መሠረት አብዛኛውን ጊዜ ከጥዋቱ 1 ሰዓት እስከ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ የሚሠሩ የሥራ ሰዓት ፈረቃቸው ቀን ቀን እንደሆነ ተቆጥሮ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ከ ምሽቱ 1 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ለሚሰሩ ደግሞ «የምሽት/የሌሊት» የሥራ ሰዓት ፈረ ቃ ኮድ 2 ይሞላላቸዋል:: ከጥዋቱ 1 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት እና ከምሽቱ 1 ሰዓት እስከ ንጋቱ 1 2 ሰዓት ባለው ጊዜ የሚሰሩ «ቀንና ሌሊት» የሥራ ሰዓት ፈረቃ ተብሎ ኮድ 3 ይሞላላቸዋል::

## ዓምድ 40 አብዛኛውን ጊዜ ------------ ለስንት ሰዓት ይሰራሉ?

አብዛኛውን ጊዜ በሚሰማሩበት የሥራ ሰዓት ፈረቃ በአንድ ፈረቃ ለስንት ሰዓት እንደሚሰሩ ተጠይቆ አ ብዛኛውን ጊዜ የሚሰሩበት የሰዓት መጠን በዚህ ዓምድ ሥር ባሉት ሁለት ካርድ ኮለሞች ይሞላል:: ቀን ቀን ለሚሰሩት አብዛኛውን ጊዜ ቀን ቀን ለስንት ሰዓት እንደሚሰሩ ተጠይቆ በካርድ ኮለሞቹ የሚሞላ ሲ ሆን ምሽት/ሌሊት ለሚሰሩት በምሽት/በሌሊት ጊዜ ለስንት ሰዓት እንደሚሰሩ ተጠይቆ ሰዓቱ በካርድ ኮ ለሞች ይሞላል:: ቀንና ምሽት/ሌሊት ለሚሰሩት ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ ቀን እና ምሽት/ሌሊት የሚሰ ሩት አጠቃላይ ሰዓት ተደምሮ በካርድ ኮለሞቹ ይሞላል:: ለምሳሌ:- ቀን ቀን ለ 6 ሰዓት፣ ምሽት/ሌሊ ት ደግሞ ለ 4 ሰዓት የሚሰራ ሰው 6+4=10 በመሆኑ በካርድ ኮለሞቹ 10 ይሞላል::

## ዓምድ 41 ባለፉት 7 ቀናት ይሠሩት/ያከናወኑት ከነበረው ዋነኛ የሥራ ዓይነት በተጨማሪ/በተደ ራቢነት ሌላ ምርታማ ሥራ ሠርተዋል?

በዚህ ዓምድ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ተግባር ላይ ከአራት ሰዓት በላይ ተሠማርተው የነበሩና ዕድሜአቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰብ አባላት ሆነው /በዓምድ 27 ኮድ 1/ እና ሥራ እያላቸው ያልሠሩ/በዓምድ 28 ከኮድ 1-3 ለተሞላላቸው/ በዓምድ 30 ባለፉት 7 ቀናት በዋነኛነት ያከና ወኑት ስራ ተብሎ ከተመዘገበው ስራ በተጨማሪነት/በተደራቢነት ሥራ ሰርተው እንደሆነ ይጠየቃሉ:: ባ ለፉት 7 ቀናት ያከናውኑ ከነበረው ሥራ በተጨማሪ/በተደራቢነት ሌላ ሥራ ለሰሩ በአምዱ «አዎን» ተ

መዝግቦ በካርድ ኮለሙ ደግሞ ኮድ 1 የሚሞላ ሲሆን ላልሰሩ ደግሞ "የለም" ኮድ 2 ይሞላል፡፡ ለምሳሌ ፡- አንድ አስተማሪ በዋነኛነት ያከናወነው ሥራ ማስተማር ሆኖ በተጨማሪ/በተደራቢነት ደግሞ ልብስ ስ ፌት ወይም አናጢነት ስራ ሊያከናውን ይችላል፡፡

**ዓምድ 42** <u>ባለፉት 7 ቀናት ይሠሩት ከነበረው ሥራ በተጨማሪ/በተደራቢነት ሌላ ሥራ ለመሥራት ጥረት አድርገው ነበር ወይም ለመስራት ዝግጁ ነበሩ?</u>

የዚህ ዓምድ ጥያቄ የሚቀርብላቸው ዕድሜአቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰብ አባላት ሆነው ባለፉት 7 ቀናት ምርታማ ሥራ የሰሩ (በዓምድ 27 ኮድ 1 ለተሞላላቸው) እና ባለፉት 7 ቀናት በተጨማሪ/በተደራቢነት ሌላ ሥራ ለመስራት ጥረት አድርገው እነደሆነ ወይም ለመስራት ዝግጁ እንደነበሩ ይጠይቃል፡፡ ባለፉት 7 ቀናት ተጨማሪ ሥራ ለመሥራት ጥረት አድርገው ለሚያውቁ ወይም ተጨማሪ ሥራ ቢያገኙ ለመስራት ዝግጁ ለነበሩ በዚህ ዓምድ «አዎን» ተመዝግቦ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 ሲሞላላቸው ጥረት ላላደረጉ ወይም ዝግጁ ላልነበሩ ደግሞ በአምዱ «የለም» ተመዝግቦ በካርድ ኮለሙ ኮድ 2 ይሞላላቸዋል፡፡

**ዓምድ 43** <u>ባለፉት 7 ቀናት ሲሰሩት የነበረውን ሥራ ወይም ሲሰሩበት የነበረውን ድርጅት ለመቀየር ጥረት አድርገው ነበር?</u>

የዚህ ዓምድ ጥያቄ የሚቀርብላቸው ዕድሜአቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰብ አባላት ሆነው ባለፉት 7 ቀናት ምርታማ ሥራ የሰሩ (በዓምድ 27 ኮድ 1 ለተሞላላቸው) ሲሆኑ የሚቀርብላቸው ጥያቄ ደግሞ ባለፉት 7 ቀናት ይሠሩት የነበረውን ሥራ በመተው ሌላ ዓይነት ሥራ ለመስራት ወይም ይሠሩበት የነበረውን ድርጅት ለመቀየር ጥረት አድርገው ያውቁ እነደሆነ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ይሠሩት የነበረውን የሥራ ዓይነት ወይም ድርጅት ለመቀየር ጥረት ሳደረጉ በዓምዱ አዎን ተጽፎ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 የሚሟላ ሲሆን፣ ጥረት ላላደረጉ ደግሞ በዓምዱ የለም ተጽፎ በካርድ ኮለሙ ኮድ 2 ተሞልቶ ለሁሉም መልሶች ወደ ዓምድ 47 ይታለፋል፡፡

**ዓምድ 44** <u>ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት አድርገው ነበር?</u>

በዚህ ዓምድ ሥራ የሌላቸው ነገር ግን ሥራ ቢያገኙ የሚሰሩ ዕድሜአቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰብ አባላት ባለፉት ሦስት ወራት (የጥናቱን ሣምንት ጨምሮ) ሥራ ለማግኘት ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ጥረት ማድረጋቸውን እንጠይቃለን፡፡ የሥራ መፈለጉ ተግባር በሚፈለገው የሥራ ዓይነትና ጊዜ አይወሰንም፡፡ ይህም ማለት የሥራው ዓይነት የግል ሥራ÷ የትርፍ ጊዜ ሥራ÷ ጊዜያዊ ሥራ÷ በወቅት የሚገኝ ወይም በዚህ ጥናት ውስጥ እንደሥራ ከሚቆጠሩት አንዱን የሥራ ዓይነት ለመጀመር ወይም ለመሥራት ጥረት ካደረጉ ሥራ እየፈለጉ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ መረጃ ሰጪው የሚሰጠው መልስ አዎን ከሆነ በተገቢው ካርድ ኮለም ኮድ 1 ይሞላና ወደ ዓምድ 46 ይታለፋል ፤ የለም ከሆነ ደግሞ በካርድ ኮለሙ ኮድ 2 ተሞልቶ የሚቀጥለው ዓምድ ይጠየቃል፡፡ አንድ ሥራ ፈላጊ ሥራ ለማግኘት ጥረት እንዳደረገ የሚቆጠረው ለምሳሌ፡- የሥራ አጥ ካርድ ካወጣ፣ የሥራ ማመልከቻ ለመስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ካስገባ፣ በተለያዩ ቦታዎች የሚለጠፉ የሥራ ማስታወቂያዎችን ካነበበ፣ በጋዜጦች በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሥራ ማስታወቂያዎችን ከተከታተለ፣ በዘመድ በጓደኛ ክትትል ካደረገ፣ ሥራ ያለባቸውን ቦታዎች እየተዘዋወረ ከጠየቀ፣ የግል ሥራ ለመጀመር እየሞከረ ከሆነ እና የመሳሰሉትን የፈፀመ ከሆነ ነው፡፡

**ዓምድ 45** <u>ለምንድነው ለመሥራት ወይም ሥራ ለመጀመር ጥረት ያላደረጉት?</u>

በዓምድ 44 ኮድ 2 ለተሞላላቸው ማለትም ባለፉት 3 ወራት ሥራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ምንም ጥረት ያላደረጉትን ዕድሜአቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰብ አባላት በዚህ ዓምድ ጥረት ያላደረጉበትን ምክንያት በመጠየቅ በዓምዱ ግርጌ ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ውስጥ ዋነኛውን ምክንያት የያዘው ኮድ በዓምዱ ስር ባሉት ካርድ ኮለሞች ይመዘገባል/ይሞላል፡፡ የኮዶቹም ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**01** =

<u>በሕመም፣ በአካል ጉዳት፡-</u> ባይታመሙ ወይም አካል ጉዳት ባይደርስባቸው ኖሮ ባለፉት ሶስት ወራት ስራ ለማግኘት ወይም ለመጀመር ጥረት ያደርጉ የነበሩ፣

**02** =

<u>በግል ወይም በቤተሰብ ጉዳይ፡-</u> በራስ ወይም በቤተሰብ ምክንያት ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉ (ከታች ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ)

**03** =

<u>የቤት ውስጥ ሥራ/ኃላፊነት፡-</u> ስራ ያልፈለጉት ወይም ጥረት ያላደረጉት በቤት ውስጥ ኃላፊነት ስላለባቸው፣ ለምሳሌ በቤት እመቤትነትና ልጅ አሳዳጊ ስለሆኑ፤

04 =

<u>እርጅና/ጡረታ</u>:- በእርጅና ወይም ዕድሜ በመግፋት እና ጡረታ በመውጣታቸው ምክን ያት ባለፉት ሶስት ወራት ሥራ ያልፈለጉ፡

05 =

<u>በትምህርት/ስልጠና</u> :- በትምህርት/ስልጠና ላይ በመሆናቸው ምክንያት ባለፉት ሶስት ወ ራት ስራ ለመፈለግ ያልሞከሩ፣

06 =

<u>ሥራ አግኝቼ (የግል ሥራ) ለመጀመር በቀጠሮ ላይ ነኝ</u>:- የራሳቸውን የግል ሥራ ወ ይም በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥረው ሥራ ለመጀመር በሂደት ላይ ያሉ፣

07 =

<u>የቀድሞ ሥራዬ ለመመለስ እየተጠባበቅኩ ነኝ</u>:- ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት ወ ደ ቀድሞ ሥራቸው ለመመለስ ተስፋ ስላላቸውና እየተጠባበቁ ስለሆነ፣

08 =

<u>ሥራ አገኛለሁ ብዬ ስለማላስብ</u>:- ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ሥራ ለማግኘት ሞክረው ሳይሳካላቸው ተስፋ የቆረጡ እና በሌሎችም ምክንያቶች ባለፉት ሶስት ወራት ስራ ያልፈለጉት ከሥ ራ ዕድሉ መጥበብ የተነሳ ስራ አላገኝም በማለት ተስፋ የቆረጡትን ይጨምራል፣

09 =

<u>የግል ሥራ ለመጀመር የጥሬ ዕቃ፣ የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ እጥረት ይኖራል ብዬ ስለማስብ</u>:- የግል ሥራ ለመጀመር ለሚያስቡ ሰዎች የግል ሥራ ያልጀመሩት በጥሬ/ገንዘብ ወይ ም በቁሳቁስ እጥረት ይኖራል ብለው የሚያስቡ፣

10 =

<u>ልጅ ስለሆነ/ች</u>:- ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት ዕድሜዬ ገና ለስራ ብቁ አይደለም ብለው ስለሚያስቡ፣

11 = <u>ሌላ(ይገለፅ)</u>:- ከላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውጭ ሥራ ለማግኘት ጥረት ያላደረጉት፣

<u>ማስታወሻ</u>:- ኮድ 02 የሚሞላላቸው ከትምህርት፣ ከቤት ውስጥ ሥራ፣ ወይም ከመታመም የተለየ ሌላ የግል ወ ይም የቤተሰብ ጉዳይ <u>ለምሳሌ</u>:- በሐዘን፣ ቤት በመጠበቅ፣ ዘመድ በማስታመም የመሳሰሉ በምርታማ ተግባር ውስጥ በማይካተቱ ሥራዎች ላይ የነበሩትን ነው።

## ዓምድ 46 <u>ባለፉት 7 ቀናት ሥራ ካልነበረዎት በሚቀጥለው አንድ ወር ሥራ ቢገኝልዎ ለመስራት ዝግጁ ነዎት</u>?

በዚህ ዓምድ ጥያቄ የምናቀርብላቸው "ስራ ያልሰሩ" ዕድሜአቸው 10 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ የቤተሰ ብ አባላት ነው። ይህም ማለት በጥናቱ ወቅት በቅጥርም ሆነ በግል ምንም ዓይነት ሥራ ያልሰሩ እና ወ ደፊት የሚጀምሩት የተዘጋጀ ሥራ የሌላቸውን ማለት ነው። ይህ ጥያቄ ሥራ እያላቸው በጥናቱ ሳምን ት በተለያየ ምክንያት ሥራ ያልሰሩትን አይመለከትም።

መረጃ ሰጪዎች የጥናቱን ሣምንት ጨምሮ በአራት ሳምንታት ውስጥ "ስራ ቢያገኙ" እንደሚሰሩ ይጠየቃ ሉ። የሚሰጡት መልስ በተገቢው ካርድ ኮለም ይመዘገባል። ለዚህ ጥያቄ አዎን ለመለሱ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1፣ የለም ለመለሱ ደግሞ ኮድ 2 ይሞላላቸዋል። መረጃ ሰጪው ከተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውጭ/በ ኋላ መሥራት እንደሚችሉ እንኳን ቢናገሩ የለም የሚለው ኮድ 2 ነው የሚሞላው። <u>ለምሳሌ</u>: ተማሪዎ ች ትምህርቴን እንደጨረስኩ መጀመር እችላለሁ ቢሉ ወይም አንድ ጉዳይ ያለበት ሰው ጉዳዩን እንደጨ ረስኩ መሥራት እችላለሁ ቢል በዚህ ጥያቄ በተጠቀሰው ጊዜ ሥራውን መጀመር የማይችሉ ከሆነ በዓም ዱ ኮድ 2 ይሞላላቸዋል።

# ክፍል 4 ያለፉት 12 ወራት የሥራ ሁኔታ

## ዓምድ 47

<u>ለመረጃ ሰብሳቢ :- ለመልስ ሰጭው የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንድ በአንድ አቅርበህ/ሽ በ ያንስ በአንዱ የሥራ ዓይነት ከተሰማሩ በካርድ ኮለሙ ኮድ «1» ይሞላል። በአንዳቸውም በአንዱ ም ሥራ እንኳን ካልተሰማሩ በካርድ ኮለሙ ኮድ «2» ይሞላል።</u>

በዚህ ዓምድ እያንዳንዱ ዕድሜው 10 ዓመትና በላይ የሆነ የቤተሰቡ አባል ከጥናቱ ቀን በፊት ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በቅጥር/በክፍያ ወይም ነግዶ ለማትረፍ ወይም በግብርና ወይም በሌላ የማምረት ተግባር ወይም አገልግሎት በመስጠት ተግባር ተሰማርቶ እንደሆነ ይጠየቃል። በዚህ ጥያቄ ለማወቅ የተፈለገው የቤተሰብ አባላቱ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ለጥቂት ጊዜ እንኳን ቢሆን በምርታማ ተግባር ላይ መሠማራት አለመሠማራታቸውን ነው። ዓምዱ ሰዎች ሊሰማሩ የሚችሉባቸውን 8 ዋና ዋና የሥራ ዘርፎችን የያዘ ሲሆን እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በነኚህ የሥራ ዘርፎች ተሰማርቶ እንደሆነ ለማወቅ ጥያቄዎች ከመጀመሪያው ጀምሮ አንድ በአንድ ይቀርቡለታል። ከተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች በአንዱ እንኳን ከተሳተፈ በምርታማ ተግባር እንደተሰማራ ተቆጥሮ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 ይሞላል። ነገር ግን ከተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች ውስጥ በአንዱም እንኳ አልተሰማራሁም ካለ ኮድ 2 ይሞላና ወደ ዓምድ 51 ይታለፋል። በመጠይቁ ላይ የሠፈረው ጥያቄ እንዳለ ለመልስ ሰጪው መነበብ ይኖርበታል። ይህን ዓምድ ለመሙላት በዓምዱ ስር ስለተዘረዘሩት ስምንት ዋና ዋና የሥራ ዘርፎች ዝርዝር ማብራሪያና የምርታማ ሥራን ትርጉም በሚመለከት ለዓምድ 24 የተሰጠውን ማብራሪያ ተመልከት/ቺ።

## ዓምድ 48 <u>(በዓምድ 47 ኮድ 1 ለተሞላላቸው) በሁሉም ምርታማ ሥራዎችዎ ባለፉት 12 ወራት በጠቅላላው ለምን ያህል ወራት ነበር የተሰማሩት</u>?

በዚህ ዓምድ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ምርታማ ስራ ሰርተው ለሚያውቁ (በዓምድ 47 ኮድ 1 ለተሞላላቸው) በሙሉ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በአከናወኗቸው ምርታማ ስራዎች በጠቅላላው ለምን ያህል ወራት በሥራ ተሰማርተው እንደነበር ተጠይቆ መልስ ሰጪው በሚሰጡት መልስ መሠረት ከሚከተሉት ኮዶች መካከል ተስማሚው ኮድ በካርድ ካለሙ ይሞላል።

<u>ማስታወሻ</u>:- አንድ ሰው አንድ ወር በምርታማ ተግባር እንደተሠማራ የሚቆጠረው በዓመት ውስጥ በድምሩ 4 ሣምንታት በምርታማ ተግባር ከተሳተፈ ብቻ ነው። አንድ ሰው አንድ ሣምንት ስራ የሚባለው ደግሞ በዚያ ሣምንት ውስጥ ባሉት ቀናት በድምሩ ቢያንስ ለአራት ሰዓት በምርታማ ተግባር ከተሳተፈ ብቻ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል።

1. **ከ1 ወር በታች:-**
   ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በአከናወኗቸው ምርታማ ስራዎች ከ1 ወር ላነሰ ጊዜ ተሰማርተው ለነበሩ
2. **ከ1 እስከ 3 ወር:-**
   ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በአከናወኗቸው ምርታማ ስራዎች ከ1 እስከ 3 ወራት ተሰማርተው ለነበሩ
3. **ከ4 እስከ 5 ወር:-**
   ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በአከናወኗቸው ምርታማ ስራዎች ከ4 እስከ 5 ወራት ተሰማርተው ለነበሩ
4. **ከ6 እስከ 9 ወር:-**
   ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በአከናወኗቸው ምርታማ ስራዎች ከ6 እስከ 9 ወራት ተሰማርተው ለነበሩ
5. **ከ10 እስከ 12 ወር:-**
   ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በአከናወኗቸው ምርታማ ስራዎች ከ10 እስከ 12 ወራት ተሰማርተው ለነበሩ

## ዓምድ 49 <u>ባለፉት 12 ወራት ዋነኛ የሥራዎ ዓይነት ምንድነው</u>?

በዚህ ዓምድ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በምርታማ ተግባር ላይ ሲሳተፉ የነበሩ ሰዎች /በዓምድ 47 ኮድ 1 የተሞላላቸው/ ስለ ዋነኛ ሥራቸው ዓይነት ይጠየቃሉ። ከአንድ በላይ ሥራ ለነበራቸው አባላት የሚጠየቅላቸው ስለ ዋናው ሥራቸው ማለትም ከሌሎቹ የበለጠ ጊዜ የወሰደውን/የሚወስደውን ይሆናል። የሥራ ዓይነትም የሚገለጸው በአብዛኛው ጊዜ ግለሰቡ ምን በማድረግ እንደሚውል በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ በዝርዝር በመመዝገብ ይሆናል። የሥራ ዓይነት አሞላልን በሚመለከት ላለፉት 7 ቀናት በዓምድ 29 ስር የተሰጠውን ዝርዝር ማብራሪያ ተመልከት/ቺ።

## ዓምድ 50 <u>ዋነኛ ሥራዎን ያከናወኑበት ድርጅት/የሥራ ዘርፍ ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድነው</u>?

ይህን ዓምድ ለመሙላት ግለሰቡ የት ወይም በየትኛው ድርጅት እንደሚሠሩ በመጠየቅ ሲሆን ለዝርዝር አሞላሉ የዓምድ 31ን የአሞላል መመሪያ ተመልከት/ቺ። በዚህ ዓምድ የሚሞላው መረጃ ያለፉት 12 ወራትን በሚመለከት ሲሆን በዓምድ 31 የሚሞላው ግን ያለፉት 7 ቀናትን በሚመለከት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

<u>ማስታወሻ</u>:- የዓምድ 51 ጥያቄ የሚመለከታቸው ባለፉት 12 ወራት ምንም ምርታማ ስራ ያልሠሩትን (በዓምድ 47 ኮድ 2 ለተሞላላቸው) ስለሆነ በዚህ ዓምድ መረጃ የተሞላላቸው በሙሉ ወደ ዓምድ 52 ያልፋሉ።

ዓምድ 51 ***ሥራ ያልሰሩበት ዋነኛ ምክንያት ምን ነበር? (በዓምድ 47 ኮድ 2 ለተሞላላቸው)***

በዚህ ዓምድ ባለፉት 12 ወራት በማንኛውም ምርታማ ሥራ/ተግባር ሳልተሰማሩ ( በዓምድ 47 ኮድ 2 የተሞላላቸው) ስራ ያልሰሩበት ምክንያት ተጠይቆ ከሚከተሉት ኮዶች ውስጥ አንዱ ይሞላላቸዋል::

0 =

***ሥራ አጥ/ፈላጊ:-*** ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ሥራ ያልሰሩና ስራ በመፈለግ ላይ የነበሩ ወይም ሥራ ቢያገኙ ሊሠሩ ዝግጁ የነበሩ፣

1

= **ሕመም (አካል ጉዳት):-** የአካል ጉዳት ደርሶባቸው ወይም በሕመም ምክንያት ባለፉት 12 ወራት ምንም ሥራ ያልሰሩ፣

2

= **ልጅ (ለሥራ ያልደረሱ):-** እነዚህ ግለሰቦች ዕድሜአቸው 5 ዓመትና በላይ ሲሆኑ ባለፉት 12 ወራ ት በምርታማ ሥራ ያልተሰማሩበትን ምክንያት ሲገልፁ "ልጅ" በመሆናቸው የሚል መልስ የሚሰጡ ና ቸው:: ዕድሜአቸው 15 ዓመትና በላይ የሆኑ ይህ ኮድ ሊሰጣቸው አይችልም:: በመማር ላይ ያሉ ልጆ ች የሚሞላላቸው ኮድ 6 እንጂ ልጅ ተብሎ ኮድ 2 አይደለም::

3

= **ጡረተኛ/እርጅና:-** ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ሳይሠሩ በቤት አበል፣ ባጠራቀሙት ገንዘብ ፣ በቤት ኪራይ ገቢ ወይም በቤተሰብ እርዳታ የሚተዳደሩ ናቸው:: በጡረታ ወይም በእርጅና ምክንያት ሥራ ያልሠሩ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ::

4 = **ሴተኛ አዳሪ:-** ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ በሴተኛ አዳሪነት ሲተዳደሩ የነበሩ፣

5 =

**ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ብቻ:-** እነዚህ ግለሰቦች የገንዘብ ወይም የዓይነት ክፍያ ሳያገኙ ምግብ ማብሰል፣ ልብስ ማጠብ የመሳሰሉትን በቤት ውስጥ የሚሠሩ ሥራዎችን በመስራት ያሳለፉ ናቸው:: የቤ ት እመቤት ሴቶች በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ::

6 =

**ተማሪ:-** እነዚህ ግለሰቦች ቀን ቀን ትምህርት በመከታተላቸው የተነሳ ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊ ዜያቸውን ምርታማ ሥራ ያልሰሩ፣

7 = **መስራት ባለመፈለግ:-** ባለፉት 12 ወራት ምንም ምርታማ ሥራ ያልሠሩ ሆነው ያልሰሩበትን ምክንያት ሲጠየቁ «ለመስራት ፍላጎት ስላልነበረኝ» ብለው ለሚመልሱ ይህ ኮድ ይሞላል::

8 =

**ሌላ** ከላይ ከተዘረዘሩት በተለየ ምክንያት ሥራ ያልሠሩ **ለምሳሌ:-** በቤት ሠራተኛነት፣ በተለማማጅነት ልመና፣ ...ወዘተ. ከላይ ከኮድ 1 እስከ 7 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውጪ መልስ ለሰጡ መልሱ በዓምዱ ተሞልቶ ኮድ 8 በካርድ ኮለሙ ይሞላል::

ዓምድ 52 **ለመረጃ ሰብሳቢ ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት ለሆኑ የቤተሰብ አባላት ኮድ 1፣ ዕድሜአ ቸው ከ5-17 ዓመት ውጪ ለሆኑ ደግሞ ኮድ 2 በመሙላት ኮድ 1 ለተሞላላቸው ሁሉ የመስመር ተራ ቁጥራቸውን ክበብ/ቢ::**

በዚህ ዓምድ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በዓምድ 16 የተሞላውን ዕድሜ መሠረት በማድረግ ዕድሜአቸ ው ከ5-17 ዓመት ለሆናቸው የቤተሰብ አባላት በሙሉ በካርድ ኮለሙ ኮድ 1 በመሙላት ከዓምዱ በስተ ቀኝ የተሞላው የመስመር ተራ ቁጥራቸው ይከበባል:: ዕድሜአቸው ከ5 ዓመት በታችና ከ17 ዓመት በላ ይ ለሆናቸው ደግሞ ኮድ 2 የሚሞላ ሲሆን የመስመር ተራ ቁጥራቸው አይከበብም:: የዓምዱ ዋና ዓላ ማ ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት የሆኑ የቤተሰብ አባላትን በመለየት የመስመር ተራ ቁጥራቸውን ወደ ቀ ጣዮች ቅጾች (ቅጽ 2 እና 3) ለማስተላለፍ ነው::

# ምዕራፍ 4

## በቅጽ 1 የክፍል 5 (የቤተሰብ መጠይቅ) አሞላል መምሪያ

የቤተሰብ መጠይቅ ለጥናቱ የተመረጠውን ቤተሰብና ቤተሰቡ የሚኖርበትን ቤት መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ሲሆን መረጃውንም የሚያስሞላው የቤተሰብ ኃላፊ ወይም ሌላ አዋቂ የሆነ የቤተሰብ አባል ሊሆን ይችላል። የቤተሰብ መጠይቅ ለመልስ ሰጪዎች የሚቀርበው ሁሉም መጠይቆች ከተጠናቀቁ በኋላ መጨረሻ ላይ ነው። ይህም ማለት ቅጽ 1 የቤተሰብ አባላት መጠይቅ (ከክፍል 1 እስከ ክፍል 4)፣ ቅጽ 2 እና ቅጽ 3 ከተጠናቀቀ በኋላ ማለት ነው። ነገር ግን ቅጽ 3 የሚሞላላቸው ልጆች እቤት ካልተገኙ መረጃ ሰብሳቢው ልጆቹን የሚያገኝበትን ጊዜ ቀጠሮ ከሰጠ በኋላ ከቤተሰቡ ተሰናብቶ ከመውጣቱ በፊት የቤተሰብ መጠይቁን ይሞላል።

### ዓምድ 53-58 <u>የቤተሰቡ የፍልሰት ሁኔታ</u>

በነዚህ ዓምዶች ቤተሰቡ መደበኛ መኖሪያ ቦታውን ለውጦ ያውቅ እንደሆነ፣ ከለወጠም በጥናቱ ወቅት ወደሚኖርበት ቦታ ከመምጣቱ በፊት በየትኛው ክልል፣ ዞን እና ከተማ/ገጠር ይኖር እንደነበር ይጠየቃል። በተጨማሪም በጥናቱ ወቅት ወደሚኖርበት ቦታ ለመምጣት ያበቃውን ዋነኛ ምክንያትና በዚያ ቦታ ያለ ማቋረጥ ለስንት ዓመት እንደኖረ ይጠይቃል።

### ዓምድ 53 <u>ይህ ቤተሰብ ከተመሰረተ ጀምሮ ከዚህ ከተማ ወይም ወረዳ ገጠር ውጪ በመደበኛነት ኖሮ ያውቃል</u>?

በዚህ ጥያቄ ቤተሰቡ ከተመሰረተ ጀምሮ ጥናቱ እስከሚካሄድበት ወቅት ድረስ መደበኛ መኖሪያ ቦታውን ለውጦ ያውቅ እንደሆነ ይጠየቃል። መደበኛ መኖሪያ ቦታ ቤተሰቡ ያለማቋረጥ ቢያንስ ለ 6 ወር የኖረበት ቦታ ወይም ለዘለቄታው ለመኖር አቅዶ የቆየበት ቦታ ማለት ነው። ቤተሰቡ ዘመድ ለመጠየቅ፣ ለጉብኝት እና ለመሳሰሉት ጉዳዮች ከ 6 ወር ላነሰ ጊዜ የቆየበት ቦታ እንደመደበኛ መኖሪያ አይቆጠርም። የቤተሰብ መንቀሳቀስ ሲባል በቀጥታ የሚያያዘው ከቤተሰቡ ሃላፊ ጋር መሆኑ መታወቅ አለበት። አንድ የቤተሰብ ሃላፊ ያልሆነ መደበኛ የቤተሰብ አባል መኖሪያውን ቢለውጥ ቤተሰቡ የመኖሪያ አድራሻውን እንደለወጠ አይቆጠርም ማለት ነው። ስለዚህ ከላይ እንደተገለፀው የቤተሰብ እንቅስቃሴ ሲባል ከኃላፊው እንቅስቃሴ ጋር የሚገናዘብ ነው።

ቤተሰቡ ከተመሰረተ ጀምሮ መደበኛ መኖሪያ ቦታውን ለውጧል የሚባለው፣

ሀ. <u>በገጠር ለሚኖር ቤተሰብ፡-</u> ቤተሰቡ ከተመሰረተ ጀምሮ በጥናቱ ወቅት ከሚኖርበት ወረዳ ውጭ በሚገኝ ገ/ማህበር ወይም በማንኛውም ከተማ ውስጥ በመደበኛነት ይኖር ከነበረ ሲሆን፣

ለ. <u>በከተማ ለሚኖር ቤተሰብ፡-</u> ቤተሰቡ ከተመሰረተ ጀምሮ በጥናቱ ወቅት ከሚኖርበት ከተማ ውጭ ሌላ ቦታ በመደበኛነት ይኖር ከነበረ ነው።

በዚህ መሠረት ቤተሰቡ ከተመሰረተ ጀምሮ መደበኛ መኖሪያ ቦታውን ለውጦ የሚያውቅ ከሆነ ኮድ 1 ከተከበበ በኋላ በካርድ ኮለሙ ይሞላል። መደበኛ መኖሪያ ቦታውን ለውጦ ለማያውቅ ቤተሰብ ኮድ 2 ይሞላና ወደ ዓምድ 59 ይታለፋል። የቤተሰቡን ኃላፊ ጨምሮ የቤተሰቡ አባላት በሙሉ ወይም በከፊል መደበኛ መኖሪያ ቦታቸውን ለውጠው የሚያውቁ ከሆነ ቤተሰቡ መደበኛ መኖሪያ ቦታውን እንደለወጠ ይቆጠራል። ነገር ግን የቤተሰቡን ኃላፊ ሳይጨምር አንድ ወይም ከአንድ በላይ የቤተሰቡ አባላት መደበኛ መኖሪያ ቦታቸውን ቢለውጡ ግለሰቦች እንጂ ቤተሰቡ መደበኛ መኖሪያ ቦታውን እንደለወጠ አይቆጠርም።

### ዓምድ 54 <u>ቤተሰቡ ወደ እዚህ ቦታ ከመምጣቱ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ በየትኛው ክልል ይኖር ነበር</u>?

ቤተሰቡ ወደ እዚህ ቦታ ከመምጣቱ በፊት የኖርበት የነበረው ክልል ተጠይቆ በሚከተሉት ኮዶች አማካይነት ይሞላል።

| | |
|---|---|
| 01= ትግራይ ክልል | 07= ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል |
| 02= አፋር ክልል | 12= ጋምቤላ ክልል |
| 03= አማራ ክልል | 13= ሐረሪ ክልል |
| 04= ኦሮሚያ ክልል | 14= አዲስ አበባ |
| 05= ሶማሌ ክልል | 15= ድሬዳዋ |

06= ቤንሻንጉል-ጉምዝ ክልል        16= ከኢትዮጵያ ውጭ (የአገሩ ስም ይሞላል)

**ዓምድ 55** <u>ቤተሰቡ ወደ እዚህ ቦታ ከመምጣቱ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ በየትኛው ዞን ይኖር ነበር?</u>

ቤተሰቡ ወደ እዚህ ቦታ ከመምጣቱ በፊት ይኖርበት የነበረው ዞን ተጠይቆ የዞኑ ኮድ በካርድ ኮለሙ ይሞላል:: የዞኖች ዝርዝርና ኮድ በዚህ መመሪያ <u>በዕዝል 2</u> ተያይዞ ስለሚገኝ ለዚህ ዓምድ የሚሰጡትን መልሶች በትክክል መሙላት ያስፈልጋል::

**ዓምድ 56** <u>ቤተሰቡ ወደ እዚህ ቦታ ከመምጣቱ በፊት ይኖርበት የነበረው ቦታ ከተማ ነው ወይስ ገጠር?</u>

ቤተሰቡ አሁን ወደሚኖርበት ቦታ ከመምጣቱ በፊት ይኖርበት የነበረው ቦታ ከተማ ከሆነ ኮድ 1 ተከቦ የከተማው ስም ምን እንደሆነ ተጠይቆ ይሞላል:: ገጠር ከሆነ ኮድ 2 ይከበብና ይኸው ኮድ በካርድ ኮለሙ ይሞላል::

**ዓምድ 57** <u>ቤተሰቡን አሁን ወደሚኖሩበት የመኖሪያ ቦታ ለመምጣት ያበቃው ዋነኛ ምክንያት ምንድነው?</u>

ቤተሰቡ የቀድሞ መደበኛ መኖሪያ ቦታውን ለውጦ በጥናቱ ወቅት ወደሚኖርበት ቦታ ለመምጣት ያበቃው ዋነኛ ምክንያት ተጠይቆ ከዚህ በታች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ተስማሚውን መልስ የያዘው ኮድ በካርድ ኮለሙ ይሞላል:: አማራጭ መልሶችና ኮዶቻቸው የሚከተሉት ናቸው::

| | |
|---|---|
| 1= በትምህርት | 5= ሥራ በማግኘት/በዝውውር |
| 2= የጋብቻ መመስረት | 6= መፈናቀል (ጦርነት፣ ድርቅ ወዘተ...) |
| 3= የጋብቻ መፍረስ | 7= የመሬት ችግር |
| 4= ሥራ ፍለጋ | 8= ሌላ (ይገለጽ)________ |

**ዓምድ 58** <u>ቤተሰቡ አሁን በሚኖርበት የመኖሪያ ቦታ ያለማቋረጥ ለምን ያህል ዓመት ቆይቷል?</u>

መደበኛ መኖሪያ ቦታውን ለውጦ ለሚያውቅ (በዓምድ 53 «አዎን»/ ኮድ 1 ለተሞላለት) ቤተሰብ ጥናቱ በሚካሄድበት ቦታ ያለማቋረጥ ለስንት ዓመት እንደቆየ ተጠይቆ በዓምዱ ስር ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ተስማሚው ኮድ ተከቦ በካርድ ኮለሙ ይሞላል:: ቤተሰቡ ያለማቋረጥ የኖረበት ጊዜ ተብሎ የሚወሰደው ወደ ጥናቱ ቦታ መጥቶ በመደበኛነት መኖር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ጥናቱ ቀን ያለውን ሙሉ ዓመት ነው:: ኮዶቹና አማራጭ መልሶቹ የሚከተሉት ናቸው::

| | |
|---|---|
| 0= ከ1 ዓመት በታች | 4= 4 ዓመት |
| 1= 1 ዓመት | 5= 5-6 ዓመት |
| 2= 2 ዓመት | 6= 7-9 ዓመት |
| 3= 3 ዓመት | 7= 10 ዓመትና በላይ |

**ዓምድ 59** <u>የቤቱ ይዞታ ምንድን ነው?</u>

የቤቱ ይዞታ ማለት የቤቱ ባለቤት ማን እንደሆነ የሚያመለክት ነው:: ስለዚህ የቤቱ ይዞታ በውስጡ ከሚኖሩት የቤተሰብ አባላት የአንዱ የግል ንብረት ከሆነ ከነዋሪዎቹ መካከል ማንም ኪራይ የማይከፍልበት መሆን አለበት:: ቤቱ የኪራይ ከሆነ አከራዩ ቀበሌ ወይም የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት ወይም ግለሰብ ሊሆን ይችላል:: ይዞታቸው ከኪራይ ነፃ የሚባሉ ቤቶች በቀበሌ፣ በመንግሥት ወይም በአሠሪ ድርጅት/ግለሰብ ከኪራይ ነፃ ቤተሰቡ እንዲኖሩበት የተሰጠ ወይም በዘመድ፣ በጓደኛ፣ ወዘተ. በአደራ መልክ የተሰጡትን ሁሉ ያጠቃልላል:: እንዲሁም ነዋሪው ከግለሰብ ተከራይቶ የሚኖር ከሆነ «ከግለሰብ በመከራይት» የሚለው ተከቦ ኮድ 5 ይሞላል::

ስለዚህ በዚህ ዓምድ የቤቱን ይዞታ ሁኔታ በመጠየቅ ከዚህ ቀጥሎ ከተሰጡት የኮዶች ዝርዝር ውስጥ ትክክለኛውን ኮድ በማክበብ ይህ ኮድ በካርድ ኮለሙ ውስጥ ይሞላል:: ከኮድ 1-4 የተሞላላቸው ወደ ዓምድ 61 እንዲያልፉ ይደረጋል::

| | |
|---|---|
| 1= በግል ይዞታ (በነዋሪዎች ባለቤትነት) | 4= በድጎማ - ከአሰሪ |
| 2= በነፃ - ከአሰሪ ድርጅት/ግለሰብ | 5= ከግለሰብ በመከራየት |
| 3= ከኪራይ ነፃ - ከሌላ ድርጅት/ሌላ ግለሰብ | 6= ከመንግሥት አከራይ ድርጅት (ቀበሌ/ኪራይ ቤቶች) |

**ዓምድ 60** <u>ቤቱ የኪራይ ከሆነ በወር የሚከፈለው ኪራይ ስንት ብር ነው?</u>

በዓምድ 59 ኮድ 5 ወይም ኮድ 6 ለተሞላላቸው (ከግለሰብ፣ ከመንግስት ወይም ከአከራይ ድርጅት ተከራይቶት ለሚኖር ቤተሰብ) ለመኖሪያ ቤቱ ኪራይ ለወር ምን ያህል ብር እንደሚከፈል ተጠይቆ የብሩ መጠን በካርድ ኮለሞች ይሞላል:: የኪራዩ መጠን ወደ ሙሉ ብር ተጠጋግቶ መሞላት ይኖርበታል::

## ዓምድ 61 የመኖሪያ ቤቱ ግድግዳ የተሠራው ከምንድነው?

አብዛኛው የቤቱ ግድግዳ የተሠራበት የዕቃ ዓይነት ተጠይቆ መልሱ ከተከበበ በኋላ በካርድ ኮለሙ ኮዱ ይመዘገባል። መልሱ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የዕቃ ዓይነቶች የተለየ ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ አብዛኛው የቤቱ ግርግዳ የተሠራው ከምን እንደሆነ ተጠይቆ "ሌላ" በሚለው ኮድ ስር ይመዘገባል።

| | |
|---|---|
| 1= ከእንጨትና ከጭቃ | 5= ብሎኬትና ሲሚንቶ |
| 2= እንጨትና ሣር | 6=ሸክላና ሲሚንቶ |
| 3= ከድንጋይና ጭቃ | 7= ቀርከኸ/ሸንበቆ |
| 4= ድንጋይና ሲሚንቶ | 8= ሌላ (ይገለፅ)_______ |

## ዓምድ 62 የመኖሪያ ቤቱ ጣራ የተሠራው ከምንድነው?

አብዛኛው የቤቱ ጣራ የተሠራበት የዕቃ ዓይነት ተጠይቆ መልሱ ከተከበበ በኋላ በካርድ ኮለሙ ኮዱ ይመዘገባል። መልሱ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የዕቃ ዓይነቶች የተለየ ከሆነ በተሰጠው ክፍት ቦታ አብዛኛው የቤቱ ጣራ የተሠራው ከምን እንደሆነ ተጠይቆ "ሌላ" በሚለው ኮድ ስር ይመዘገባል።

| | |
|---|---|
| 1= ቆርቆሮ | 4= እንጨትና አፈር |
| 2= ኮንክሪት/ሲሚንቶ | 5= ቀርከሃ/ሸንበቆ |
| 3= ሣር | 6= ሌላ /ይገለጽ/______ |

## ዓምድ 63 የመኖሪያ ቤቱ ስንት ክፍሎች አሉት?

«ክፍል» ሲባል ዙሪያውን ከወለል እስከ ኮርኒሱ ወይም ጣሪያው ድረስ አንድ አዋቂ ሰው ለማስቆም በሚደርስ ግድግዳ የተከበበና ቢያንስ አራት ካሬ ሜትር የሆነ ቦታ ሆኖ ስፋቱ ለአንድ አዋቂ ሰው አልጋ ለማዘርጋት የሚበቃ ሥፍራ ያለው ነው። ስለዚህ ጠቅላላ የቤቱ ክፍሎች የእንግዳ መቀበያ ሳሎን የምግብ ፣ የመኝታ፣ የወጥ ቤት፣ የሠራተኛ መኝታና ለሌላ ሥራ የሚያገለግሉ ክፍሎችንም ያጠቃልላል። ነገር ግን የመታጠቢያና የመፀዳጃ ክፍል፣ የመተላለፊያ ኮሪደሮችና በረንዳዎች እንደ ክፍል አይቆጠሩም። የክፍሎች ብዛት ከሚከተሉት የኮድ ዝርዝሮች ውስጥ ትክክለኛውን ኮድ በመክበብ ይኸው ኮድ በካርድ ኮለሙ ውስጥ ይሞላል።

| | |
|---|---|
| 1= አንድ ክፍል | 3= ሦስት ክፍል |
| 2= ሁለት ክፍል | 4= አራት ክፍሎችና በላይ |

## ዓምድ 64 የመኖሪያ ቤቱ ምን ዓይነት መፀዳጃ አለው?

ቤቱ ምን ዓይነት መፀዳጃ እንዳለው በመጠየቅ ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ኮዶች ውስጥ በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በዓምድ 64 ባለው ካርድ ኮለም ይሞላል። ቤቱ የጉድጓድ መፀዳጃና በውኃ የሚወርድ መፀዳጃ ካለው በውኃ የሚወርድ መፀዳጃ ተመርጦ ይኸው በዓምዱ ይመዘገባል። በመበላሸቱ (በመፍረሱ ወይም በመሙላቱ) የተነሳ ጥቅም የማይሰጥ መፀዳጃ ካለውና ይኸው ሊጠገን የማይችል ከሆነ ቤቱ መፀዳጃ ቤት እንደሌለው ይቆጠራል።

| | |
|---|---|
| 1= መፀዳጃ የለውም | 4= የጉድጓድ መፀዳጃ የግል |
| 2= በውኃ የሚወርድ መፀዳጃ የግል | 5= የጉድጓድ መፀዳጃ የጋራ |
| 3= በውኃ የሚወርድ መፀዳጃ የጋራ | |

## ዓምድ 65 ቤቱ ምን ዓይነት ማድ ቤት አለው?

አንድ ቤት አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ክፍሎች ሙሉ በሙሉ ለምግብ ማብሰያ የሚያገለግሉ ሊኖሩት ይችላል። ክፍሉ ሰዎች ቢተኙበትም አብዛኛውን ጊዜ ለምግብ ማብሰያ እስከዋለ ድረስ እንደ ማድ ቤት ይቆጠራል። ማድቤቱን በቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ብቻ የሚጠቀሙበት ወይም ከሌላ ቤት የሚኖሩ ቤተሰቦች እየመጡ በጋራ የሚጠቀሙበት ሊሆን ይችላል።

**የግል ማድቤት፡-** አንድ ማድቤት የግል ነው የሚባለው በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ቤተሰቦች ሲጠቀሙበት ብቻ ነው።

**የጋራ ማድቤት፡-** አንድ ማድቤት የጋራ ነው የሚባለው ከቤት ውጭ ከሌላ ቤት የሚኖሩ ቤተሰቦች ማድ ቤት ከአለው ቤተሰብ ጋር በጋራ ሲጠቀሙበት ነው።

**ማድቤት የለውም፡-** አንድ ቤት ማድቤት የለውም የሚባለው ቤተሰቡ ለምግብ ማብሰያ ወይም ማዘጋጃ የተ መደበ ክፍል የሌለው በመሆኑ ምግብ የሚዘጋጀው ለሌላ አገልግሎት በሚውሉ ክፍሎች ወይም በሜዳ ላ ይ ሲሆን ነው፡፡ መኖሪያ ቤቶች እንደሁኔታው ዘመናዊ ወይም ባህላዊ ማድቤት ሊኖራቸው ወይም ላይኖ ራቸው ይችላል፡፡

**ዘመናዊ ማድቤት፡-** ቢያንስ የቧንቧ ውኃና የዕቃ ማጠቢያ (ሲንክ) ያለው ሆኖ ለምግብ ማብሰያ ከኤሌክትሪክ ምድጃ፣ ከቡታ ጋዝ ምድጃ፣ የላምባ ምድጃ ወይም ዘመናዊ የሆነ ከእንጨት ወይም ከከሰል የሚሠራ ም ድጃ ፥ … ወዘተ. አንዱ ወይም ከዚያ በላይ ያለው ዘመናዊ ማድ ቤት ይባላል፡፡

**ባህላዊ ማድቤት፡-** የቧንቧ ውኃና የዕቃ ማጠቢያ (ሲንክ) የሌለው ወይም ዘመናዊ ባልሆነ ምድጃ እንጨት፥ ጭራሮ፣ ከሰል፣ ቅጠል፣ … ወዘተ. ለማገዶ በመጠቀም ምግብ ለማብሰል የሚያገለግል ባህላዊ ማድ ቤት ይባላል፡፡

አንድ ቤት ዘመናዊና ባህላዊ ማድቤት ሲኖረው ዘመናዊ ማድቤት ያለው በመሆኑ ይኸው ተመርጦ በዓ ምድ 65 ከተዘረዘሩት ውስጥ ኮድ 2 ተከቦ በካርድ ኮለሙ ይሞላል፡፡

ስለዚህ ቤቱ ማድቤት ያለው መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የማድቤቱን ዓይነት ቀጥሎ ከተሰጡት የኮዶች ዝር ዝር ውስጥ በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በዓምድ 65 ባለው ካርድ ኮለም ይሞላል፡፡

1= ማድቤት የለውም
2= ዘመናዊ ማድቤት በግል
3= ዘመናዊ ማድቤት በጋራ
4= ባህላዊ ማድቤት በግል
5= ባህላዊ ማድቤት በጋራ

## ዓምድ 66 <u>የቤቱ ነዋሪዎች የመጠጥ ውኃ በአብዛኛው የሚያገኙት ከየት ነው?</u>

በዚህ ዓምድ በቤቱ የሚኖሩት አባላት ለመጠጥ የሚጠቀሙበትን ውኃ በአብዛኛው ከየት እንደሚያገኙ በ መጠየቅ ከዚህ ቀጥሎ ከተሰጡት ዝርዝር ኮዶች በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይኸው በዓምዱ ሥር 67 ባለው ካርድ ኮለም ውስጥ ይሞላል፡፡

1= ከቧንቧ ውኃ እቤት ውስጥ
2= ከቧንቧ ውኃ ከግቢው ውስጥ በግል
3= ከቧንቧ ውኃ ከግቢው ውስጥ በጋራ
4= ከቧንቧ ውኃ ከግቢው ውጭ (ከግለሰብ፥ ከቦኖ፥ ከሌላ ድርጅት በነፃ ወይም በግዥ)
5= ከተጠበቀ ጉድጓድ (ምንጭ)
6= ካልተጠበቀ ጉድጓድ (ምንጭ)
7= ወንዝ ሐይቅ (ኩሬ)

ከላይ በኮድ «5» እና «6» የተመለከቱትን መልሶች በሚገባ ለይቶ ለማወቅ «የተጠበቀ» የጉድጓድ/ምን ጭ ውኃ » ትርጉሙን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

የተጠበቀ ጉደጓድ ወይም ምንጭ የሚባለው ምን ዓይነት እንደሆነ ከዚህ በታች ተዘርዝሯል፡፡

1/ በጉደጓዱ ወይም በምንጩ ዙሪያ በሲሚንቶ የተገነባ ግንብ መኖር አለበት፥ይኸውም፡-

ሀ. ጉድጓድ ከሆነ ጉድጓዱ በሚገኝበት የአፈር ሁኔታ ግንቡ ቢያንስ ከ2 እስከ 4 ሜትር ወደ መሬት ውስጥ የገባ እና 70 ሳንቲ ሜትር ያህል ደግሞ ከመሬት ወደ ላይ ከፍ ብሎ የወጣ መሆን ይኖርበ ታል፡፡

ለ. ምንጭ ከሆነ ግንቡ ጠንካራ መሬት ወይም አለት እስከሚገኝበት ድረስ መሬት ውስጥ የገባና እንደ አስፈላጊነቱ ከመሬት በላይ ከፍ ብሎ የወጣ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከግንቡ በአንድ በኩል ውኃ ማ ውጫ ክፍት ቧንቧ ያለው መሆን አለበት፡፡

2/ በጉድጓድም ሆነ በምንጭ ዙሪያ የተገነባው ግንብ ከላይ ከሲሚንቶ የተሠራ ወይም ሌላ ዓይነት ጥብቅ ክዳን እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡

3/ ወደ ጉድጓዱ ወይም ምንጩ ጎርፍ እንዳይገባ የጎርፉን አቅጣጫ የሚቀይር ተስማሚ ቦይ ጎርፍ ሊመ ጣ ከሚችልበት አካባቢ ወይም አቅጣጫ መኖር አለበት፡፡

4/ እንደ መጸዳጃ ቤት ከመሳሰሉት ውኃውን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች ጉድጓዱም ሆነ ምንጩ ቢያንስ ቢ ያንስ ከ25 እስከ 30 ሜትር የራቀ መሆን አለበት፡፡

5/ በተራ ቁጥር 4 የተገለፀው በካይ ቆሻሻ ዓይነት የውኃው ጉድጓድ ወይም ምንጩ ከሚገኝበት ከፍ ባለ ቦታ ቢኖር እርቀቱ በተራ ቁጥር 4 ላይ ከተጠቀሰው ርቀት ብዙ መብለጥ ይኖርበታል፡፡

ስለዚህ ቤተሰቡ ውኃ የሚያገኘው ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በሚያሟላ ሁኔታ ከተጠበቀ ጉደጓድ ወይ ም ምንጭ ከሆነ ከተጠበቀ ውኃ እንደተጠቀመ ይቆጠራል፣ በቧንቧ የሚመጣ ውኃ ካልሆነ በስተቀር ከወ

ንዝ ወይም ከሐይቅ እየተቀዳ የሚገኘው ውኃ በአጠቃላይ ያልተጠበቀ ነው ለማለት ይቻላል:: ስለ ዚህ ከወንዝ፣ ከሐይቅ ወይም ኩሬ እየቀዳ የሚጠቀም ቤተሰብ በተጠበቀ ውኃ አይጠቀምም ማለት ነ ው:: ከቧንቧ የሚገኝ ውኃ ግን በአጠቃላይ እንደተጠበቀ ይቆጠራል:: ውኃው ግን ወደ ተጠቃሚ ዎቹ ቤት የሚደርሰው በሰው ጉልበት ወይም በጋማ ከብቶች ሊሆን ይችላል::

## ዓምድ 67 <u>የቤቱ ነዋሪዎች ለምግብ ማብሰያ አብዛኛውን ጊዜ ምን ዓይነት ማገዶ ይጠቀማሉ</u>?

የቤቱ ነዋሪዎች ለምግብ ማብሰያ የሚጠቀሙበትን የማገዶ ዓይነት በመጠየቅ በተገኘው መልስ መሠ ረት ከዚህ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት የኮዶች ዓይነት በትክክለኛው ኮድ ክብ በማድረግ ይኸው ኮድ በዓም ድ 67 ስር ባሉት ካርድ ኮለሞች ውስጥ ይሞላል::

| | |
|---|---|
| 1= ማገዶ አይጠቀሙም | 4= ኬሮሲን /ነጭ ጋዝ/ |
| 2= ኤሌክትሪክ | 5= እንጨት /ከሰል፣ ቅጠል፣ ሰጋቱራን ይጨምራል/ |
| 3= ሲሊንደር | 6= ሌላ /ይገለጽ/ _______________ |

በጥያቄው መሠረት የሚመዘገበው ቤተሰቡ በአብዛኛው የሚጠቀምበት የማገዶ ዓይነት ነው:: ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የማገዶ ዓይነት ለሚጠቀሙ ሁሉ በይበልጥ የሚጠቀሙበት የማገዶ ዓይነት ተ ጠይቆ ይመዘገባል:: ቤተሰቡ ምግብ የማያበስል ከሆነ (<u>ለምሳሌ</u>:- ሆቴል ለሚመገቡ ፥ ከሌላ ቤት የ ሚመገቡ ... ወዘተ.) ማገዶ አይጠቀሙም የሚለው ኮድ 1 ይመዘገባል:: እንዲሁም <u>ለምሳሌ</u>:- ኤ ሌክትሪክ ተብሎ ኮድ 2 የሚመዘገብላቸው ቤቶች በአብዛኛው ኤሌክትሪክ የሚጠቀሙ ማለት ሲሆን ይህም ኤሌክትሪክ ብቻ ወይም ሌላ ዓይነት ማገዶ ከኤሌክትሪክ ሌላ በተጨማሪ የሚጠቀሙ ቢሆን ም ይበልጥ የሚጠቀሙበት ማገዶ ኤሌክትሪክ ከሆነ ነው::

## ዓምድ 68 <u>የቤተሰቡ ቋሚ ንበረቶች</u>

የቤተሰቡን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ ለመገመት ቤተሰቡ ያሉትን ቋሚ ንብረቶች እንደመለኪያ በመውሰድ መገመት ይቻላል:: ስለዚህ የእያንዳንዱን ንብረት ስም ለመልስ ሰጪው በማንበብ የሚሰ ጠውን መልስ መክበብ ተገቢ ይሆናል:: መልስ ሰጭው የተጠቀሰው ዕቃ እንደ ሬዲዮ ያለሆኖ የተ ሰበረ መሆኑን ከተናገረ ከተሰበረ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነው በመጠየቅ ዕቃው ከጥቅም ውጭ የሆነወ ለጊዜው ከሆነ እንደሚሰራ ተቆጥሮ መልሱ «አዎን» ስለሚሆን ኮድ «1» ይከበባል:: ለእያንዳንዱ ንብረት ኮድ «1» ወይም «2» መከበቡን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል:: በዚህ ዓምድ ክፍት የሚተወ መልስ ያለመኖሩን ማወቅ ያስፈልጋል::

## ዓምድ 69 - 70B <u>የቤተሰቡ ግምታዊ ወጪ እና ገቢ መጠን በብር</u>

የቤተሰቡ ወጪና ገቢ የቤተሰቡን ኢኮኖሚያዊ ደህንነት የሚያሳዩ መረጃዎች በመሆናቸው ለዚህ ጥ ናት ጠቃሚ ናቸው:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ቤተሰቦች የቤተሰባቸውን ትክክለኛ ወጪና ገቢ ለማስ ታወስ ስለሚቸገሩ ወይም ለመግለፅ ስለማይፈልጉ በዚህ ጥናት ወጪአቸው እና ገቢአቸው ከስንት እ ስከ ስንት ብር እንደሚሆን እንዲገምቱ ይጠየቃሉ:: የቤተሰቡ የፍጆታ ወጪ ሲባል ለቤተሰቡ የም ግብ፣ የመጠጥ፣ የቤት ኪራይ፣ ለልብስ እና ጫማ፣ ለትምህርት፣ ለትንራንስፖርት ...ወዘተ በአጠቃላይ ለቤተሰቡ ፍጆታ የወጣውን ወራዊ ወጪ የሚያጠቃልል ሲሆን የቤተሰቡ ገቢ ደግሞ ቤተሰቡ ከተለ ያዩ የገቢ ምንጮች ያገኘውን ገቢ በሙሉ ያጠቃልላል::

## ዓምድ 69 <u>የዚህ ቤተሰብ ግምታዊ የወር አማካይ ወጪ በብር ምን ያህል ይሆናል</u>?

በዚህ ዓምድ ለቤተሰቡ የተለያዩ የፍጆታ ቁሳቁሶች እና አገልግሎቶች ቤተሰቡ የሚያወጣው አማካ ይ የወር ወጪ ምን ያህል ብር እንደሆነ ተጠይቆ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ተስማሚው ኮድ ተከቦ ይኸው ኮድ በካርድ ኮለሙ ይሞላል:: አማራጭ መልሶቹ የሚከተሉት ናቸው::

| | |
|---|---|
| 1= 50 ብርና በታች | 4= ከ601 - 1000 ብር |
| 2= ከ51 - 300 ብር | 5= 1001 ብርና በላይ |
| 3= ከ301 - 600 ብር | |

## ዓምድ 70A <u>*በከተማ* የዚህ ቤተሰብ ግምታዊ የወር አማካይ ገቢ ምን ያህል ብር ይሆናል</u>?

በዚህ ዓምድ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች (ከደሞዝ፣ ከግል ንግድ ከሚገኝ ትርፍ፣ ከቤተሰብ አባላት ውጪ ከሚገኝ ተቆራጭ፣ ከቤትና ከተለያዩ ቁሳቁሶች ኪራይ፣ ከጡረታና ከመሳሰሉት) የቤተሰቡ አማካይ የወር ገቢ ምን ያህል ብር እንደሆነ ተጠይቆ ከሚከተሉት አማራጭ መልሶች መካከል ተስማሚው ኮድ ተከቦ በካርድ ኮለሙ ይሞላል፡፡ ከንግድ የሚገኝ ገቢ የሚባለው በወር የተካሄደው ሽያጭ ሳይሆን በወር ውስጥ የተገኘው ትርፍ ብቻ ነው፡፡

| | |
|---|---|
| 1= 50 ብርና በታች | 5= ከ401 – 700 ብር |
| 2= ከ51 – 100 ብር | 6= ከ701 – 1000 ብር |
| 3= ከ101 – 200 ብር | 7= 1001 ብርና በላይ |
| 4= ከ201 – 400 ብር | |

## ዓምድ 70B ***በገጠር የዚህ ቤተሰብ ያለፉት 12 ወራት ግምታዊ ገቢ ምን ያህል ብር ይሆናል?***

በገጠር አካባቢ የሚኖር ቤተሰብ በአብዛኛው ገቢ የሚያገኘው ከግብርናው ውጤት ከአመታዊ የሰብል ምርት በመሆኑ የቤተሰቡ ገቢ የሚጠየቀው ያለፉትን 12 ወራት በሚመለከት ነው፡፡ በዚህ መሠረት በገጠር ለሚኖር ቤተሰብ ከማንኛውም የገቢ ምንጭ (ከግል እረሻ ውጤት፣ ከግል ንግድ ከሚገኝ ትርፍ፣ ከደሞዝ፣ ከቤተሰቡ አባላት ውጪ ከሚገኝ ተቆራጭ እና ከመሳሰሉት) ቤተሰቡ ምን ያህል ብር እንዳገኘ ተጠይቆ ከሚከተሉት አማራጭ መልሶች መካከል ተስማሚው ኮድ ከተከበበ በኋላ በካርድ ኮለሙ ይሞላል፡፡ በአብዛኛው በገጠር አካባቢ ቤተሰቦች የሚያገኙት ገቢ በአይነት (በተለያዩ የእርሻ ውጤቶች) ስለሚሆን ቢሸጥም ባይሸጥም በአጠቃላይ የዓመቱ ምርት በአካባቢ የገበያ ዋጋ በብር ተገምቶ ተስማሚው ኮድ መሞላት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን በገጠር የሚኖሩ የወር ደሞዝተኞች ነጋዴዎች ወዘተ ገቢያቸውን በወር መግለፅ የሚቀላቸው ከሆነ የቤተሰቡ የወር ገቢ ወደ ዓመት ተቀይሮ (በ12 ተባዝቶ) ተስማሚው ኮዱ ሊሞላላቸው ይችላል፡፡ አማራጭ መልሶቹም የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | |
|---|---|
| 1= 600 ብርና በታች | 5= ከ4801 – 8400 ብር |
| 2= ከ601 – 1200 ብር | 6= ከ8401 – 12000 ብር |
| 3= ከ1201 – 2400 ብር | 7= 12001 ብርና በላይ |
| 4= ከ2401 – 4800 ብር | |

## ምዕራፍ 5

## የቅጽ 2 አሞላል መመሪያ_

### ክፍል 6፡- የልጆች የፍልሰት ሁኔታ

በዚህ ክፍል ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት የሆናቸው ልጆች የፍልሰት ሁኔታ የሚጠየቅ ሲሆን ለፈለሱ ልጆች ከተወለዱ ጀምሮ አብረው ሲኖሩ ከነበሩበት ቤተሰብ ተለይተው ወደ ሌላ ቤተሰብ ሊፈልሱ የቻሉበት ዋነኛ ምክንያትም የሚጠየቅበት ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ክፍል ፍልሰት የሚለው ፅንሰ ሀሳብ የተለመደ ፍችውን በጠበቀ መንገድ ከቦታ ቦታ የሚደረግ እንቅስቃሴን የያዘ ብቻ ሳይሆን ከጥናቱ ዓላማ አኳያ በአንድ ቦታ ላይም ከአንድ ቤተሰብ ወደ ሌላ ቤተሰብ የተደረገን የልጆችን እንቅስቃሴ ጭምር የሚያካትት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ልጅ በአንድ በሆነ ምክንያት በመደበኛነት ይኖርበት የነበረውን ከተማ ለቆ ወደ ሌላ ከተማ ቢሄድ በተለመደው የፍልሰት ትርጓሜ መሰረት እንደ ፈለሰ የሚቆጠር ሲሆን ነገር ግን ልጁ የፈለሰው ከተወለደ ጊዜ ጀምሮ ከሚኖርበት ቤተሰብ ጋር ከሆነ ከዚህ ጥናት ዓላማ አኳያ እንደፈለሰ/ች አይቆጠርም፡፡ እንደዚሁም ጋብቻ በሚፈርስበት ጊዜ ልጁ/ልጅቷ የቤተሰብ ኃላፊውን ጨምሮ ከአብዛኞቹ የቤተሰቡ አባላት ጋር ከቀረ/ች እንደፈለሰ/ች አይቆጠርም፡፡ አንዳንድ ግለሰቦች ከቤተሰባቸው ውጭ በሆስፒታል ወይም በጤና ጣቢያ ወይም ሌሎች ዘመዶች ቤት ወልደው ለተወሰነ ጊዜ እዚያው ሊቆዩ ይችላሉ፤ በዚህ ጊዜ ልጁ በሌላ ቤተሰብ ሳይሆን በራሱ ቤተሰብ ውስጥ እንደተወለደ አድርገን መቁጠር ይኖርብናል፡፡ ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ ያለማቋረጥ ከቤተሰባቸው ጋር በመደበኛነት ያልኖሩ የምንላቸው፡-

1) አሁን ከሚኖሩበት ቤተሰብ ውጭ በመደበኛነት ከሌላ ቤተሰብ ጋር የኖሩ/የሚኖሩ

2) በሚኖሩበት ቤተሰብ ውስጥ ተወልደው በመሀሉ ከሌላ ቤተሰብ ጋር በመደበኛነት ሲኖሩ ቆይተው የተመለሱ፡፡ ይህ ማለት ግን ለጥቂት ጊዜ ብቻ ከሌላ ቤተሰብ ጋር ኑረው የተመለሱትን ልጆች ሳይሆን ስድስት ወርና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ከሌላ ቤተሰብ ጋር ቆይተው የተመለሱትን ነው፡፡

601.

**<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ከተወለደ/ች ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ቤተሰብ ጋር ያለማቋረጥ በመደበኛነት አብሮ/ራ ኖሯል/ኖራለች?</u>**

በዚህ ጥያቄ ልጁ/ልጅቷ ከተወለደ/ች ጊዜ ጀምሮ አሁን አብሮ/ራ እየኖረ/ች ካለበት/ችበት ቤተሰብ ጋር ያለማቋረጥ በመደበኛነት አብሮ/ራ ለመኖሩ/ሯ የሚጠየቅ ሲሆን አዎን ከሆነ ኮድ 1 ተከቦ ወደ ጥያቄ 701 ይታለፋል፤ የለም ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ይከበብና ቀጣዩ ጥያቄ ይጠየቃል፡፡

602.

**<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ/ቷ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የኖረበት/ችበት ቦታ የት ነው?</u>**

በዚህ ጥያቄ ደግሞ ልጁ/ልጅቷ ከሌላ ቤተሰብ የመጣ/ች ከሆነ ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ/ቷ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የኖረበት/ችበት ቦታ (ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣታቸው በፊት በመደበኛነት ይኖሩበት የነበረው ቤተሰብ ያለበት ቦታ) የሚጠየቅ ሲሆን በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ለመጨረሻ ጊዜ የኖረበት/ችበት ክልል እና ዞን ስም ይመዘገባል፤ በካርድ ኮለሞቹም የክልሉና የዞኑ ኮዶች ይሞላሉ፡፡ የክልል ኮዶች ከዚህ በታች የተሰጡ ሲሆን የዞኖች ዝርዝርና ኮድ ደግሞ በዚህ መመሪያ በዕዝል 2 ገፅ___ ተያይዟል፡፡

| | |
|---|---|
| 01= ትግራይ ክልል | 07= ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል |
| 02= አፋር ክልል | 12= ጋምቤላ ክልል |
| 03= አማራ ክልል | 13= ሐረሪ ክልል |
| 04= ኦሮሚያ ክልል | 14= አዲስ አበባ |
| 05= ሶማሌ ክልል | 15= ድሬዳዋ |
| 06= ቤንሻንጉል-ጉምዝ ክልል | 16= ከኢትዮጵያ ውጭ (የአገሩ ስም ይሞላል) |

<u>ማስታወሻ</u> ፡-

-ልጁ/ልጅቷ ወደ ቤተሰቡ ከመምጣቱ/ቷ በፊት የኖረበት/ችበት ቦታ ከአገር ውጭ ከሆነ የአገሩ ስም ለክልል በተሰጠው ቦታ ላይ ይሞላል፤ ለዞን የተሰጠው ክፍት ቦታ ግን በ '-' ይታለፋል፡፡

603.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ/ቷ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የኖረበት/ች በት ቦታ ከተማ ነው ወይስ ገጠር?**

ልጁ/ልጅቷ ከሌላ ቤተሰብ ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ/ቷ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ የኖረበት/ችበት ቦታ ከተማ ከሆነ ኮድ 1 ይከበብና የከተማው ስም በተሰጠው ቦታ ላይ ይፃፋል፤ ገጠር ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ይከበባል (ገጠር በሚለው አኳያ ለመፃፊያ የሚሆን ቦታ ያልተተወው የገጠሩን ስም መፃፍ አስፈላጊ ስላልሆነ ነው)። እዚህ ላይ ሁለትና ከሁለት በላይ ከሆኑ ቤተሰቦች ጋር ሲኖሩ የቆዩ ልጆች በጥናቱ በሚሸፈነው ቤተሰብ ውስጥ ካጋጠሙ የሚመዘገብላቸው ለመጨረሻ ጊዜ ይኖሩበት የነበረውን ቤተሰብ የመኖሪያ ቦታ ነው።

604.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ/ቷ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ በኖረበት/ችበት ሥፍራ ምን ያደርግ/ታደርግ ነበር?**

ልጁ/ልጅቷ ከሌላ ቤተሰብ ወደዚህ ቤተሰብ ከመምጣቱ/ቷ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ በኖረበት/ችበት ሥፍራ ምን ያደርግ/ታደርግ እንደነበር ተጠይቆ ማንኛውንም ዓይነት ሥራ ሲሰራ/ስትሰራ ከነበረ ኮድ 1፡- ትምህርት/ስልጠና ሲከታተል/ስትከታተል ከነበረ ኮድ 2፤ ትምህርት/ስልጠና እየተከታተለ/ች ማንኛውንም ዓይነት ሥራ ሲሰራ/ስትሰራ ከነበረ ኮድ 3 የሚከበብ ሲሆን መልሱ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች የተለየ ከሆነ ደግሞ ኮድ 4 ተከቦ መልሱ በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ይገለፃል።

605. **(የልጁ/ጅቷ ስም) ከዚህ ቤተሰብ ጋር ለመኖር ያመጣው/ት ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው?**

የዚህ ጥያቄ ዓላማ ልጆች ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ አብረው ሲኖሩ ከነበሩበት ቤተሰብ ተለይተው ወደ ሌላ ቤተሰብ የሚፈልሱባቸውን ዋነኛ ምክንያቶች ለመለየት ነው። በዚህም መሰረት ልጁ/ልጅቷ ከተወለደ/ች ጊዜ ጀምሮ አብሮ/ራ ሲኖር/ስትኖር ከነበረበት/ችበት ቤተሰብ ተለይቶ/ታ ከዚህ ቤተሰብ ጋር ለመኖር ያመጣው/ት ዋነኛ ምክንያት ተጠይቆ ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች መካከል የተስማሚው ኮድ ይከበባል። በዚህ ክፍል መግቢያ ላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ አብረው ሲኖሩ ከነበሩበት ቤተሰብ ጋር አብረው መደበኛ የመኖሪያ ስፍራቸውን የለቀቁ ልጆች እንደ ፈለሱ አይቆጠርም፤ በመሆኑም ለዚህ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል የሥራ ዝውውር የሚለው የልጁን የራሱን የሥራ ዝውውር በተመለከተ እንጅ የቤተሰቡን የሥራ ዝውውር በተመለከተ እንዳልሆነ መረዳት ይገባል። አማራጭ መልሶቹም ከዚህ በታች ቀርበዋል፡-

| | |
|---|---|
| 1= የሥራ ዝውውር | 6= በመፈናቀል/በጦርነት፤ ድርቅ፤ .../ |
| 2= ሥራ ስላገኘ/ች | 7= ከዘመድ ጋር ለመኖር |
| 3= ሥራ ለመፈለግ | 8= በወላጅ ሞት ምክንያት |
| 4= ትምህርት/ስልጠና ለመከታተል | 9= ሌላ (ይገለፅ) ____________ |
| 5= በጋብቻ መፍረስ | |

606.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) አሁን በሚኖርበት/በምትኖርበት የመኖሪያ ቦታ ለምን ያህል ዓመት ቆይቷል/ ቆይታለች?**

ልጁ/ልጅቷ ለመጨረሻ ጊዜ በመደበኛነት ሲኖርበት/ስትኖርበት ከነበረው ቤተሰብ ተለይቶ/ታ አሁን ወደሚኖርበት/ምትኖርበት ቤተሰብ ከመጣ/ች በኋላ በዚህ ቦታ ያለማቋረጥ ለምን ያህል ዓመት እንደቆየ/ች ተጠይቆ ተገቢው ኮድ ይከበባል። አማራጭ መልሶቹም ከዚህ በታች ቀርበዋል፡-

| | |
|---|---|
| 0= ከአንድ ዓመት በታች | 4= አራት ዓመት |
| 1= አንድ ዓመት | 5= ከ5-6 ዓመት |
| 2= ሁለት ዓመት | 6= ከ7-8 ዓመት |
| 3= ሦስት ዓመት | 7= 9 ዓመትና በላይ |

## ክፍል 7፡- የልጆች የትምህርት ሁኔታ

701.

**<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) በያዝነው የትምህርት ዘመን ትምህርት እየተከታተለ/ች ነው? ምን ዓይነት ትምህርት?</u>**

በዚህ ጥያቄ ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት የሆኑ ልጆች የትምህርት ሁኔታ የሚጠየቅበት ነው። ይህ ጥያቄ በመደበኛ (በመንግስት፣ በግል፣ በሙያ/ቴክኒክ ት/ቤቶች ... ወዘተ ) እና መደበኛ ባልሆነ (ለ ምሳሌ በቄስ ት/ቤት፣ በቁርአን ት/ቤት፣ በመዋዕለ ሕፃናት፣ በመሠረተ ትምህርት ... ወዘተ) ትምር ት እየተከታተሉ ያሉት የሚለዩበት ነው። በጥናቱ ወቅት መደበኛ ትምህርት ለሚከታተሉት ኮድ 1 ይከበባል፣ የሙያ ትምህርት ለሚከታተሉ ደግሞ ኮድ 2 ይከበብና ወደ ጥያቄ 703 ይታለፋል። መ ደበኛ ያልሆነ ትምህርት ለሚከታተሉ ኮድ 3 ፡-

ምንም ዓይነት ትምህርት ለማይከታተሉ ደግሞ ኮድ 4 ይከበባል። ኮድ 3 እና ኮድ 4 ለተከበበላቸ ው ልጆች ወደ ጥያቄ 704 ይታለፋል። ስልጠና ሲባል በአንድ ድርጅት ወይም መ/ቤት የተወሰነ ጊ ዜ ተመድቦለት ፕሮግራም ተንድፎለት ከቀለም ትምህርት ውጭ የሆነ የሙያ ትምህርት/ስልጠና ነ ው። ለዝርዝር ሀሳቡ በቅፅ 1 ዓምድ 21 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ።

702

**<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) አሁን የሚከታተለው/የምትከታተለው የክፍል ወይም የትም ህርት ደረጃ ስንተኛ ነው?</u>**

ከላይ በጥያቄ 701 ሲጠየቁ አዎን ብለው ኮድ 1 የተሞላላቸው ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት የሆኑ ልጆች በአሁኑ ወቅት ወይም ሴምስተር የሚከታተሉት የትምህርት ደረጃ ይጠየቃሉ። ከዚህ ጥያቄ በፊት በቅፅ 1 ዓምድ 20 የጨረሱት ከፍተኛ ክፍል መጠየቃቸው ይታወሳል። በዚህኛው ዓምድ የጨረሱት ሳይሆን በአሁኑ ሴምስተር ስለሚከታተሉት የትምህርት ደረጃ ብቻ የሚጠይቅበት ነው። ስለዚህ ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለማ ከታተሉ ያሉበት የትምህርት/የክፍል ደረጃ እንደ ኮድ ተወስዶ ይሞላል። ለምሳሌ 3ኛ ክፍል እየተከታተሉ ላሉ ኮድ 03 ይሞላል። ከ12ኛ ክፍል በላይ ለሚከታተሉ ሁሉ ግን ኮድ 13 በካርድ ኮለሙ ይሞላል።

703.

**<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፈው ሳምንት መደበኛ ትምህርት ወይም ስልጠና ተከታትሎ/ላ ነበር?</u>**

ጥናቱ በሚካሄድበት ሳምንት ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት የሆናቸው የቤተሰቡ አባላት መደበኛ ትምህርት/ስ ልጠና እየተማሩ/እየተከታተሉ መሆን አለመሆናቸው ተጠይቆ ሙሉ ጊዜአቸውን/ሰዓት በትምህርት/ስልጠና ለሚያሳልፉ ኮድ 1፣ ግማሽ ቀን ብቻ ለሚማሩ ኮድ 2፣ ለማታ ተማሪዎች ወይም ከግማሽ ቀን በታች ለሚ ማሩ ኮድ 3፣ እንዲሁም በጥናቱ ሳምንት ለማይማሩ ኮድ 4 ይሞላላቸዋል። ከኮድ 1-3 ለተከበበላቸው ወደ ጥያቄ 801 የሚታለፍ ሲሆን ኮድ 4 ለተከበበላቸው ደግሞ የሚቀጥለው ጥያቄ ይቀርብላቸዋል። በዚያ ሳምን ት ትምህርት ቤት ያልሄዱ የቤተሰቡ አባላት በመማር ላይ እንዳሉ ተደርጎ እንዳይመዘገቡ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

704 **<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ከዚህ ቀደም መደበኛ ትምህርት ተምሮ/ራ ነበር ?</u>**

ይህ ጥያቄ የሚመለከተው በጥያቄ 701 መደበኛ ያልሆነ ትምህርት እየተማርኩ ነው ብለው ኮድ 3 የተከበበ ላቸውን ወይም አልማርም ብለው ኮድ 4 የተከበበላቸውን ሲሆን ከጥናቱ በፊት በማናቸውም ዓመታት ውስ ጥ (የጥናቱን ዓመት ጨምሮ) ትምህርት ተምረው ያውቁ እንደሆነና እንዳልሆነ ተጠይቀው ከተሰጡት አማ ራጭ መልሶች አንዱን ብቻ እንዲመልሱ ይደረጋል።

1=

<u>በዚህ ዓመት ጀምሮ/ራ አቋርጧል/አቋርጣለች</u>፡- በያዝነው የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህ ርት/ስልጠና ጀምረው ነገር ግን ትምህርታቸውን/ስልጠናቸውን በተለያዩ/ምክንያቶች በማ ቋረጣቸው በመማር ላይ ለማይገኙ ልጆች ይህ ኮድ ይሰጣቸዋል። በተለያየ ምክንያት ለጥቂተ ቀናት ከትምህርት ገበታ/ከስልጠና ቀርተው ነገር ግን ወደ ትምህርታቸው/ስልጠናቸው መመ ለስ የሚፈልጉና ት/ቤቱም እንዲመለሱ የሚፈቅድላቸው ልጆች ጀምረው እንዳቋረጡ አይቆ ጠርም።

2=

**ከዚህ ዓመት በፊት ተምሮ/ራ ነበር:-** ከጥናቱ ዓመት በፊት በነበረ በማንኛውም ዓመት መደበኛ ትምህርት/ስልጠና ለተማሩ የሚሰጥ ኮድ ነው:: ተምረው ያቋረጡ ሲባል ባለፉት ዓ መታት ውስጥ ቢያንስ አንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃን አጠናቀው ያቋረጡ ማለት ነው::

3=

**ምንም ተምሮ/ራ አያውቅም/አታውቅም:-** በጥናቱ ዓመትም ሆነ ከጥናቱ ዓመት በፊት ምን ም ትምህርት/ስልጠና ተምረው/ተከታትለው ለማያውቁ ልጆች የሚሰጥ ነው::

4=

**ለጊዜው ባለፈው ሳምንት የቀረ/ች:-** በተለያየ ምክንያት ባለፈው ሳምንት ከትምህርት ገበታ/ ከስልጠና የቀሩ ነገር ግን ወደ ትምህርታቸው/ ስልጠናቸው መመለስ የሚፈልጉና ት/ቤቱም እንዲመለሱ የሚፈቅድላቸው ልጆች ይህ ኮድ ይከበብላቸዋል::

705

**(የልጁ/ጅቷ ስም) መደበኛ ትምህርት/ስልጠና ያልተከታተለበት/ችበት ዋና ምክንያት ምንድነው?**

ይህ ጥያቄ በጥያቄ 701 መደበኛ ያልሆነ ትምህርት እከታተላለሁ ብለው ኮድ 3 እና፣ መደበኛም መደበኛ ያ ልሆነም ትምህርት አልተከታተለም ብለው ኮድ 4 የተሞላላቸው፣ በጥያቄ 703 ላይ ባለፈው ሳምንት ትምህ ርት እንደማይከታተሉ ተረጋግጦ ኮድ 4 የተሞላላቸውን ይመለከታል:: ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ውስጥ ተቀራራቢ ከሆኑት ዋነኛ የሆነውን ምክንያት በመውሰድ ኮዱ ይከበባል:: ለምሳሌ ልጁ በጥናቱ ሳምንት በህ መም/ወይም በአካል ጉዳት ትምህርት ያልተከታተለ ከሆነ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች በህመም ወይም በአካ ል ጉዳት የሚለው ኮድ 06 ይሞላለታል:: እንዲሁም 12ኛ ክፍል ሳጠናቀቁ ሌላ በሚለው አንፃር ኮድ 15 በ ከቦ 12ኛ ክፍል ያጠናቀቁ ተብሎ በተሰጠው ቦታ ላይ ይገለፃል:: ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ትምህርቱን ያልተከታተለ ከሆነ መልስ ሰጪው ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ዋነኛውን ምክንያት ብቻ እ ንዲመርጥ ይደረጋል::

01= ባቅራቢያው ት/ቤት ወይም ማሰልጠኛ ማዕከል ባለመኖሩ
02= ቤተሰቡ ለት/ቤት ወይም ለስልጠና የሚከፍለው/የምትከፍለው ገንዘብ ስለሌለው
03= በትምህርት ደካማ ስለሆነ/ችና ትምህርትለመማር ፍላጎት ስለሌለው/ላት
04= በትምህርት ስለወደቀ/ች
05= አስተማሪዎችን ስለሚፈራ /ምትፈራ
06= በህመም/በአካል ጉዳት
07= በቤት ውስጥ ሥራ ቤተሰቦቹን/ቿን ስለሚረዳ /ምትረዳ
08= እራሱን/ሷን ለመርዳት ስለሚሠራ/ምትሰራ
09= ለቤተሰቡ/ቧ ገቢ ለማስገኘት ሲል ስለሚሠራ /ምትሰራ
10= ቤተሰቦቹ/ቿ ትምህርት እንዲማር/ትማር ስልጠና እንዲከታተል/ድትከታተል ስለማይፈቅዱ
11= በጋብቻ ምክንያት
12= በመፈናቀል (በጦርነት፣ በድርቅ)
13= በቤተሰብ ዝውውር
14= በቤተሰብ መበተን (በፍቺ፣ በሞት)
15= ሌላ (ይገለፅ) ________________

## ክፍል 8:- ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ሁኔታና ምንም አለመሥራት (ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት ለ ሆኑ ልጆች)

በዚህ ክፍል ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት የሆኑ ልጆች ለቤተሰቡ ግልጋሎት የሚውሉ ምርታማ ያልሆኑ የቤት ውስጥ ሥራዎችን መስራት አለመስራታቸው የሚጠየቅ ሲሆን የሚሰሩ ከሆነ በቀን በአማካይ ለስንት ሠዓት እንደሚሰሩ እና የሰሯቸው ግልጋሎቶችም ምን ምን እንደሆኑ የሚዘረዘርበት ነው:: እንዲሁም በዚሁ ክፍል ባለፉት 7 ቀናት የቤት ውስጥ ሥራን ጨምሮ ምንም ዓይነት ሥራ ያልሠሩ፣ ትምህርት ያልተከታተሉ፣ በምር ታማም ሆነ ምርታማ ባልሆነ ሥራ ያልተሰማሩ ልጆች ተለይተው ምንም ዓይነት ሥራ ያልሠሩበት ምክንያት ይጠየቅላቸዋል::

*ማስታወሻ 1* ፡- ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ሲባል በቤት ውስጥ ለቤተሰቡ ግልጋሎት የሚውሉ ምርታማ ያልሆኑ ሥራዎች በቤተሰቡ አባላት ያለክፍያ ለወላጆቻቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው፣ ለአያቶቻቸው/ለአሳዳጊዎቻቸው ሲያከናወኑ ነው። እነዚህም ለቤተሰቡ ምግብ ማዘጋጀትና ማቅረብ፣ ለቤተሰቡ ልብስ መስፋት፣ መጠገን፣ ማጠብ፣ መተኮስ፣ ለቤተሰቡ የሚውሉ የፍጆታ ዕቃዎች መግዛት፣ ህፃናትን፣ የታመሙትንና አቅመ ደካማዎችን በቤት ውስጥ መንከባከብ፣ የቤተሰቡን መኖሪያ ማፅዳት፣ የቤተሰቡን ቋሚ ንበረቶች ማፅዳት፣ ባለበት ሁኔታ መጠበቅ፣ ለቤተሰቡ አባላት ወይም ለዕቃዎቻቸው/ንብረቶቻቸው... ወዘተ የማጓጓዝ አገልግሎት መስጠትን ያጠቃልላሉ።

*ማስታወሻ 2* ፡- ምንም ያልሠሩ የሚባሉት ባለፉት 7 ቀናት የቤት ውስጥ ሥራን ጨምሮ ምንም ዓይነት ሥራ ያልሠሩ፣ ትምህርት ያልተከታተሉ፣ በምርታማም ሆነ ምርታማ ባልሆነ ሥራ ላይ ያልተሰማሩ ናቸው።

801

**(የልጁ/ጅቷ ስም) በቤት ውስጥ ሥራ ወይም ለቤተሰቡ ግልጋሎት በመስጠት በወላጆቹ/ቿ (በአሳዳጊዎቹ/ቿ) ቤት ውስጥ በመደበኛነት ይሠራል/ትሠራለች?**

ልጁ/ልጅቷ ያለክፍያ በመደበኛነት እንደሚሠራ/እንደምትሠራ ተጠይቆ/ቃ በየቀኑ የሚሠራ/የምትሠራ ከሆነ ኮድ 1፣ ቅዳሜ እና እሁድ ብቻ የሚሠራ/የምትሠራ ከሆነ ኮድ 2፣ አልፎ አልፎ የሚሠራ/የምትሠራ ከሆነ ኮድ 3፣ ምንም የቤት ውስጥ ሥራ የማይሠራ/የማትሠራ ከሆነ ኮድ 4 ይከበባል። ኮድ 3 ለተከበበላቸው ወደ ጥያቄ 803 የሚታለፍ ሲሆን ኮድ 4 ለተከበበላቸው ደግሞ ወደ ጥያቄ 901 ይታለፋል።

እዚህ ላይ አንድ ልጅ በየቀኑ ወይም ቅዳሜና እሁድ ይሠራል የሚባለው የሠራበት/ችበት ሰዓት ከግምት ውስጥ ሳይገባ ከላይ በማስታወሻው ላይ የተዘረዘሩ የቤት ውስጥ ሥራዎችን በመደበኛነት ከሠራ/ች ነው። እንደ ሁም ምንም እንኳን በመደበኛነት ባይሆንም የተዘረዘሩትን የቤት ውስጥ ሥራዎች አልፎ አልፎ የሚሠራ/የምትሠራ ከሆነ ኮድ 3 ይከበባል።

802 **(የልጁ/ጅቷ ስም) በቀን በአማካይ ስንት ሰዓት ይሠራል/ትሠራለች?**

ይህ ጥያቄ የሚቀርበው ከላይ በየቀኑ ወይም ቅዳሜና እሁድ እሠራለሁ ብለው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ለተከበበላቸው ልጆች ሲሆን በመደበኛነት ከሚሠራበት/ከምትሠራበት ጊዜ አኳያ (በየቀኑ ወይም ቅዳሜና እሁድ) ልጁ/ልጅቷ በቀን በአማካይ ስንት ሰዓት እንደሚሠራ/እንደምትሠራ ተጠይቆ/ቃ ከታች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ተገቢው ኮድ ይከበባል።

| | |
|---|---|
| 1= ከ1 ሰዓት ላነሰ ጊዜ | 4= ከ5-6 ሰዓታት |
| 2= ከ1-2 ሰዓታት | 5= ከ7-8 ሰዓታት |
| 3= ከ3-4 ሰዓታት | 6= 9 ሰዓት ወይም ከዚያ በላይ |

803

**(የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፈው ሣምንት የሰራቸውን/ችውን የቤት ውስጥ ግልጋሎቶች ይግለጹልኝ?**

ይህ ጥያቄ በቀጥታ ለመልስ ሰጭው ከቀረበ በኋላ ለሚሰጣቸው (ለሚጠራቸው) ተግባራት ኮድ 1 ይከበብና ያልዘረዘራቸውን ተግባራት ደግሞ አንድ በአንድ በማንበብ እየተጠየቀ ልጁ/ጅቷ ለሰራቸው/ችው የቤት ውስጥ ግልጋሎቶች አዎን በሚለው አንፃር ኮድ 1 ላልሰራቸው/ችው ደግሞ የለም በሚለው አንፃር ኮድ 2 ይከበባል ። ባለፈው ሣምንት ላልሰሩ ልጆች "L= አልሠራም/ችም" በሚለው አኳያ ኮድ 1 ይከበባል።

| | |
|---|---|
| A= ቤት መጠበቅ | G= እንጨት/ኩበት መልቀም |
| B= ቤት ማጽዳት | H= ልጅ መጠበቅ/መንከባከብ |
| C= ምግብ ማዘጋጀት | I=. መልዕክት መላላክ |
| D= ምግብ ማቅረብ | J=. ውሃ መቅዳት |
| E= ልብስ ማጠብ/መጠገን/መተኮስ | K= ሌላ ይገለጽ___________ |
| F= ከገበያ ዕቃ መግዛት | L= አልሠራም/ችም |

804 **ለመረጃ ሰብሳቢ፡- ልጁ/ልጅቷ ባለፈው ሳምንት ምርታማ ሥራ ሠርቷል/ታለች ?**

ይህ ጥያቄ ለመልስ ሰጪው በቀጥታ ቀርቦ የሚጠየቅ ሳይሆን መረጃ ሰብሳቢው ከቅፅ 1 ዓምድ 25፣ 27ን እና 28ን በመመልከት የሚያጣራበት ነው። ልጁ/ልጅቷ ባለፈው ሳምንት ምርታማ ሥራ ሠርቶ/ታ ከሆነ ማለትም በዓምድ 27 ኮድ 1 ወይም በዓምድ 28 ከኮድ 1-3 ተከቦ ከሆነ ለጥያቄ 804 ኮድ 1 በማክበብ ወደ ጥያ

ቄ 901 ማለፍ ያስፈልጋል። እንዲሁም ልጁ/ልጅቷ ባለፈው ሳምንት ምርታማ ሥራ ያልሠራ/ች ከሆነ ማለት ም በዓምድ 25 ኮድ 2 እና በዓምድ 28 ኮድ 4፣ ወይም በዓምድ 27 ኮድ 2 እና በዓምድ 28 ኮድ 4 ተከቦ ከሆነ ተከቦ ከሆነ ለጥያቄ 804 ኮድ 2ን በማክበብ የሚቀጥለውን ጥያቄ ያቀርባል።

805

**(<u>የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፉት 7 ቀናት ምርታማ ያልሆነ የቤት ውስጥ ሥራ ሠርቷል/ሠር ታለች? ወይም ትምህርት ተከታትሏል/ላለች?</u>**

(<u>ማስታወሻ</u>:- ትምህርት የሚለው መደበኛ ያልሆነ ትምህርትንም ይጨምራል)

ይህ ጥያቄ የሚቀርበው ከላይ በጥያቄ 804 ላይ ልጁ/ልጅቷ ባለፈው ሳምንት ምርታማ ሥራ ካልሠራ/ች ሲ ሆን በዚህ ጥያቄ ደግሞ ባለፉት 7ቀናት ምርታማ ያልሆነ የቤት ውስጥ ሥራ መሥራት አለመሥራቱ/ቷ ወይ ም መደበኛ ያለሆነ ትምህርትን ጨምሮ ትምህርት መከታተል አለመከታተሉ/ሏ የሚጠየቅበት/የምትጠየቅበት ነው። በዚህም መሰረት ለጥያቄው አዎን ላሉ ኮድ 1 ተሞልቶ ወደ ጥያቄ 901 የሚታለፍ ሲሆን የለም ላሉ ደግሞ ኮድ 2 ተሞልቶ ቀጣዩ ጥያቄ ይቀርብላቸዋል።

806

**(<u>የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ምንም ዓይነት ሥራ ያልሠራበት/ችበት ወ ይም ትምህርት ያልተከታተለበት/ችበት ዋና ምክንያት ምንድን ነበር?</u>**

በጥያቄ 804 እና 805 ልጁ/ጅቷ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ሥራም ሆነ በትምህርት ወይም ምር ታማ ባልሆነ የቤት ውስጥ ሥራ አልተሳተፍኩም ብሎ/ብላ ከሆነ በሥራም ሆነ በትምህርት ያልተሳተፈበት/ ችበት ዋና ምክንያት ተጠይቆ ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች መካከል ተገቢ የሆነው ኮድ ይከበባል። ዕድሜ አቸው ከ10 ዓመት በላይ የሆናቸው ሴት ልጆች ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ሥራም ሆነ በትምህር ት ወይም ምርታማ ባልሆነ የቤት ውስጥ ሥራ ያልተሳተፈችበት ምክንያት በሴተኛ አዳሪነት ስለተሰማራች ነ ው ብሎ መልስ ሰጭው ከነገረን ኮድ 6ን በማክበብ ይህንኑ መግለፅ ያስፈልጋል።

1= በሕመም
2= በአካል ጉዳት
3= ልጅ ስለሆነ/ች
4= በልመና ሥራ ላይ ስለነበረ/ች
5= ከቤት ውጭ ሲዞር/ስትዞር ስለነበረ/ች
6= ሌላ (ይገለጽ) ____________________

## <u>ክፍል 9:-ባለፉት በማናቸውም ጊዜያት በሥራ ላይ ተሠማርተው ስለሚያውቁ ልጆ ች ከሠሩት ወይም ከሚሠሩት ሥራ ጋር በተያያዘ የጤና እና የደህንነት ሁኔታ የተ መለከቱ ጥያቄዎች</u>

በዚህ ክፍል ውስጥ የተካተቱ ጥያቄዎች የሚመለከቱት ባለፉት በማናቸውም ጊዜያት በሥራ ላይ ተሠማርተወ ው የሚያውቁ ዕድሜያአቸው ከ5-17 ዓመት የሆናቸውን ልጆች ሲሆን ልጆቹ ከሠሩት ወይም ከሚሠሩት ሥራ ጋር በተያያዘ የጤና እና የደህንነት ሁኔታን የዳሰሱ ዝርዝር ጥያቄዎች የሚቀርቡበት ነው። በዚህ ክፍል ል ጆች የሠሩት ወይም የሚሠሩት ሥራ የሚከተሉትን ያካትታል:-

1. ምርታማ ሥራን (በቅጽ 1 ዓምድ 24 ከተዘረዘሩት የሥራ ዓይነቶች መካከል አንዱን ወይም ከአንድ በላይ መሥራትን ወይም ማገዝን ያጠቃልላል) እና
2. በቅጽ 2 ክፍል 8 የተጠቀሱት ያለክፍያ የሚሠሩ ለቤተሰብ ግልጋሎት የሚውሉ ምርታማ ያልሆኑ ሥራዎችን መሥራትን ያካትታል።

<u>ማስታወሻ</u> በዚህ ክፍል ህመም/ጉዳት የሚለው ልጆቹ በሥራ ቦታ ላይ ወይም በሚሠሩት ሥራ ምክንያት የደ ረሰባቸው ጉዳት ወይም የህመም ስሜት ማለት ሲሆን ይህ ግን እንደ ህመም/ጉዳት የሚቆጠረው የህመሙ ወ ይም የጉዳቱ ስሜት ቢያንስ ለአንድ ቀን ከቀየባቸው ወይም ደግሞ በዚህ ምክንያት ልጆቹን ቢያንስ ለአንድ ቀን ሥራቸውን ለመሥራት እንዳይችሉ ከከለከላቸው ነው።

901.

<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) በማናቸውም ጊዜ በሥራ ላይ (በሥራ ቦታ) የደረሰበት/ባት ህመም /ጉዳት አለ? ወይም ደግሞ በሥራው ምክንያት ህመም ወይም የአካል ጉዳት ደርሶበት/ባት ያውቃል?</u>

በዚህ ጥያቄ ልጁ/ልጅቷ አሁን እየሠራ/ች ባለው/ችው ወይም ከአሁን በፊት በሠራቸው/ችው ሥራዎች በሥራ ላይ (በሥራ ቦታ) የደረሰበት/ባት ህመም/ጉዳት አለ? ወይም ደግሞ በሥራው ምክንያት ህመም ወይም/ጉዳት ደርሷል? ተብሎ የሚጠየቅ ሲሆን ደርሶ ከሆነ ኮድ 1፣ ካልደረሰ ደግሞ ኮድ 2 ይከበብና ወደ ጥያቄ 911 ይታለፋል ። ልጁ/ልጅቷ በማናቸውም ጊዜ ሥራ ሠርቶ/ታ የማያውቅ/የማታውቅ ከሆነ ኮድ 3 ይከበብና በዚሁ ቅጽ ክፍል 11 ወደሚገኘው ጥያቄ 1106 ይታለፋል።

902. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ህመሙ ወይም ጉዳቱ የደረሰበት/ባት ምን ያህል ጊዜ ነው?</u>

የዚህ ጥያቄ ዓላማ ከላይ በጥያቄ 901 በሥራ ላይ (ቦታ) ወይም በሥራው ምክንያት ህመም/ጉዳት ደርሶብኛል ተብሎ ኮድ 1 ከተከበበ ህመሙ/ጉዳቱ ምን ያህል ተደጋጋሚ እንደነበር ለማወቅ ሲሆን በዚህም መሠረት በልጁ/ልጅቷ ላይ ህመም /ጉዳት የደረሰው በተደጋጋሚ ከሆነ ኮድ 1፣ አልፎ አልፎ ከሆነ ኮድ 2 እንዲሁም በጣም አልፎ አልፎ ከሆነ ደግሞ ኮድ 3 ይከበባል።

እዚህ ላይ <u>በጣም አልፎ አልፎ</u> በሚለው ውስጥ መካተት የሚገባቸው 1 ወይም 2 ጊዜ ህመም/ጉዳት ለደረሰባቸው ሲሆን <u>አልፎ አልፎ</u> በሚለው ውስጥ መካተት የሚገባቸው ደግሞ 3 ወይም 4 ጊዜ ህመም/ጉዳት ለደረሰባቸው ነው እንዲሁም 5 ጊዜና ከዚያ በላይ ለደረሰባቸው <u>በተደጋጋሚ</u> የሚለው ኮድ ይከበብላቸዋል።

903.

<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ከደረሱበት/ባት ህመሞች/ጉዳቶች ውስጥ ከበድ ያለው ሕመም/ጉዳት በደረሰበት/ባት ጊዜ የሚሠራበት/የምትሠራበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሠጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድነው/ምን ነበር?</u>

በዚህ ጥያቄ ልጆችን ከበድ ላሉ ህመሞች/ ጉዳቶች የሚያጋልጡ ልጆች የሚሠሩባቸውን የድርጅት ዓይነቶችን ለመለየት ሲሆን በዚህም መሠረት ልጁ/ልጅቷ ከደረሰበት/ባት ህመሞች/ጉዳቶች ውስጥ ከበድ ያለው ሕመም/ጉዳት በደረሰበት/ባት ጊዜ የሚሠራበት/የምትሠራበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም ድርጅቱ የሚሠጠው አገልግሎት ዓይነት ተጠይቆ በተሠጠው ክፍት ቦታ ላይ ይገለፃል። የድርጅት ዋና ምርት ወይም ድርጅቱ የሚሰጠው አገልግሎት በሚሞላበት ጊዜ ችግር እንዳይፈጥር ሰፋ ያለ ማብራሪያ በቅጽ 1 ዓምድ 32 አሞላል ላይ ስለተገለፀ ከዚያ መመልከት ይቻላል።

904.

<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ከደረሱበት/ባት ህመሞች/ጉዳቶች ውስጥ ከበድ ያለው ህመም/ጉዳት የደረሰበት/ባት ምን ዓይነት ሥራ በሚሠራበት/በምትሠራበት ወቅት ነው/ነበር?</u>

በዚህ ጥያቄ ልጆችን ከበድ ላሉ ህመሞች/ ጉዳቶች የሚያጋልጡ የሥራ ዓይነቶችን ለመለየት የተፈለገ ሲሆን በዚህም መሠረት ልጁ/ልጅቷ ከደረሰበት/ባት ህመሞች/ጉዳቶች ውስጥ ከበድ ያለው ሕመም/ጉዳት የደረሰበት/ባት ምን ዓይነት ሥራ በሚሠራበት/ በምትሠራበት ወቅት እንደነበር ተጠይቆ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ይገለፃል። የሥራ ዓይነት በሚሞላበት ጊዜ ለቅጽ 1 ዓምድ 30 አሞላል በዝርዝር የተሰጡትን የሥራ ዓይነቶች መመልከት ይቻላል።

905.

<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ህመም/ጉዳት ደርሶበት/ባት ከሆነ የህመሙ/የጉዳቱ ዓይነት ምንድን ነው/ነበር? (እስከ ሦስት ጉዳቶች ይዘርዝሩ)</u>

ልጁ/ልጅቷ ከአሁን በፊት ባከናወኗቸውም ሆነ አሁን እየሰሩ ባሏቸው ሥራዎች ምክንያት ከደረሱባቸው ህመሞች /ጉዳቶች መካከል እስከ ሦስት የሚሆኑ ህመሞች/ጉዳቶች በተሰጠው ክፍት ቦታ ይዘረዘራሉ።

ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆኑ ህመሞች እና አደጋዎች በሚሞሉበት ጊዜ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተገናዝበው በሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ተለይተው ከተዘረዘሩት ዋና ዋና የህመምና የጉዳት አይነቶች ጋ ር የተጣጣሙ መሆን ስላለባቸው ለዚህ እንዲረዱ ከዚህ በታች ተሰጥተዋል። ምናልባት ከመልስ ሰጭዎች የምናገ ኛቸውን አንዳንድ የህመምና የጉዳት አይነቶች ከተዘረዘሩት ጋር ለማጣጣም አስቸጋሪ ሆነው ልናገኛቸው ስለምንች ል ለቢሮ አሠራር የሚረዱ አስተያየቶችን በመፃፍ እንዳሉ እናስቀምጣቸዋለን። ለምሣሌ ከታች ከተዘረዘሩት መካከ ል የእጅ ወይም የእግር መቆረጥ ማለት አንድ ስለት ወይም ሌላ ነገር የእጅን ወይም የእግርን ክፍል ሲቆርጥ ነገ ር ግን የተቆረጠው ክፍል ከሰውነቱ ሳይለያይ ሲቀር ነው። የእጅ ወይም የእግር መጎረድ ማለት ግን የተቆረጠው ክፍል ከሰውነቱ ሙሉ በሙሉ ሲለያይ ነው። እንደዚሁም የመተንፈስ ችግር ማለት በሥራ ላይ ወይም ቦታ በተ ከሰተ ችግር ለተወሰነ ጊዜ/ለዘለቄታው ያጋጠመ ወይም በዚህ ምክንያት በመተንፈሻ አካል ላይ የደረሰ ህመም ማ ለት ሲሆን መታፈን/Suffocation/ ማለት ደግሞ በሥራ ላይ ወይም ቦታ በተከሰተ ችግር ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ለመተንፈስ አለመቻል ማለት ነው።

- አጠቃላይ በሽታ ለምሳሌ እንደ ትኩሳት፣ ብርድ ወዘተ...
- የዓይን ህመም
- የጆሮ ህመም
- የቆዳ ህመም
- የመተንፈስ ችግር
- የማጅራት በሽታ
- የወገብ በሽታ
- ደም ማነስ
- የአካል መላጥና/መቀጥቀጥ
- የአካል መቃጠል
- የእጅ/የእግር መቆረጥ
- የእጅ/የእግር መጎረድ
- የአካል መወጋት
- ውልቃት
- የአካል መሰበር
- የስር መዞር
- የዓይን ጉዳት
- የጆሮ ጉዳት
- መታፈን
- የመስመጥ ችግር
- ሌላ በሽታ (ይገለጽ)
- ሌላ ጉዳት (ይገለጽ)

906.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) የደረሰበት/ባት ህመም/ጉዳት ሥራ ለመሥራት እንዳይችል/ትችል ከልክሎታል/ሏታል?**

ይህ ጥያቄ በጥያቄ 905 ከሥራ ጋር በተያያዘ ምክንያት ጉዳት ወይም ህመም ደርሶብናል ብለው የመለሱ በደረሰ ባቸው ህመም ወይም ጉዳት ምክንያት ሥራ ከመሥራት መተጓጎል አለመተጓጎላቸው የሚጠየቅበት ሲሆን ህመሙ ወይም ጉዳቱ ለጊዜው ከሥራ አስተጓጉሏቸው ከሆነ ኮድ 1፣ ለዘለቄታው ከሥራ ካገዳቸው ኮድ 2 እንዲሁም ሥ ራ ከመሥራት ካላገዳቸው ኮድ 3 ይከበብላቸዋል።

907.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) ላይ ከደረሱ ህመሞች ወይም ጉዳቶች መካከል ከፍተኛ በሆነው ህመ ም/ጉዳት ምክንያት ምን ዓይነት ህክምና ተደርጎለታል/ላታል?**

ይህ ጥያቄ በሠሩት ሥራ ምክንያት ከደረሰባቸው ህመም/ጉዳት መካከል ከፍተኛውን የሚመለከት ነው። ለዚህ ከ ፍተኛ ለሆነው ህመም/ጉዳት ምን ዓይነት ህክምና ተወስዶ እንደሆነ ለማወቅ የተፈለገ ሲሆን ከ1-5 ከተዘረዘሩት አማራጮች ውስጥ የተገቢው ኮድ ይከበባል። ባህላዊ ወይም ዘመናዊ ህክምና ተደርጎለታል/ላታል የሚሉ ከሆነ በ ቅደም ተከተላቸው መሠረት ኮድ 1 ወይም 2 ተከቦላቸው ወደ ጥያቄ 910 ወይም 909 ያልፋሉ። ዘመናዊ ህክ ምና ሲባል በሆስፒታል፣ በጤና ጣቢያ/ክሊኒክ...ወዘተ. መታከምን ነው። እንደሁም በዘመናዊ ህክምና ተቋም ተ ኝተው ህክምና ከወሰዱ ኮድ 3 ተከቦላቸው በሚቀጥለው ጥያቄ በህክምና ላይ የቆዩበት ቀን ተጠይቆ ይሞላላቸዋ ል። ምንም ህክምና ካልወሰዱ ኮድ 4 የሚከበብ ሲሆን ከዚህ የተለየ መልስ ከሰጡ ኮድ 5 ተከቦላቸው ሁለቱም ወ ደ ጥያቄ 911 ያልፋሉ።

908.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) በህክምና ተቋም ተኝቶ/ታ የታከመባቸው/ችባቸው ቀናት ብዛት ም ን ያህል ነበር?**

ልጁ/ልጅቷ በደረሰበት/ባት ህመም/ጉዳት ምክንያት በህክምና ተቋም ተኝቶ/ታ ህክምና የወሰደበት/ችበት ቀን ብ ዛት ተጠይቆ በተሰጠው ካርድ ኮለም ውስጥ ይሞላል። 97 ቀንና ከዚያ በላይ በህክምና ተቋም ተኝተው ለታከሙ ኮድ '97' ይሞላል።

909. **(የልጁ/ጅቷ ስም) በጤና ባለሙያ የታከመው/የታከመችው የት ነው?**

ይህ ጥያቄ ልጁ/ልጅቷ በደረሰበት/ባት ህመም/ጉዳት ምክንያት በጤና ባለሙያ የታከመበት/ችበት ቦታ የሚጠየ ቅበት ነው። ይህ ጥያቄ የሚመለከታቸው ግን ከላይ በጥያቄ 907 ኮድ 2 ወይም 3 ለመለሱ ብቻ ነው። እዚህ ላ ይ ልጁ/ልጅቷ በማናቸውም ጊዜ በሥራ ላይ/በታ ለደረሱበት/ባት ህመሞች/ ጉዳቶች በጤና ባለሙያ የታከመባ ቸውን/የታከመችባቸውን ቦታዎች ለመለየት አማራጮቹን አንድ በአንድ በማንበብ እየተጠየቀ ልጁ/ጅቷ በተጠቀሰ ው ቦታ ታክሞ/ማ ከሆነ አዎን በሚለው አንፃር ኮድ 1፣ በተጠቀሰው ቦታ ካልታከመ/ች ደግሞ የለም በሚለው አንፃር ኮድ 2 ይከበባል። ልጁ/ልጅቷ በደረሰበት/ባት ህመም/ጉዳት ምክንያት በጤና ባለሙያ የታከመው/ችው ቤት ውስጥ ወይም ሌላ ቦታ ከሆነ "ሌላ(ይገለፅ)" በሚለው አንፃር ኮድ 1 ተከቦ የታከመበት/ችበት ቦታ ይገለፃል።

A= ሥራ ቦታ
B= ሆስፒታል/ጤናጣቢያ
C= መድሐኒት ቤት
D= ክሊኒክ/ጤና ኬላ
E= ሌላ(ይገለፅ) ____________________

910. **(የልጁ/ጅቷ ስም) ለህክምና የወጣውን ወጭ ማን ከፈለ?**

ይህ ጥያቄ ልጁ/ልጅቷ በደረሰበት/ባት ህመም/ጉዳት ምክንያት ለወሰደው/ችው ህክምና የወጣውን ወጭ የከፈለው ማን እንደሆነ የሚጠየቅበት። በመሆኑም የተሰጡትን አማራጮች አንድ በአንድ በማንበብ አዎን በሚለው አንፃር ኮድ 1 ወይም ደግሞ የለም በሚለው አንፃር ኮድ 2 ይከበባል። ከተሰጡት አማራጮች መካከል ነፃ ህክምና የሚ ባለው ህክምናው ክፍያ የሚያስፈለገው ሆኖ እያለ ነገር ግን ወጭው በመንግሥት፣ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ በ ግለሰቦች፣ ወዘተ... ሲሸፈን ነው። ነገር ግን ልጁ/ልጅቷ የወሰደው/ችው ህክምና ምንም ዓይነት ክፍያ የማይጠይቅ ከሆነ ህክምናው ክፍያ አላስፈለገውም ይባላል።

A= ወላጅ/አሳዳጊ
B= አሠሪ/ከወላጅ ወይም ከአሳዳጊ ውጭ
C= ልጁ/ጅቷ ራሱ/ሷ
D= ነፃ ሕክምና
E= ክፍያ አላስፈለገውም
F= ሌላ(ይገለፅ) ____________________

911. **መረጃ ሰብሳቢ፦ (የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፉት 7 ቀናት ምርታማ ሥራ ሠርቷል/ታለች?**

**(የማጣሪያ ጥያቄ)** ይህ ጥያቄ በቀጥታ ለመልስ ሰጭዎች የሚቀርብ ሳይሆን መረጃ ሰብሳቢው ወደ ኋላ ተመልሶ ጥ ያቄ 804ን በመመልከት የሚያጣራው/የምታጣራው ነው። በዚህም መሠረት ልጁ/ልጅቷ ባለፈው ሳምንት በሥራ ላይ ከነበረ/ች ኮድ 1 ተሞልቶ ወደሚቀጥለው ጥያቄ የሚታለፍ ሲሆን ባለፈው ሳምንት በሥራ ላይ ካልነበረ/ች ደግሞ ኮድ 2 ይሞላና ወደ ጥያቄ 1105 ይታለፋል።

912. **(የልጁ/ጅቷ ስም) በሥራ ላይ እያለ/ች የአደጋ/ጉዳት መከላከያዎች ይጠቀማል/ትጠቀማለች? የሚጠቀም/የምትጠቀም ከሆነ ምን ዓይነት የአደጋ/ጉዳት መከላከያዎች ይጠቀማል/ ትጠቀማለች?**

የዚህ ጥያቄ አላማ በምርታማ ሥራ ላይ የተሰማሩ ልጆች የአደጋ/ጉዳት መከላከያዎችን መጠቀም አለመጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን ይህ ጥያቄ በቀጥታ ለመልስ ሰጭው ከቀረበ በኋላ ልጁ/ጅቷ ይጠቀሙባቸዋል ብሎ ለሚጠራቸው የአደጋ/ጉዳት መከላከያዎች ኮድ 1 ይከበባል። ያልጠራቸውን አማራጭ የአደጋ/ጉዳት መከላከያዎች ደግሞ አንድ በአንድ በማንበብ ልጁ/ጅቷ ለተጠቀመባቸው አዎን በሚለው አንፃር ኮድ 1 ላልተጠቀመባቸው ደግሞ የለም በሚለው አንፃር ኮድ 2 ይከበባል። ለዚህ ጥያቄ የተሰጡ አማራጮች ባብዛኛው ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋ ር የማይጣጣሙ ቢመስሉም ነገር ግን በአለም አቀፍ ደረጃ እንዲያገለግሉ ተለይተው የቀረቡ ናቸው። ነገር ግን የተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ሊያጋጥሙን የሚችሉ በርካታ ሀገር በቀል የአደጋ/ጉዳት መከላከያዎችን በሙሉ ስ ላልያዙ ከተዘረዘሩት ውጭ ሲያጋጥም ሌላ በሚለው አንፃር ኮድ 1 ይከበብና በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ በደንብ ሊገ

ለፅ ይገባል፡፡ ለምሣሌ ልጁ/ጅቷ ሥራ በሚሠራበት/ በምትሠራበት ጊዜ የሚጠቀምበትን/የምትጠቀምበትን የሰሌን ባርኔጣ፡-

¨ ቦት ጫማ፣ ወዘተ... መልስ ሰጭው ለአደጋ/ጉዳት መከላከያ ብለው ነው የሚጠቀሙበት ካለን ሌላ ይገለፅ በሚለው አንፃር ኮድ 1 በማክበብ የሰሌን ባርኔጣውን፣ ቦት ጫማውን ወዘተ... በተሰጠው ቦታ ላይ እንገልፃለን፡፡ ልጁ/ጅቷ ሥራ በሚሠራበት/ በምትሠራበት ጊዜ ምንም ዓይነት የአደጋ/ጉዳት መከላከያዎችን የማይጠቀም/የማትጠቀም ከሆነ ምንም አይጠቀምም/አትጠቀምም በሚለው አማራጭ አንፃር ኮድ 1 ይከበባል፡፡

A= መከላከያ መነጽር
B= መከላከያ ቆብ
C= የጆሮ ውታፍ/ልባስ
D= ልዩ የሥራ ጫማ
E= የእጅ ጓንት
F= ሌላ (ይገለጽ)______________________
G= ምንም አይጠቀምም/አትጠቀምም

## 913. (የልጁ/ጅቷ ስም) የሚሠራውን/የምትሠራውን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች የአደጋ መከላከያ ያደርጋሉ/ይጠቀማሉ?

ይህ ጥያቄ ልጁ/ልጅቷ የሚሠራቸውን/የምትሠራቸውን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች የአደጋ መከላከያ መጠቀም አለመጠቀማቸውን በመጠየቅ የአደጋ መከላከያ አጠቃቀምን በተመለከተ ልጆች ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸውን ንፅፅር ለማየት የሚረዳ ሲሆን የሚጠቀሙ ከሆነ ኮድ 1፣ የማይጠቀሙ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ተሞልቶ ወደ ጥያቄ 915 ይታለፋል፡፡

## 914. (የልጁ/ጅቷ ስም) የሚሠራውን/የምትሰራውን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች ምን ዓይነት የአደጋ መከላከያ ይጠቀማሉ?

ይህ ጥያቄ በቀጥታ ለመልስ ሰጭው ከቀረበ በኋላ ልጁ/ጅቷ የሚሠራውን/የምትሰራውን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች ይጠቀሙባቸዋል ብሎ ለሚጠራቸው የአደጋ/ጉዳት መከላከያዎች ኮድ 1 ይከበባል፡፡ ያልጠራቸውን አማራጭ የአደጋ/ጉዳት መከላከያዎች ደግሞ አንድ በአንድ በማንበብ ሌሎች ሰዎች ለተጠቀሙባቸው አዎን በሚለው ዓምድ ስር ኮድ 1 ላልተጠቀሙባቸው ደግሞ የለም በሚለው ዓምድ ስር ኮድ 2 ይከበባል፡፡

A= መከላከያ መነጽር
B= መከላከያ ቆብ
C= የጆሮ ውታፍ/ልባስ
D= ልዩ የሥራ ጫማ
E= የእጅ ጓንት
F= ሌላ (ይገለጽ)______________________

## 915. (የልጁ/ጅቷ ስም) በሚሠራው/በምትሠራው ሥራ ምክንያት ሊያጋጥሙት/ሚት የሚችሉ የጤና ችግሮች አሉ ብሎ ያስባል/ታስባለች?

የዚህ ጥያቄ ዓላማ በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ ልጆች በሚሰሩት ሥራ ምክንያት ለጤና ችግሮች ሊጋለጡ ስለሚችሉ ይህ ሁኔታ አለ ብለው ልጆቹ ማሰብ አለማሰባቸውን ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን ለመጠየቅ ሲሆን የጤና ችግሮች አሉ ብለው የሚያስቡ ከሆነ ኮድ 1 ካልሆነ ደግሞ ኮድ 2 ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ይህን በተመለከተ የሚያውቁት ነገር ከሌለ ኮድ 3 ይሞላል፡፡

# ክፍል 10. ቤተሰብ/አሳዳጊ ላልሆነ ለሌላ ሠው በክፍያ (በገንዘብ ወይም በዓይነት) ወይም ያለ ክፍያ ተቀጥረው ስለሚሠሩ ልጆች (ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት ስለሆኑልጆች)

ይህ ክፍል ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት የሆናቸው ልጆች ቤተሰብ/አሳዳጊ ላልሆነ ለሌላ ሰው በክፍያ (በገንዘብ ወይም በዓይነት) ወይም ያለክፍያ ተቀጥረው በሚሠሩበት ጊዜ ከአሠሪዎቻቸው ጋር ስላላቸው ግንኙነት፣ ስለሚያገኟቸው ጥቅማ ጥቅሞችና ስለመሳሰሉት ጥያቄዎች የሚቀርቡበት ክፍል ነው፡፡

## 1001. (የልጁ/ጅቷ ስም) በአሁኑ ወቅት የሚሠራው/ የምትሠራው ለማን ነው?

ይህ ጥያቄ ልጁ/ጅቷ የሚሠራው/የምትሠራው ለማን እንደሆነ የሚጠየቅበት ሲሆን ለወላጅ/አሳዳጊ ኮድ 1 ተከቦ ወደ ጥያቄ 1101 ይታለፋል፡፡ ከሚኖርበት ቤተሰብ ውጭ ለሆነ ለሌላ ሰው/ድርጅት የሚሠራ/የምትሠራ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ተከቦ ወደ ቀጣዩ ጥያቄ ይታለፋል፡፡ ልጁ/ጅቷ ከቤተሰቡ ጋር እየኖረ/ች ተቀጥሮ/ራ ለቤተሰቡ በ

ቤት ውስጥ ሠራተኛነት (የቤት ሠራተኞችን፣ ዘበኞችን፣ አትክልተኞችን፣ የቤተሰብ ሾፌሮችን፣ ወዘተ... ይካትታል) የሚሠራ/የምትሠራ ከሆነ ኮድ 3 የሚከበብ ሲሆን ከቤተሰቡ ጋር እየኖረ/ች በቤተሰቡ ድርጅት ውስጥ ተቀጥሮ/ ራ የሚሠራ/የምትሠራ ከሆነ ደግሞ ኮድ 4 ይከበባል(ይህም
የድርጅት ዘበኞችን፣ አትክልተኞችን፣ ሾፌሮችን፣ ወዘተ... ሊያካትት ይችላል)፡-
፡ ኮድ 3 ወይም 4 የተሞላላቸው ወደ ጥያቄ 1103 እንዲያልፉ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም ልጁ/ጅቷ የሚሠራው/የም ትሠራው ለራሱ/ሷ ከሆነ ኮድ 5 ይከበብና ወደ ጥያቄ 1101 ይታለፋል፡፡

1002. (የልጁ/ጅቷ ስም) ለሌላ ሠው/ድርጅት የሚሠራ ከሆነ ከአሠሪው/ዋ ወይም ከቀጣሪው/ዋ ጋር ያለው/ያላት ግንኙነት ምን ይመስላል?

በዚህ ክፍል የሚጠየቁት በጥያቄ 1001 ኮድ 2 ለተከበበላቸው ሲሆን ልጁ/ልጅቷ ከአሠሪው/ዋ ወይም ከቀጣሪው /ዋ ጋር ያለው/ያላት ግንኙነት ምን እንደሚመስል የሚጠየቅ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ግንኙነቱ/ቷ ጥሩ ከሆነ ኮ ድ 1 ይከበብና ወደ ጥያቄ 1004 ይታለፋል፣ መጥፎ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ይከበብና ወደቀጣዩ ጥያቄ የሚታለፍ ሲሆን ልጁ/ልጅቷ ከአሠሪው/ዋ ወይም ከቀጣሪው/ዋ ጋር ስላለው/ስላላት ግንኙነት መልስ ሰጭው አስቦበት የማ ያውቅ ወይም ግድ የሌለው ከሆነ ኮድ 3 ተከቦ ወደ ጥያቄ 1004 ይታለፋል፡፡

1003.

(የልጁ/ጅቷ ስም) ከአሠሪው/ዋ ወይም ከቀጣሪው/ዋ ጋር ያለው/ያላት ግንኙነት መጥ ፎ ከሆነ ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?

ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1002 ከአሠሪያቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት መጥፎ እንደሆነ ለተገለፀላቸው ልጆች ግንኙ ነቱ መጥፎ የሆነበትን ምክንያት ለማወቅ የሚያስችል ነው፡፡ አማራጭ መልሶችም ከኮድ 1-7 ተዘርዝረዋል፡፡ አንዳ ንድ ጊዜ ሴት ልጆች በሴትነታቸው በአሠሪያቸው የመደፈር ሁኔታ ሊያጋጥም ስለሚችል አስገድደው ለመድፈር ስለሞከሩ ወይም ስለደፈሯት የሚል መልስ ከተገኘ ሌላ በሚለው ላይ መገለፅ ይኖርበታል፡፡ ለመልስ ሰጭው ከA -G የተሰጡትን አማራጭ መልሶች በማንበብ ለእያንዳንዱ ጥያቄ "አዎን" ኮድ 1፡-
፡ ወይም "የለም" ኮድ 2 እየተከበበ የሚመለስ ይሆናል፡፡ ግንኙነቱ መጥፎ የሆነበት ምክንያት ከተዘረዘሩት ውጭ ከሆነ ደግሞ ሌላ በሚለው አንፃር ኮድ 1 ይከበብና በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ይገለፃል፡፡

A= ከአቅም በላይ ብዙ እንዲሠራ/ድትሠራ ይፈለጋል
B= ለረጅም ሰዓት እንዲሠራ/ድትሠራ ይፈለጋል
C= ክፍያው ትንሽ ነው
D= በወቅቱ አይከፈልም
E= ይደበደባል/ትደበደባለች
F= በቃላት ይተነኩሱታል/ያጥላሉታል
G= ሌላ (ይገለጽ) ____________________

1004. ከሚከተሉት ጥቅማ ጥቅሞች ውስጥ ቀጣሪው የትኞቹን ለ (የልጁ/ጅቷ ስም) ይሰጣል?

የዚህ ጥያቄ አላማ ቤተሰብ/አሳዳጊ ላልሆነ ለሌላ ሠው ተቀጥረው የሚሠሩ ልጆች ከቀጣሪዎቻቸው ጥቅማ ጥቀሞ ችን ማግኘት አለማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን የሚያገኙ ከሆነ ደግሞ የጥቅማ ጥቅሞቹ ዓይነቶች ምን እንደሆ ኑ ለመለየት ነው፡፡ በዚህም መሠረት አማራጭ ጥቅማ ጥቀሞችን አንድ በአንድ በማንበብ ልጁ/ጅቷ የሚያገኙ ከ ሆነ አዎን በሚለው አምድ ስር ኮድ 1 ይከበብላቸዋል ካልሆነ ደግሞ የለም በሚለው ዓምድ ሥር ኮድ 2 ይከበብላ ቸዋል፡፡ ከተጠቀሱት ጥቅማ ጥቀሞች ውጭ የሚያገኙ ከሆነ ሌላ በሚለው አንፃር ኮድ 1 በማክበብ ለዚህ በተሰጠ ው ቦታ ላይ መገለፅ የሚገባው ሲሆን፣ መልስ ሰጭው ልጆቹ ጥቀሞችን ማግኘት አለማግኘታቸውን የማያውቅ ከ ሆነ አላውቅም በሚለው አንፃር ኮድ 1 ይከበብለታል፡፡ እንዲሁም አሠሪው ምንም ጥቅማጥቅም የማይሰጥ ከሆነ "J. ምንም ዓይነት ጥቅማ ጥቅም አይሰጥም" በሚለው አኳያ ኮድ 1 ይከበባል፡፡

A. እረፍት ወይም የሕመም ፈቃድ ከክፍያ ጋር
B. ማህበራዊ ዋስትና ፣የጤና ኢንሹራንስ
(ጡረታ፣ የሕይወት ኢንሹራንስ ... ወዘተ)
C. ቦነስ (በየጊዜው)
D. ነፃ ወይም በከፊል ክፍያ ዩኒፎርም(የሥራ ልብስ)
E. ነፃ ምግብ
F. ለምግብ ከፊል ክፍያ
G. ነፃ ወይም በከፊል ክፍያ ትራንስፖርት
H. ነፃ ወይም በከፊል ክፍያ መኖሪያ
I. ሌላ (ይገለጽ)____________________

J. ምንም ዓይነት ጥቅማ ጥቅም አይሰጥም
K. አላውቅም

## ክፍል 11. በምርታማ ሥራ የተሠማሩ ልጆች በመደበኛነት የሚኖሩባቸው ወላጆች (አሳዳጊዎች ) ስለ ልጆቹ (ዕድሜአቸው ከ5-17 ዓመት የሆናቸው) ያላቸው አመለካከት፣

### 1101. (የልጁ/ጅቷ ስም) ሥራ ቢተው/ብትተው በቤተሰቡ ላይ ምን ችግር ይመጣል?

በዚህ ጥያቄ ልጁ/ልጅቷ አሁን እየሠራ/ች ያለውን/ችውን ሥራ ቢተው/ብትተው በቤተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለው ችግር ምን እንደሆነ ተጠይቆ ከታች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ዋነኛውን በመለየት ኮዱ ይከበባል።

1= የቤተሰቡ የኑሮ ደረጃ ይቀንሣል
2= ቤተሰቡ ለኑሮ የሚያስፈልገውን ለማሟላት ይሣነዋል
3= እሱን/እሷን የሚተካ ሰው ለመቅጠር ስለማይቻል
የቤተሰብ ድርጅት እንቅስቃሴ ይጓተታል
4=ምንም ችግር አያመጣም
5= ሌላ (ይገለጽ)____________________

### 1102A. እንደ እርስዎ ፍላጎት ቢሆን (ልጁ/ልጅቷ ) አሁን ምን ቢያደርግ/ብታደርግ ይመርጣሉ?

በዚህ ጥያቄ ወላጆች/አሳዳጊዎች ፍላጎታቸው የሚሟላ ቢሆን አብረዋቸው በመደበኛነት የሚኖሩ በምርታማ ሥራ ላይ የተሰማሩ ልጆች አሁን ምን ቢያደርጉ እንደሚፈልጉ የሚጠየቁ ሲሆን ከዚህ በታች በዝርዝር ከቀረቡት አማራጮች መካከል የአንድ ዋነኛ መልስ ኮድ ይከበባል።

01= ሙሉ ቀን ቢማር/ብትማር
02= ገቢ በሚያስገኝ የሙሉ ቀን ሥራ ቢሠራ/ብትሠራ
03= በቤተሰብ ድርጅት ውስጥ ሙሉ ቀን እንዲሰራ/እንድትሠራ
04= ምርታማ ባልሆኑ የቤት ውስጥ ሥራዎች (እንደ ቤት ጥበቃ የመሣሰሉት ጨምሮ) ሙሉ ቀን እንዲሰራ/እንድትሠራ
05= ግማሽ ቀን እየሠራ/ች ግማሽ ቀን እንዲማር/እንድትማር
06= በትርፍ ጊዜ ለቤተሰብ ድርጅት እንዲሰራ/እንድትሠራ
07= ምርታማ ባልሆኑ የቤት ውስጥ ሥራዎች በትርፍ ሰዓት ብቻ እንዲሰማራ/ድትሠማራ
08=ትምህርት ወይም ሥልጠና አጠናቆ ሥራ እንዲጀምር/ድትጀምር
09=ከአሁኑ ሥራ የተሻለ ሥራ እንዲፈለግ/እንድትፈልግ
10= ሌላ (ይገለጽ)____________________

### 1102B.እንደ እርስዎ ፍላጎት ቢሆን (ልጁ/ልጅቷ ) ወደፊት (ሲያድግ/ስታድግ) ምን ቢያደርግ/ብታ ደርግ ይመርጣሉ?

በዚህ ጥያቄ ደግሞ ወላጆች/አሳዳጊዎች ፍላጎታቸው የሚሟላ ቢሆን አብረዋቸው በመደበኛነት የሚኖሩ በምርታማ ሥራ ላይ የተሰማሩ ልጆች ወደፊት ሲያድጉ ምን ቢያደርጉ እንደሚፈልጉ የሚጠየቁ ሲሆን በዝርዝር ከቀረቡት አማራጮች መካከል የአንድ ዋነኛ መልስ ኮድ ይከበባል። ለአማራጭ መልሶቹ ጥያቄ 1102Aን ይመልከቱ።

### 1103. (የልጁ/ጅቷ ስም) ሥራ በማይሰራበት/በማትሰራበት ወቅት ምን ያደርጋል ወይም ታደርጋለች ?

በዚህ ጥያቄ በምርታማ ሥራ የተሠማሩ ልጆች ሥራ በማይሠሩበት ወቅት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጭ ለመዝናናት ብለው የሚያደርጓቸውን ነገሮች ለማወቅ የተፈለገ ሲሆን የተዘረዘሩትን አማራጮች እንደ ልጁ እና እንደ አካባቢው ሁኔታ በማንበብ አዎን በሚለው አንፃር ኮድ 1 ወይም የለም በሚለው አንፃር ኮድ 2 ይከበባል። የተለየ መልስ ካለ ደግሞ ሌላ በሚለው አንፃር ኮድ 1 በማክበብ ለዚህ በተሰጠው ቦታ ላይ መገለፅ ያስፈልጋል።

A= መጫወት (ከጓደኞች፣ እህት፣ ወንድም፣ .. ወዘተ)
B= ቲቪ/ቪድዮ ማየት፣ ሬድዮ ማዳመጥ፣ ማንበብ
C= ማጥናት
D= ዘመድ/ጓደኛ መጠየቅ
E= ሌላ (ይገለጽ)____________________

### 1104. (የልጁ/ጅቷ ስም) ወደ ሥራ የገፋፋው/ት ዋና ምክንያት ምንድን ነው?

የዚህ ጥያቄ ዓላማ በምርታማ ሥራ ላይ የተሠማሩ ልጆች ወደ ሥራ ከሚገፋፉባቸው ምክንያቶች መካከል ዋነኛዎቹን ለመለየት ሲሆን በዚህም ከታች ከተዘረዘሩት ምክንያቶች መካከል ልጁን/ልጅቷን ወደ ሥራ የገፋፋው/ት ዋነኛ ምክንያት ኮዱ ይከበባል።

1= ለቤተሰብ ገቢ ለማስገኘት
2= ያልተከፈለ ዕዳ ለመክፈል
3= የቤተሰብን ድርጅት ለማገዝ
4= የትምህርት (ሥልጠና) ፕሮግራም ስላልተመቻቸ
5= የትምህርት (ሥልጠና) ቦታዎች ስለሚርቅ
6= ሥራ ለመልመድ
7= ሌላ (ይገለጽ)____________________

## 1105. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ መሥራት የጀመረው/ችው በስንት ዓመቱ/ቷ ነው?</u>

*ምርታማ ውይም ምርታማ ባልሆነ የቤት ውስጥ ሥራ የተሰማሩ ልጆች ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራ መስራት የጀመሩብ ት ዕድሜ ስንት እንደሆነ ተጠይቆ ዕድሜው በሙሉ ዓመት በተሰጠው ካርድ ኮለም ውስጥ ይሞላል።*

*<u>ማስታወሻ፡-</u> ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው። ለተጨማሪ ማብራሪያ የቅጽ 1 ዓምድ 16 አሞላልን መመልከት ይ ቻላል።*

## 1106. <u>መረጃ ሰብሳቢ፡-</u> <u>ስለ ልጁ/ ልጅቷ መልስ የሰጠው የቤተሰብ አባል ተራ ቁጥር</u> (ከቅጽ 1 ዓም ድ 12 የሚወሰድ)

*ይህ ጥያቄ መረጃ ሰብሳቢው ራሱ ወደኋላ ተመልሶ ቅጹን ለመሙላት መልስ የሰጠውን የቤተሰብ አባል ተራ ቁጥ ር ከቅጽ 1 ዓምድ 12 ወስዶ የሚሞላበት ነው እንጂ ለመልስ ሰጭው በቀጥታ የሚቀርብ አይደለም።*

# ምዕራፍ 6

## ቅፅ 3 በልጆች (ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት ለሆናቸው) መመለስ የሚገባቸው ጥያቄዎችና የአሞላል መመሪያ

### ክፍል 12፣ ዕድሜአቸው ከ10 - 17 ዓመት የሆኑ ልጆች የትምህርት ፣ የሥራ ሁኔታና በስራ ላይ ስለሚደርሱ ጉዳቶችና ህመሞች፣

**መግቢያ**

ይህ ቅፅ ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት የሆኑ ልጆችን የሚመለከት ሲሆን ስለ ትምህርት/ስልጠና፡ ትምህር ታቸው በሥራ ላይ ስለሚያስከትለው ተፅዕኖ፣ የሥራና የግንኙነታቸው ሁኔታ፣ የሥራ ዕርካታና የክፍያ ሁኔታ፣ በስራ ላይ ስለሚደርሱ ጉዳቶች/ህመሞች፣ የአደጋ/የጉዳት መከላከያ መጠቀምን፣ የሚያጠቃልል ነ ው። በዚህ ቅጽ የተካተቱት ጥያቄዎች በቅጽ 2 ከቀረቡት በተለየ መልኩ ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት የሆኑ ልጆች ተጠይቀው የሚመልሷቸው ናቸው። በመሆኑም ጥያቄዎቹ መቅረብ የሚገባቸው ለልጆቹ ለ ራሳቸው ነው። በቅፅ 2 ለቤተሰብና ለአሳዳጊ የቀረቡ ጥያቄዎች በድጋሚ ልጆቹ ራሳቸው ተጠይቀው እ ንዲመልሱ የተደረጉ ጥያቄዎች ይኖራሉ። ይህም የመረጃውን ተመሳሳይነትና ጥራት ለመለካት ያስችላል። ለቀረቡት ጥያቄዎች ከአንድ በላይ መልስ ቢሰጥ ጥያቄው ከአንድ በላይ መልስ የማይፈልግ ከሆነ መረጃ ሰብሳቢው <u>ዋነኛውን</u> ተብሎ የተሰጠው መልስ መውሰድ ይገባዋል። መረጃ ሰብሳቢ በይለፍ (Skip rule) ወቅት ስህተት እንዳይሰራ በማሰብ አልፎ አልፎ የማጣሪያ ጥያቄዎች (Filtering questions) ቀርበዋል። እነዚህም የማጣሪያ ጥያቄዎች ለመልስ ሰጪው የሚቀርቡ ሳይሆን መረጃ ሰብሳቢ ው አገናዝቦ ለማጣራት እንዲያስችለው ተብሎ የቀረቡ ናቸው። ስለዚህ መረጃ ሰብሳቢው በማጣሪያው ላ ይ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተመልሶ በመመልከት ተገቢውን ኮድ ይከብላቸዋል።

1201.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) በያዝነው የትምህርት ዘመን ትምህርት እየተከታተልክ/ሽ ነው? ምን ዓይነት ትምህርት?**

በዚህ ጥያቄ ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት የሆኑ ልጆች የትምህርት ሁኔታ የሚጠየቅበት ነው። ይህ ጥያ ቄ መደበኛ ትምህርት (በመንግስት ት/ቤቶች፣ በግል ት/ቤቶች ... ወዘተ) እና መደበኛ ያለሆነ ትምህር ት (ለምሳሌ በቄስ፣ በቁርአን ት/ቤቶች፣ በመዋዕለ ፅፃናት ትምርት እንዲሁም በመሠረተ ትምህርት) እየ ተከታተሉ ያሉትን የሚመለከት ነው። በጥናቱ ወቅት መደበኛ ትምህርት ለሚከታተሉ ኮድ 1 ይከበባል። የሙያ/የቴክኒክ ሥልጠና ለሚወስዱ ወይም ለሚከታተሉ ኮድ 2 ተከቦ ወደ ጥያቄ 1204 ይታለፋል። መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ለሚከታተሉ ኮድ 3 ተከቦ ወደ ጥያቄ 1203 ይታለፋል፣ እንዲሁም የለም አ ልማርም ብለው ኮድ 4 የመለሱትን ወደ ጥያቄ 1205 እንዲያልፉ በማድረግ ከዚህ ቀደም ስልጠና/መደ በኛ ትምህርት መማር አለመማራቸውን ይጠይቃሉ። በዚህ ዓምድ ልጁ/ልጅቷ ከተሰጡት አማራጭ መል ሶች ከአንድ ዓይነት በላይ በሆነ የትምህርት ዘርፍ ተሳትፎ ካላቸው ለኮድ በተሰጠው ቅደም ተከተል መ ሠረት ቀድሞ የተቀመጠውን በዋነኝነት የሚማረውን የትምህርት ዓይነት ይወስዳል። ለምሳሌ በመደበኛ ት/ቤት የመደበኛ ቀለም ትምህርትና የሙያ ትምህርት ለሚማሩ የሚሞላላቸው ኮድ 1 ይሆናል።

1202.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) አሁን የምትከታተለው/ይው የክፍል ወይም የትምህርት ደረጃ ስንተኛ ነው?**

ከላይ በጥያቄ 1201 ሲጠየቁ አዎን ብለው ኮድ 1 ለተከበበላቸው ይህ ጥያቄ ይቀርብላቸዋል። ዕድሜአቸ ው ከ10-17 ዓመት የሆኑ ልጆች በአሁኑ ወቅት ወይም ሴምስተር እየተከታተሉ ያሉትን የትምህርት ደረ ጃ ይጠየቃሉ። ከዚህ ጥያቄ በፊት በቅፅ 1 ዓምድ 20 የጨረሱትን ከፍተኛ ክፍል መጠየቃቸው ይታወሳል ። በዚህኛው ጥያቄ የጨረሱት ሳይሆን በአሁኑ ሴምስተር ስለሚከታተሉት የትምህርት ደረጃ ብቻ የሚጠ ይቅበት ነው። ስለዚህ ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለሚከታተሉ ያሉበት የትምህርት/የክፍል ደረጃ እንደ ኮ ድ ተወስዶ ይሞላል። ለምሳሌ 3ኛ ክፍል እየተከታተሉ ላሉ ኮድ 03 ይሞላል። ከ12ኛ ክፍል በላይ እየ ተከታተሉ ላሉ ደግሞ ኮድ 13 በካርድ ኮለሙ ይሞላላቸዋል።

1203. **(የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፈው ሳምንት ትምህርት ተከታትለህ/ሽ ነበር?**

ጥናቱ በሚካሄድበት ሳምንት ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት የሆናቸው የቤተሰቡ አባላት ትምህርት እየተ ማሩ መሆን አለመሆናቸው ተጠይቆ ሙሉ ጊዜአቸውን/ሰዓት በመደበኛ ትምህርት ለሚያሳልፉ ኮድ 1፣ በመደበኛ ትምህርት ግማሽ ቀን ብቻ ለሚማሩ ኮድ 2፣ በመደበኛ ትምህርት የማታ ተማሪዎች ኮድ 3 ይ ከበብላቸዋል። ከኮድ 1-3 ለተከበበላቸው ወደ ጥያቄ 1208 ይታለፋል። እንዲሁም በጥናቱ ሳምንት መደ በኛ ባልሆነ ትምህርት ለተማሩ ኮድ 4 ተሞልቶላቸው ወደ ጥያቄ 1205 ያልፋሉ። ምንም ለማይማሩ ኮ

ድ 5 ተከቦ የሚቀጥለውን ጥያቄ ይጠየቃሉ። በዚሁ ዓመት ወይም ሴሚስቴር ለመማር ተመዝግበው ነገ ር ግን ትምህርታቸውን ያልጀመሩ ወይም ያቋረጡ ወይም በጥናቱ ሳምንት ትምህርት ቤት ያልሄዱ የቤ ተሰቡ አባላት በመማር ላይ እንዳሉ ተደርጎ እንዳይመዘገብ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

1204. **(የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፈው ሳምንት ስልጠና ተከታተለህ/ሽ ነበር?**

ይህ ጥያቄ የሚያተኩረው ልጆች ከትምህርት በተጨማሪ ወይም ከትምህርት ውጭ የሙያ ስልጠና እየተ ከታተሉ መሆኑን ለማወቅ ነው። ስልጠና ሲባል በአንድ ድርጅት ወይም መ/ቤት የተወሰነ ጊዜ ተመድቦ ለትና ፕሮግራም ተንድፎለት ከቀለም ትምህርት ውጭ የሆነ የሙያ ትምህርት/ስልጠና ሲሰጥ ነው። ለም ሳሌ ሙዚቃ መሣሪያ፣ አናጢነት፣ ግንበኝነት፣ መካኒክነት ...ወዘተ። ስለሆነም ይህ ጥያቄ ሲጠየቅ ከታች የተመለከቱትን ነጥቦች መረዳት ያስፈልጋል።

- የምስክር ወረቀት እንደሚያስገኙ ታቅደው በመንግስታዊም ሆነ በግል ድርጅቶች የሚሰጡ ማናቸው ም የአጭርም ሆነ የረጅም ጊዜ የሙያ ስልጠናዎች እንደሙያ ስልጠና ይቆጠራሉ።

- አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሙያ ትምህርትን ብቻ የሚማሩ (ለምሳሌ በማታው ክፈለ ጊዜ) በሙያ እንደሚሰለጥኑ ይቆጠራል።

- ነገር ግን እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ የቀለም ትምህርት እየተማሩ ያሉ በሙያ እንደሚሰለጥኑ አይቆጠ ርም፣ እንዲሁም ከ12ኛ ክፍል በላይ (በዩኒቨርስቲ /ኮሌጅ/ ተቋም... ወዘተ) በቀንም ሆነ በማታው ክ ፈለ ጊዜ Professional ትምህርት የሚማሩ በሙያ ትምህርት እንደሰለጠኑ አይቆጠርም።

1205.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) ከዚህ ቀደም መደበኛ ትምህርት ተምረህ/ሽ ነበር ወይም ስልጠ ና ተከታትለህ/ሽ ነበር?**

ይህ ጥያቄ የሚቀርበው በጥያቄ 1201 መደበኛ ያልሆነ ትምህርት እየተማርኩ ነው ብለው ኮድ 3 የተከ በበላቸውንና አልማርም ብለው ኮድ 4 የተከበበላቸውን የሚመለከት ነው። ከጥናቱ በፊት ባሉት በማናቸ ውም ዓመታት ውስጥ ትምህርት ተምረው ወይም ስልጠና ወስደው ያውቁ እንደሆነና እንዳልሆነ ተጠይ ቀው ከተሰጡት አማራጭ መልሶች አንዱን ብቻ እንዲመልሱ ይደረጋል።

1= <u>በዚህ ዓመት ጀምሬ አቋረጫለሁ፡</u>

በያዝነው የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርት ጀምረው ነገር ግን ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያ ቶች በማቋረጣቸው በመማር ላይ ለማይገኙ ልጆች ይህ ኮድ ይሰጣቸዋል። በተለያየ ምክንያት ባለፈው ሳምንት ለጥቂት ቀናት ከትምህርት ገበታ ቀርተው ነገር ግን ወደ ትምህርታቸው መመለስ የሚፈል ጉና ት/ቤቱም እንዲመለሱ የሚፈቅድላቸው ልጆች ጀምረው እንዳቋረጡ አይቆጠርም።

2= <u>ከዚህ ዓመት በፊት ተምሬ ነበር፡</u>

ከጥናቱ ዓመት በፊት በነበረ በማንኛውም ዓመት መደበኛ ትምህርት ለተማሩ የሚሰጥ ኮድ ነው። ተ ምረው ያቋረጡ ሲባል ባለፉት ዓመታት ውስጥ ቢያንስ አንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃን አጠናቀው ያ ቋረጡ ማለት ነው።

3= <u>ምንም ተምሬ አላውቅም፡</u>

በጥናቱ ዓመትም ሆነ ከጥናቱ ዓመት በፊት በመደበኛ ት/ቤቶች ምንም ተምረው ለማያውቁ ልጆች የሚሰጥ ነው።

4= <u>ለጊዜው ባለፈው ሳምንት የቀሩ፡</u>

በያዝነው የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርት እየተማሩ የነበሩ ነገር ግን ባለፈው ሳምንት በተለያየ ምክንያት ለጥቂተ ቀናት ከትምህርት ቤት ቢቀሩም ተመልሰው እንደሚገቡ እርግጠኛ የሆኑ ይህ ኮ ድ ይከበብላቸዋል።

1206.

<u>**(የልጁ/ጅቷ ስም) መደበኛ ትምህርት ያልተከታተልክበት/ሽበት ወይም ትምህርት ያቋረጥክበት/ሽበት ወይም ስልጠና ያልወሰድክበት/ሽበት ምክንያት ምንድነው?**</u>

ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1205 ከኮድ 1-3 የመለሱትን ማለትም ትምህርት ያቋረጡትን፣ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ብቻ የሚማሩትንና ምንም የማይማሩትን የሚመለከት ነው፡፡ ከተዘረዘሩት አማራጭ መልሶች ውስጥ ተቀ ራራቢ ከሆኑት ዋነኛ የሆነውን ምክንያት በመውሰድ ኮዱ ይከበባል፡፡ ለምሳሌ ልጁ በጥናቱ ሳምንት በህ መም/በአካል ጉዳት ትምህርት ያልተከታተለ ከሆነ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች በህመም/ በአካል ጉዳት የሚለው ኮድ 06 ይከበባል፡፡ እንዲሁም በቤተሰብ ድርጅት በክፍያም ሆነ ያለክፍያ ለቤተሰቡ ገቢ ለማ ስገኘት ወይም ለቤተሰቡ ገቢ ለማስገኘት ብለው በግል ወይም በቅጥር በመሥራታቸው ምክንያት የማይ ማሩ/ትምህርት ያቋረጡ ኮድ 09 ይሰጣቸዋል፡፡ ከአንድ በላይ በሆኑ ምክንያቶች ትምህርቱን ያልተከታተ ለ/ች ከሆነ መልስ ሰጪው/ዋ ዋነኛውን ምክንያት ብቻ እንዲመርጥ/እንድትመርጥ ይደረጋል፡፡ አማራጭ መልሶቹም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ ይህን ጥያቄ የተጠየቀት በሙሉ ጥያቂ 1207 ስለማይመለከታቸ ው ወደ ጥያቄ 1208 ያልፋሉ፡፡

01 = በአቅራቢያዬ ት/ቤት ወይም የማሰልጠኛ ማዕከል ባለመኖሩ
02 = ቤተሰቤ ለት/ቤት ወይም ለስልጠና የምከፍለው ገንዘብ ስለሌለው
03 = በትምህርት ደካማ ስለሆንኩና ትምህርት ለመማር ወይም ስልጠና ለመውሰድ ፍላጎት ስለሌኝ
04 = በትምህርት ስለወደቅሁ
05 = አስተማሪዎችን ስለምፈራ
06 = በህመም/በአካል ጉዳት
07 = በቤት ውስጥ ሥራ ቤተሰቦቼን ስለምረዳ
08 = እራሴን ለመርዳት ስል ስለምሠራ
09 = ለቤተሰቤ ገቢ ለማስገኘት ስል ስለምሠራ
10 = ቤተሰቦቼ ትምህርት እንድማር ወይም ስልጠና እንድከታተል ስለማይፈቅዱ
11 = በጋብቻ ምክንያት
12 = በመናፈቅል (በጦርነት፣ በድርቅ)
13 = በቤተሰብ ዝውውር
14 = በቤተሰብ መበተን (በፍቺ፣ በሞት)
15 = ሌላ (ይገለፅ) __________________

1207 **<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፈው ሳምንት ለምን አልተማርክም/ሽም?</u>**

ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1205 ኮድ 4 የመለሱትን የሚመለከት ነው፡፡ እነዚህ ልጆች በዚያ ሴሚስተር ተመዝግበው ትምህርት በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን በጥናቱ ሳምንት ብቻ በተለያዩ አጋ ጣሚዎች ከትምህርት ቤት የቀሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ ትምህርት እንደአቋረጡ ተደርጎ እንዳይወሰዱ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡ ባለፈው ሳምንት ከትምህርት የቀሩበት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች ከታች ከኮድ 1-6 የተዘረዘረ ስለሆነ ከነዚህ አማራጭ መልሶች መካከል ተስማሚው ኮድ ይከበባል፡፡

| | |
|---|---|
| 1 = በቤት ውስጥ ሥራ ቤተሰቦቼን ስለምረዳ | 4 = በህመም/በአካል ጉዳት |
| 2 = እራሴን ለመርዳት ስል ስለምሠራ | 5 =ትምህርት ቤት ስለተዘጋ (በበዓል፣ በክረምት…ወዘተ) |
| 3 = ለቤተሰቤ ገቢ ለማስገኘት ስል ስለምሠራ | 6 = ሌላ (ይገለፅ) __________________ |

1208. **<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፉት 7 ቀናት ያከናወንካቸው/ሻቸው ሥራዎች ምን ምን ናቸው?</u>**

ይህ ጥያቄ ልጆች ባለፈው ሳምንት ሙሉ ወይም ከፊል ጊዜአቸውን እንዴት እንዳሳለፉ የሚመለከት ነው ፡፡ ባለፈው ሳምንት ልጁ/ጅቷ በምርታማ ሥራ ተሰማርቶ/ታ ከሆነ ኮድ 1 ምርታማ ሥራና በቤት ውስ ጥ ሥራ ከተሰማራ/ች ኮድ 2 እና ምርታማ ባልሆነ የቤት ውስጥ ሥራ ላይ ከተሰማራ/ች ኮድ 3 ይወሰዳ ል፡፡ በምርታማ ባልሆነ ሥራ <u>ለምሳሌ</u>፡- በሴተኛ አዳሪነት፣ ልመና …ወዘተ ከተሰማሩ ኮድ 4 ይሰጣል፤ እ ንዲሁም ምንም አልሠራሁም ካሉ ኮድ 5 ይከበባል፡፡ ይሁን እንጂ ለዚህ ጥያቄ ኮዱ 4 እና ኮድ 5 የተከ በበላቸውን ወደ ጥያቄ 1227 በማሳለፍ ከዚህ ቀደም ሌላ ሥራ ሲሰሩ የአካል መጎዳት/ህመም አጋጥሟቸ ው እንደሆነ ይጠየቃሉ፡፡ <u>ሥራ እያላቸው ባለፈው ሳምንት በተለያየ ምክንያት ያልሠሩ ካሉ በጥናቱ ሳም ንት ምርታማ ሥራ እንደሠሩ ተቆጥሮ ኮድ 1 ይከበብላቸዋል፡፡</u> በተጨማሪም ምርታማ ያልሆነ ሥራ ለሁ ለት የተከፈለ በመሆኑ በጥንቃቄ ማጤን ይገባል፡፡

ቀደም ሲል ስለ ምርታማ ስራ መግለጫ በቅጽ 1 ዓምድ 24 ላይ በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ሆኖም ግን በድጋሚ ለግንዛቤ እንዲረዳ በማሰብ በዚህ ክፍል ባጭሩ ቀርቧል፡፡ ምርታማ ሥራ ሲባል የሥራ ውጤት የሆነው ን ሸቀጣ ሸቀጥ ወይም አገልግሎት በከፊል ወይም በጠቅላላ በገንዘብም ሆነ በዓይነት ወይም በዕቃ በመለ ወጥ ገቢ ለማግኘት ለገበያ ለማቅረብ ሲቻል ነው፡፡ በራስ ወይም በቤተሰብ ይዞታ በመንግስታዊ በሕዝባ

ዊ ወይም በግለሰብ ቤት ወይም ድርጅት በቀን፣ በሳምንት፣ በወር፣ ወይም በሰሩት መጠን ክፍያ ወይም ገቢ ለማግኘት ሥራ ከሰሩ እንደምርታማ ሥራ ይቆጠራል፡፡ በሌላ አገላለፅ ምርታማ ሥራ ለግል ወይም ለመንግስት ተቀጥሮ አገልግሎት መስጠትን ወይም የግል ስራ መስራትን፣ መነገድን፣ የግብርና ሥራን፣ ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎችን ማምረትን፣ በቤተሰብ ድርጅት/እርሻ ውስጥ ያለክፍያ መስራትንና በመለማመድ ላይ ያሉትን ያጠቃልላል፡፡ ነገር ግን ለቤተሰብ ያለክፍያ የሚሠራ የቤት ውስጥ ሥራ፣ በበጎ ፈቃደኝነት ማገዝ ወይም በዘመቻ የሚሠራ ሥራ <u>ለምሳሌ ነፃ</u> አገልግሎት የሆነ የደን ተከላ እንደምርታማ ሥራ አይቆጠርም፡፡ ያለክፍያ የቤት ውስጥ ሥራ ምን ማለት እንደሆነ በቅጽ 2 ክፍል 8 ተገልጿል፡፡ በምርታማ ሥራ ውስጥ የሚጠቃለሉ የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባራትን በተመለከተ በቅፅ 1 ዓምድ 24 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡

1209.

<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) በትላንትናው ዕለት በሰራሃቸው/ሻቸው በሁሉም ሥራዎች ለስንት ሰዓት ሰርተሃል/ሻል?</u>

በዚህ ዓምድ ባለፈው ቀን ልጁ/ልጅቷ የሠራውን/ችውን ጠቅላላ የሥራ ሰዓት መጠን ይሞላል፡፡ ይህ ጥያቄ የሚመለከተው ቀደም ብሎ ባለው ቀን ወይም በትላንትናው ቀን የሠሩት የሥራ ሰዓት ሲሆን ይህም ምርታማ ተግባር በመሥራት ያሳለፉትንና የቤት ውስጥ ሥራ የሠሩበትን የሥራ ሰዓት አንድ ላይ በመደመር ነው፡፡ ልጆች ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሠሩት የስራ ሰዓት መጠን ካለማስታወስ የተነሳ ይቸገሩ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን በተቻለ መጠን በእርጋታ በመጠየቅና በአካባቢው ከተከናወኑ ድርጊቶች ጋር በማገናዘብ በትላንትናው ዕለት ከጠዋት እስከ ምሽት የሠሩትን የስራ ሰዓት መጠን ለማግኘት ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ለአንድ ልጅ የተሞላ መረጃ ለሌላኛው በማነፃፀሪያነት ሊጠቅም ይችላል፡፡ አንዳንድ ልጆች የተለያየ ሥራ የሚሠሩ ከሆነና እንዲሁም በፈረቃ ለሚሰሩ በሁሉም ሥራዎች የዋለውን የሥራ ሰዓት ብዛት አንድ በአንድ አጣርቶ በመጠየቅ ጠቅላላው የስራ ሰዓት መጠን ይሞላል፡፡

1210. <u>(የማጣሪያ ጥያቄ)</u>

ይህ ጥያቄ ልጆች ባለፈው ሳምንት ትምህርት/ስልጠና ተከታትለው እንደሆነ የማጣሪያ ጥያቄ በመሆኑ መረጃ ሰብሳቢው መልስ ሰጪውን ሳይጠይቅ በራሱ የሚያጣራበት ነው፡፡ ይህ ጥያቄ ለመልስ ሰጪው ቀርቦ የሚጠየቅ ሳይሆን መረጃ ሰብሳቢው ጥያቄ 1201፣ 1203 እና 1204ን በጥንቃቄ በመመልከት የሚያጣራው ነው፡፡ ልጁ/ልጅቷ ባለፈው ሳምንት ትምህርት ወይም ስልጠና እየተከታተሉ እንደሆነ ማለትም ለጥያቄ 1203 ከኮድ 1-4 ወይም ለጥያቄ 1204 ከኮድ 1-3 መከበቡን በማረጋገጥ ለዚህ ጥያቄ ኮድ 1 ይከበብና የሚቀጥለው ጥያቄ ይጠየቃል፡፡ እንዲሁም ልጁ/ልጅቷ ትምህርት/ሥልጠና ካልደወሰዱ ማለትም ለጥያቄ 1201 ኮድ 4፣ ለጥያቄ 1203 ኮድ 5 ወይም ለጥያቄ 1204 ኮድ 4 የተሰጣቸው መሆኑን በማረጋገጥ ለዚህ ጥያቄ ኮድ 2 በመክበብ ወደ ጥያቄ 1212 የታለፋል፡፡

1211. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ሥራህ/ሽ ትምህርትህን/ሽን በደንብ እንዳትከታተል/ይ አድርጓል?</u>

ይህ ጥያቄ ሥራ እየሠሩ ከፊል ጊዜያቸውን በትምህርት ላይ የሚያሳልፉ ልጆችን ይመለከታል፡፡ በዚህ ዓምድ ልጆች በሥራ ላይ በመሳተፋቸው ስራቸው ትምህርታቸውን አደናቅፎ ከሆነ ኮድ 1 ካልሆነ ደግሞ ኮድ 2 ይከበባል፡፡ አንድ ልጅ የሚሠራው ሥራ ትምህርቱን አደናቅፎታል የሚባለው በሥራው ምክንያት ከትምህርት ቤት ደጋግሞ ወይም አልፎ አልፎ የሚቀር ከሆነ፣ የሚያረፍድ ከሆነ፣ ለጥናት ጊዜ ያጣ... ወዘተ ከሆነ ነው፡፡

1212. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ሥራውን የምትሠራው/ሪው ለማነው?</u>

ለወላጅ/ለአሳዳጊ ወይም ለቤተሰብ ያለክፍያ የሚያገለግሉ ልጆች ኮድ 1 ተከቦላቸው ወደ ጥያቄ 1225 ይታለፋል፡፡ ከቤተሰብ ውጭ ለሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት በክፍያም ሆነ ያለክፍያ ለሚሰሩ ኮድ 2 ይከበብላቸዋል፡፡ በቤት ውስጥ ተቀጣሪ ሠራተኛ ከሆኑ <u>ለምሳሌ፡-</u> በቤት ሠራተኛ፣ ለዘበኛ፣ ለእረኛ ...ወዘተ ኮድ 3 ተከቦላቸው ወደ ጥያቄ 1214 ይታለፋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ በቤተሰቡ ድርጅት (<u>ለምሳሌ፡-</u> በቤተሰቡ ሱቅ፣ እርሻ ወይም ተመሳሳይነት ባለው ድርጅት ውስጥ) ተቀጥረው ለሚሠሩ ኮድ 4 ተከቦ ወደ ጥያቄ 1214 ያልፋሉ፡፡ ለግላቸው ለሚሠሩት ደግሞ ኮድ 5 ተከቦ ወደ ጥያቄ 1222 ይታለፋል፡፡

1213.

<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) አብዛኛውን ጊዜ ትርፍ ሰዓት ትሰራለህ/ሪያለሽ? ከሠራህ/ሽ በክፍያ ነው?</u>

ይህ ጥያቄ ከቤተሰብ ውጭ ለሌላ ግለሰብ/ድርጅት በክፍያ ወይም ያለክፍያ የሚሠሩትን ይመለከታል:: ክፍያ ሲባል በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን በግለሰብ ቤት የቤት ሥራ ለመ ሥራት ለተቀጠሩ የሚሰጥ ምግብ፣ ምግብና መኝታ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎት እንደ ክፍያ አ ይቆጠሩም:: አንድ ሰው ትርፍ ሰዓት ሠራ የሚባለው ሥራው ከሚጠይቀው የተለመደ የሥራ ሰዓት ው ጭ ሲሰራ ነው:: ይህም በመንግስትም ሆነ በግለሰብ ወይም ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩትን የሚ መለከት ይሆናል:: <u>ለምሳሌ:-</u> የመንግስት ሠራተኛ በቀን ስምንት ሰዓት መስራት ካለበት ከዚህ ውጭ አብ ዛኛውን ጊዜ በክፍያም ሆነ ያለክፍያ ቢሰራ እንደትርፍ ሰዓት ይቆጠራል:: በተመሳሳይ ለሌላ ግለሰብ ወ ይም መ/ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው ለሚሠሩ እንደሥራው ፀባይ በቅጥር ጊዜ ከተደረገው ስምምነት ወይም ከተለመደው የሥራ ሰዓት ውጪ አብዛኛውን ጊዜ መስራት አለመስራታቸውን ከመልስ ሰጪው ጋር በመነጋገር መረጃ ሰብሳቢው መገመት ይችላል:: በክፍያ ትርፍ ሰዓት ለሚሠሩ ኮድ 1 ያለክ ፍያ ትርፍ ሰዓት የሚሰሩ ኮድ 2 እንዲሁም ትርፍ ሰዓት ለማይሰሩት ደግሞ ኮድ 3 ይከበብላቸዋል::

1214. <u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ከአሰሪህ/ሽ ጋር ያለህ/ሽ ግንኙነት እንዴት ነው?</u>

ልጆች ተቀጥረው በሚሠሩበት ወቅት ከአሰሪያቸው ጋር ጥሩም ሆነ መጥፎ ግንኙነት ሊመሠርቱ ይችላሉ: : ይህንን ሁኔታ ለማወቅ እንዲቻል አንዳንዴ ልጆች ከመፍራት የተነሳ ትክክለኛው ሁኔታ እንዳይደብቁ አግባብቶ ረጋ አድርጎ በመጠየቅ መረጃ ለማግኘት መረጃ ሰብሳቢው ጥረት ማድረግ ይኖርበታል:: ስለዚህ ከላይ ለቀረበው ጥያቄ ጥሩ ነው ወይም አስቤበት አላውቅም ወይም ግዴለኝም ብለው ኮድ 1 ወይም ኮ ድ 3 ለተከበበላቸው ወደ ጥያቄ 1216 ይታለፋል፣ መጥፎ ነው ካሉ ደግሞ ኮድ 2 ተከቦ የግንኙነቱ መ ጥፎነት ምክንያቱ ምን እንደሆነ ለማወቅ የሚቀጥለውን ጥያቄ ይጠየቃሉ::

1215.

<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ከአሰሪህ/ሽ ጋር ያለህ/ሽ ግንኙነት መጥፎ ከሆነ ምክንያቶቹ ም ንድን ናቸው?</u>

ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1214 ከአሠሪያቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት መጥፎ ነው ብለው ለመለሱ ግንኙ ነቱ መጥፎ የሆነበትን ምክንያት ለማወቅ የሚያስችል ነው:: አማራጭ መልሶችም ከፊደል A-G ተዘርዝረዋል:: እዚህ ላይ መታወስ የሚገባው ሴት ልጆች በሴትነታቸው በአሠሪያቸው የመደፈር ሁኔ ታ በአብዛኛው ሊያጋጥም እንደሚችል ይገመታል:: ስለዚህ አስገድደው ለመድፈር ስለሞከሩ ወይም ስለደ ፈሩኝ ካሉ መልሱን ሌላ በሚለው ላይ መመዝገብ ይኖርበታል:: ለመልስ ሰጭው ከA-G የተሰጡትን አማራጭ መልሶች በማንበብ ለእያንዳንዱ ጥያቄ "አዎን" ለሚሉ ኮድ 1:- "የለም" ብለው ለሚመልሱ ኮድ 2 ይከበባል::

A. ብዙ ሥራ እንድሠራ ስለሚፈለግ - ከባድ ሥራ፣ ያለእረፍት የሚሠራ
B. ለረጅም ሰዓት እንድሠራ ስለሚፈለግ - ሥራ ከባድ ባይሆንም በሥራው ላይ ለረጅም ሰዓት እንዲ ሠሩ ሲፈለግ
C. ክፍያው ትንሽ ስለሆነ
D. በወቅቱ ስለማይከፈለኝ
E. ስለምደበደብ
F. በቃላት ስለሚተነኩሱኝ/ስለሚያጥላሉኝ
G. ሌላ (ይገለፅ) ____________________

1216.

<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) በአሁኑ ወቅት በክፍያ የምትሰራ/ሪ ከሆነ በስንት ጊዜ ነው ክፍ ያ የሚሰጥህ/ሽ?</u>

ይህ ጥያቄ ከቤተሰብ ውጪ ለሌላ ግለሰብ/ድርጅት ተቀጥረው የሚሰሩትን የሚመለከት ይሆናል:: የአከፋ ፈል ሁኔታን ስንመለከት እንደሥራው ፀባይና እንደአካባቢው ሁኔታ ይለያያል:: <u>ለምሳሌ:-</u> የኮንትራት ሥራ በስራው መጠን ሲከፈል አንዳንድ ሥራዎች ደግሞ በሰዓት ወይም በቀን ወይም በወር ሂሳብ የሚከ ፈሉም አሉ:: በገጠር አካባቢ ለእረኞች፣ ተቀጥረው ለሚያርሱ ገበሬዎች እንዲሁም ለቤት ሠራተኞች፣ ል ጅ አሳዳጊዎች አልፎ አልፎ ደሞዛቸው በዓመት ይከፈላቸዋል:: ከዚህ በመነሳት የክፍያው አይነት ከኮድ 1-8 የተዘረዘረ ሲሆን ከተዘረዘሩት አንዱ እንደሁኔታው ይወሰዳል:: እንዲሁም አይከፈለንም ለሚሉ ኮ ድ 9 ተከቦ ወደ ጥያቄ 1225 እንዲያልፉ ይደረጋል::

| | |
|---|---|
| 1= በስራው መጠን | 6 = በየወሩ |
| 2 = በየሰዓቱ | 7 = በየዓመቱ |
| 3 = በየቀኑ | 8 = ሌላ (ይገለፅ) __________ |

4 = በየሣምንቱ 9 = አይከፈለኝም
5 = በየ 15 ቀን

1217.

(የልጁ/ጅቷ ስም) በአካባቢው ካለው የአከፋፈል ሁኔታ አንፃር የተመጣጠነ ክፍያ ታገኛለህ/ሽ?

ይህ ዓምድ ዕድሜአቸው ከ10-17 ዓመት የሆናቸውን ልጆችና ተቀጥረው የሚሠሩትን የሚመለከት ሲሆን የሚያገኙት ክፍያ በልጆቹ አመለካከት ከአካባቢው የአከፋፈል ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር አዎን ተመጣጣኝ ነው ለሚሉ ኮድ 1 ሲከበብ የለም ተመጣጣኝ አይደለም ለሚሉ ደግሞ ኮድ 2 ይከበብላቸዋል፡፡ በዚህ ጥያቄ ለማወቅ የተፈለገው ልጁ የሚሰራውና የሚያገኘው ክፍያ ከአካባቢው ካለው ክፍያ አንፃር ሲታይ በቂ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ነው፡፡

1218.

የልጁ/ጅቷ ስም) በቅርቡ (የመጨረሻው) በአሰሪህ/ሽ በጥሬ ገንዘብ የተከፈለህ/ሽ ክፍያ ምን ያህል ብር ነው?

በዚህ ጥያቄ ልጁ/ጅቷ ለሚሠራው/ለምትሠራው ሥራ በቅርቡ በገንዘብ መልክ የተከፈለው/ላት ክፍያ መጠን በተሰጠው ካርድ ኮለም ላይ ይሞላል፡፡ በቅርቡ የተከፈለው ክፍያ ሲባል ከላይ በጥያቄ 1216 በምን ያህል ጊዜ እንደሚከፈለው/ላት በተገለፀው መሠረት የመጨረሻውን ጊዜ ክፍያ ማለት ነው፡፡ በገንዘብ የተገኘ ክፍያን ለመሙላት የተዘጋጀው ቦታ ባለ 4 ካርድ ኮለም ስለሆነ መልሱ በሚሞላበት ጊዜ ሳንቲሞች ካሉ ወደ ብር ተጠጋግተው አሞላሉም ከቀኝ ወደ ግራ መሆን አለበት፡፡ በገንዘብ ክፍያ ለሚያገኙ ይሞላል፡፡ ነገር ግን ጥናቱ እስከተካሄደበት ቀን ድረስ በተለያየ ምክንያት ክፍያ ያላገኙ ከሆነ ኮድ «9998» ይሞላል፡፡ ከ9997 ብር እና በላይ ለሚያገኙ ኮድ «9997» ይሞላላቸዋል፡፡ በጥናቱ ወቅት ክፍያ ያላገኙ ከሆነ ኮድ «0000» ይሞላል፡፡

1219.

(የልጁ/ጅቷ ስም) በቅርቡ (የመጨረሻው) በዓይነት ወይም በዕቃ የተከፈለህ/ሽ መጠን በብር ተገምቶ ምን ያህል ነው?

ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1218 ከተገለፀው ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ልዩነቱ አከፋፈሉ በዓይነት ወይም በዕቃ መሆኑ ነው፡፡ የምግብና የመኝታ አገልግሎት እንደ ዓይነት ክፍያ የሚቆጠረው በቅጥር ስምምነቱ ውስጥ የተገለፀ/የተነገረ ከሆነ ነው፡፡ ስለዚህ በዓይነትና በዕቃ የተሰጠን ክፍያ መረጃ ሰብሳቢው በአካባቢው የገበያ ዋጋ መሠረት ግምቱን በመውሰድ የሚሞላ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፡- ለልጁ የተሰጠው ልብስ፣ ጫማ ሊሆን ይችላል፡፡ የልጅ ልብስና ጫማው በአካባቢው ገበያ እንደ ጨርቁ ሁኔታና የጫማው ዓይነት ታይቶ በማነፃፀር ዋጋውን መገመት ይቻላል፡፡ ልጁ/ልጅቷ ምንም የዓይነት ክፍያ ካልተሰጠው/ካልተሰጣት ኮድ «0000» ይሞላል፡፡

1220. በገንዘብና በዓይነት የተከፈለ ክፍያ ድምር

ከላይ በጥያቄ 1218 በገንዘብ የተገኘን ክፍያ እና በጥያቄ 1219 በዓይነት ወይም በዕቃ የተገኘን ክፍያ መረጃ ሰብሳቢው በመደመር በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ላይ ይሞላል፡፡ እንጂ መልስ ሰጪው ጠይቆ የሚሞላ አይደለም፡፡

1221.

(የልጁ/ጅቷ ስም) ከተቀበልከው/ሽው ገንዘብ ከፊሉን ወይም ሙሉውን ለቤተሰብ ወይም ለአሳዳጊህ/ሽ ወይም ለሌላ ለምትኖርባቸው ዘመዶችህ/ሽ ትሰጣለህ/ጫለሽ?

ይህ ጥያቄ ልጆቹ ሠርተው የሚያገኙትን ገንዘብ የት እንደሚያውሉትና ለምን እንደሚጠቀሙበት ለማወቅ የሚያስችል ጥያቄ ነው፡፡ አንዳንድ ቤተሰብ ልጆቻቸውን በቅጥር መልክ ለሌላ ግለሰብ በመስጠት ክፍያውን እራሳቸው የሚቀበሉ ይኖራሉ፡፡ አንዳንድ ልጆች ደግሞ ከሚያገኙት ክፍያ ከፊሉን ብቻ ለቤተሰብ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ልጁ/ልጅቷ ከቀረቡት አማራጭ መልሶች ውስጥ ሁሉንም ክፍያ በአሠሪዬ በኩል ለቤተሰብ እሰጣለሁ የሚል ከሆነ ኮድ 1 ይከበባል፣ ሁሉንም እራሴ እሰጣቸዋለሁ ካለ ኮድ 2 ይከበባል፡፡ ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ለተከበበላቸው ወደ ጥያቄ 1225 እንዲያልፉ ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል ከፊሉን ብቻ

በአሠሪዬ በኩል ወይም ከፊሉን እራሴ እሰጣለሁ ካለ ደግሞ ኮድ 3 ወይም ኮድ 4 ይከበባል። የለም ም ንም አልሰጥም ለሚሉ ኮድ 5 ይከበባል። እንዲሁም እስካሁን አልተከፈለኝም ካሉ ኮድ 6 በመክበብ ወደ ጥያቄ 1225 ይታለፋል። ከዚህ የተለየ መልስ የሚቀርብ ከሆነ ደግሞ ኮድ 7 ተከቦ የተሰጠው መልስ በባዶ ቦታው ላይ ይፃፋል።

1222. **(የልጁ/ጅቷ ስም) ሠርተህ/ሽ ካገኘኸው/ሽው ገንዘብ ከፊሉን ትቆጥባለህ/ቢያለሽ?**

በጥያቄ 1221 በክፍያ የሚያገኙትን ገንዘብ ከፊሉን ብቻ ለቤተሰብ የሚሰጡ ወይም ምንም ለቤተሰብ የ ማይሰጡ ልጆች ካገኙት ገንዘብ ውስጥ ከፊሉን ይቆጥቡ እንደሆነ ይጠየቃሉ። መልሱ በቋሚነት እቆጥባለ ሁ የሚል ከሆነ ኮድ 1 ወይም አልፎ አልፎ ብቻ የሚቆጥብ ከሆነ ኮድ 2 ይከበባል። የለም አልቆጥብም ካለ ደግሞ ኮድ 3 ተከቦ ወደ ጥያቄ 1225 ይታለፋል። ልጆች ስለሆኑ አይቆጥቡም ተብሎ መገመት የለ በትም። አንዳንድ ልጆች ለምሳሌ:- የሊስትሮ ስራ የሚሰሩ የተሻለ ሥራ ለመፍጠር ሲሞክሩ ሌሎቹ ደግ ሞ የሊስትሮ ስራ እየሠሩ ጎን ለጎን ትምህርት የሚማሩ አሉ ለዚህም እንዲረዳቸው መጠነኛ ቁጠባን ያደ ርጋሉ ይህንን መሰል ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ የቀረበ ጥያቄ መሆኑ ታውቆ አጣርቶ መጠየቁ ተገበ ነው።

1223. **(የልጁ/ጅቷ ስም) አብዛኛውን ጊዜ የምትቆጥበው/ቢው እንዴት ነው?**

ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1222 ልጆቹ ከሚያገኙት ክፍያ ከፊሉን በቋሚነት ወይም አልፎ አልፎ እንደሚ ቆጥቡ ገልፀው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ለተከበበላቸው እንዴት እንደሚቆጥቡ ለማወቅ የሚቀርብ ነው። በ አሰሪ እጅ ለሚቆጥቡ ኮድ 1፣ በዘመድ እጅ ለሚቆጥቡ ኮድ 2፣ እንዲሁም በራሳቸው በኩል ለሚቆጥቡ ደግሞ ኮድ 3 ይከበብላቸዋል። ከዚህ የተለየ መልስ ከቀረበ ኮድ 4 ተከቦ በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ የተሰ ጠው መልስ ይፃፋል። አንዳንድ የቤት ሠራተኞች ደመወዛቸው እንዲጠራቀምላቸው በማሰብ በአሠሪያቸ ው እጅ ላልተወሰነ ጊዜያት ያስቀምጣሉ። ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ደመወዛቸው እንደተከፈላቸው በማሰብ ቁጣባው በአሰሪያቸው እጅ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል።

1224. **(የልጁ/ጅቷ ስም) እንድትቆጥብ/ቢ ያደረገህ/ሽ ምክንያት ምንድነው?**

ከላይ በጥያቄ 1222 አዎን እቆጥባለሁ ብለው ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 ለመለሱ ልጆች እንዲቆጥቡ ያበቃቸ ው ምክንያት ምን እንደሆነ ይጠይቃሉ። የራሴን ሥራ ለመጀመር ካሉ ኮድ 1 ይከበባል፣ ትምህርት ለመ ማር/ስልጠና ለማግኘት እንዲረዳኝ ነው የምቆጥበው ካሉ ደግሞ ኮድ 2 ይከበባል። እንዲሁም ቤተሰብ/ ዘመድ ለመርዳት ካሉ ደግሞ ኮድ 3 ይሰጣቸዋል። ለበዓላት ዝግጅት ወይም ለግሌ የሚያስፈልጉኝን ነገሮ ች ለማሟላት ካሉ በቅደም ተከተላቸው መሠረት ኮድ 4 እና ኮድ 5 ይከበብላቸዋል። ከዚህ የተለየ መል ስ ከተሰጠ ኮድ 6 ተከቦ መልሱ በተሰጠው ክፍት ቦታ ይገለፃል።

1225. **(የልጁ/ጅቷ ስም) አሁን በምትሠራው/ሪው ሥራ ደስተኛ ነህ/ሽ?**

አብዛኛውን ጊዜ ኑሮን ለማሸነፍ ሲባል ወይም በቤተሰብ ግፊት ልጆች ሳይፈልጉ ወይም ዕድሜአቸው ለ ሥራ ሳይደርስ ወደ ሥራ ዓለም ይገባሉ። በሥራ ላይ ያሉ ልጆች የተለያየ የሥራ ሁኔታና የተለያየ ፀባ ይ ያላቸው አሠሪዎች ያጋጥሟቸዋል። አንዳንድ ጊዜ የአዋቂ ጉልበት የሚጠይቅ ሥራ እንዲሠሩ የሚገ ደዱበት ሁኔታም ይኖራል። በዚህም ምክንያት በሥራቸው ያለመርካት/ያለመደሰት ሁኔታ ሊኖር ይችላል ። በዚህ ጥያቄ ልጆቹ በሚሠሩት ሥራ እርካታ ያገኙ ወይም አያገኙ እንደሆነ ተጠይቆ ደስተኛ ነኝ ካ ሉ ኮድ 1 ተመርጦ ወደ ጥያቄ 1227 ይታለፋል፣ የለም ደስተኛ አይደለሁም ካሉ ኮድ 2 ይከበብላቸዋል። 

1226.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) በአሁኑ ሥራህ/ሽ የማትደሰትበት/ችበት ዋነኛ ምክንያቱ ምንድነው?**

ይህ ጥያቄ ከላይ በጥያቄ 1225 «የለም» ብለው የመለሱትን የሚመለከት ነው። ልጆች ለማዘዝ ስለማይከ ብዱ፣ ጉልበታቸውን ስለማይቆጥቡ ብዙ አሠሪዎች ልጆችን ቀጥረው ማሠራትን ይመርጣሉ። ቀጣሪዎች ብዙ ትርፍ ለማግኘት ሲሉ የልጆችን ጉልበት አላግባብ ይጠቀማሉ። በዚህም ሳቢያ ስራው አድካሚ ስለ ሚሆን ልጆች የመሰልቸትና በሥራቸው ያለመርካት/ያለመደሰት ሁኔታ ይከሰታል። ይህ ጥያቄ እነዚህን ሁኔታዎች በዝርዝር ለማወቅና ለማገናዘብ የሚያስችል ነው። ስለሆነም በሥራቸው የማይረኩት በክፍያ ማነስ ምክንያት ከሆነ ኮድ 1፣ ሥራው አድካሚ ስለሆነ የሚሉ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ይከበባል። ልጆች የ ሚሠሩት ሥራ ከባድ/አድካሚ ባይሆንም ረጅም ሰዓት መሥራት የሚጠይቅ ወይም ብዙ ሥራ እንዲሠሩ የሚፈለግ ከሆነ ኮድ 3 ይከበብላቸዋል። እንዲሁም የአሠሪያቸው ፀባይ አስቸጋሪ ማለትም ነጭናጫ፣ ተ ሳዳቢ .... ወዘተ በመሆኑ ምክንያት ከሆነ ደግሞ ኮድ 4 ይከበብላቸዋል። በግሌ ሰርቼ የማገኘው ገንዘብ

አነስተኛ ስለሆነ ካሉ ኮድ 5 ይሰጣል፡፡ ከዚህ የተለየ መልስ ከተሰጠ ሌላ በሚለው ባዶ ቦታ ላይ ተጽፎ ኮድ 6 ይከበባል፡፡

1227.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) በማንኛውም ጊዜ ከስራህ/ሽ ጋር በተያያዘ ምክንያት ህመም ወይም ጉዳት አጋጥሞህ/ሽ ያውቃል?**

ይህ ጥያቄ ከዚህ ቀደም በሠሩት ሥራ ወይም አሁን በሚሠሩት ሥራ ምክንያት በአካል ላይ የደረሰ ጉዳትን/ህመምን ይመለከታል፡፡ የአካል ጉዳት ማለት ልጁ ሥራ በሚሠራበት ወቅት እግሩ ወይም እጁ ቢቆረጥ፣ ዓይኑ ቢታወር፣ ጆሮው ቢታመም ... ወዘተ ለምሳሌ ዕድሜው በሬ ጠምዶ ለማረስ ሳይደርስ በእርሻ ላይ በመሠማራቱ እግሩ ማረሻው ወግቶት ቢጎዳና ወይም እርፉን ተቆጣጥሮ ለመጨበጥ የሚያስችል አቅም በማጣቱ ወድቆ ቢሰበር ... ወዘተ የደረሰ የአካል ጉዳት ከሥራው ጋር እየተገናዘበ በመረጃ ድጋፍ የተፈለገው መረጃ መገኘት አለበት፡፡ በዚህ ክፍል ሕመም/ጉዳት የሚባለው ልጆቹ በሥራ ላይ ከሥራ ጋር በተያያዘ በሚሠሩት ሥራ ምክንያት ሳይታሰብ የደረሰባቸው የአካል ጉዳት የሕመም ስሜት ነው፡፡ የአካል ጉዳት/ሕመም ደረሰ የምንለው የጉዳቱ/የሕመሙ ስሜት ቢያንስ ለአንድ ቀን ከቆየባቸው ወይም ደግሞ በጉዳቱ ወይም በሕመሙ ምክንያት ቢያንስ ለአንድ ቀን ሥራ መሥራት ካልቻሉ ነው፡፡

በሌላ በኩል ህመም ማለት በሠሩት/በሚሠሩት ሥራ ምክንያት የደረሰባቸው ህመም ነው፡፡ ልጆች ህመሙ/ጉዳቱ ከደረሰባቸው ጊዜው የቆየ ከሆነ ጉዳት መድረሱን ሊዘነጉት ስለሚችሉና በጥናቱ ወቅት ጉዳቱ በዓይን ላይታይ ስለሚችል ጥያቄው ሲቀርብ በተቻለ መጠን መረጃ ሰብሳቢው በርጋታ በማብራራት ለማወቅ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ይህም ሲሆን እጅግ በጣም ጥቃቅንና ቀላል ጉዳቶች ጎልተው እንዳይመዘገቡ መጠንቀቅና እንዲህ ዓይነት ጉዳት እንደ ጉዳት ወይም ህመም ሊወሰዱ እንደማይገባቸው ግልጽ መሆን አለበት፡፡ ለዚህ ጥያቄ  አዎን ብለው ለመለሱ ልጆች ኮድ 1 ይከበባል፣ የለም ካሉ ኮድ 2 ተከቦ ወደ ጥያቄ 1232 ይታለፋል፡፡ እስከዛሬ ሰርቼ አላውቅም ካሉ ደግሞ ኮድ 3 ተከቦ ወደ ጥያቄ 1239 ይታለፋል፡፡

1228. **(የልጁ/ጅቷ ስም) የአካል ጉዳቱ ወይም የህመሙ ዓይነት ምንድነው?**

ከላይ በጥያቄ 1227 በሠሩት ሥራ ምክንያት ጉዳት ወይም ህመም ደርሶባቸው ለሚያውቅ ልጆች የደረሰባቸው ዋነኛ የአካል ጉዳት ወይም ህመም ዓይነት ተጠይቆ በዚህ ጥያቄ ከኮድ 01-20 ከተዘረዘረው ጋር ተቀራራቢ የሆነውን ኮድ ይከበባል፡፡ ከቀረቡት አማራጭ መልሶች የተለየ ከሆነ ኮድ 21 ወይም 22 ተመርጦ የህመሙ ወይም የጉዳቱ ዓይነት ይመዘገባል፡፡ አማራጭ መልሶቹም ከታች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

1 = አጠቃላይ በሽታ (ለምሳሌ እንደ ትኩሳት፣ ብርድ ... ወዘተ)
2 = የዓይን ህመም
3 = የጆሮ ህመም
4 = የቆዳ ህመም
5 = የመተንፈስ ችግር
6 = የማጅራት በሽታ
7 = የወገብ በሽታ
8 = ደም ማነስ
9 = የአካል መላጥና/መቀጥቀጥ
10 = የአካል መቃጠል
11 = የእጅ/የእግር መቆረጥ
12 = የእጅ/የእግር  መጎረድ
13 = የአካል መወጋት
14 = ውልቃት
15 = የአካል መሰበር
16 = የስር መዞር
17 = የዓይን ጉዳት
18 = የጆሮ ጉዳት
19 = መታፈን
20 = የመስመጥ ችግር
21 = ሌላ በሽታ (ይገለጽ)_____
22 = ሌላ ጉዳት (ይገለጽ)______

1229. **(የልጁ/ጅቷ ስም) የደረሰብህ/ሽ ህመም/ጉዳት ሥራ ለመሥራት ከልክሎሃል/ሻል?**

ይህ ጥያቄ በጥያቄ 1227 ከሥራ ጋር በተያያዘ ምክንያት ጉዳት ወይም ህመም ደርሶብናል ብለው የመለሱትን የሚመለከት ሲሆን የደረሰባቸው ጉዳት ወይም ህመም ለጊዜው ከሥራ አስተጓጉሏቸው እንደሆነ ወይም ለዘለቄታው ከሥራ አግዷቸው እነደሆነ ደግሞ ሥራ ከመሥራት አላገዳቸው እንደሆነ የሚጠየቅበት ነው፡፡ ልጆች ከሥራ ጋር በተያያዘ ከደረሰባቸው ህመሞች/ጉዳቶች መካከል አንዱ እንኳ ለዘለቄታው ከሥራ ያገዳቸው ኮድ 2 ይከበባል፡፡ ነገር ግን የደረሱባቸው ህመሞች/ጉዳቶች ለዘለቄታው ባያግዷቸውም

ቢያንስ በአንዱ ህመም/አደጋ ምክንያት ለጊዜው ከሥራ ካስተጓጎላቸው ኮድ 1 ይከበባል:: እስከዛሬ በሥ ራ ምክንያት የደረሱባቸው ህመሞች/አደጋዎች ምንም ከሥራ ካላገዳቸው ኮድ 3 ይከበባል::

1230. **(የልጁ/ጅቷ ስም) ከደረሱብህ/ሽ ህመሞች/ጉዳቶች መካከል ከፍተኛ ለሆነው ህመም/ጉዳት ምን ዓይነት ህክምና ተደርጎልሃል/ሻል?**

ይህ ጥያቄ በሠሩት ሥራ ምክንያት ከደረሰባቸው ህመም/የአካል ጉዳት መካከል ከፍተኛውን የሚመለከት ሲሆን:: ለዚህ ከፍተኛ ለሆነው ህመም/ጉዳት ምን ዓይነት ህክምና ወስዶ እነደሆነ ለማወቅ ነው:: ለዚህ ጥያቄ መልሱ ከኮድ1-5 ከተዘረዘረው ውስጥ የሚመለስ ይሆናል:: ባህላዊ ወይም ዘመናዊ ህክምና ተደር ጎልኛል የሚሉ ከሆነ በቅደም ተከተላቸው መሠረት ኮድ 1 ወይም 2 ተከቦላቸው ወደ ጥያቄ 1232 ያል ፋሉ:: ዘመናዊ ህክምና ሲባል በሆስፒታል፣ በጤና ጣቢያ/ክሊኒክ መታከምን ይመለከታል:: በዘመናዊ ህ ክምና ተቋም ተኝተው ህክምና ከወሰዱ ኮድ 3 ተከቦላቸው በሚቀጥለው ጥያቄ በህክምና ላይ የቆዩበት ቀን ይሞላል:: ምንም ህክምና አልወሰድኩም ካሉ ኮድ 4 ተከቦላቸው ወደ ጥያቄ 1232 ይታለፋል፤ እን ዲሁም ከዚህ የተለየ መልስ ከሰጡ ኮድ 5 ተከቦላቸው የሰጡት ወደ ጥያቄ 1232 እንዲያልፉ ይደረጋል::

1231.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) በህክምና ተቋም ተኝተህ/ሽ የታከምክባቸው/ሽባቸው ቀናት ም ን ያህል ነበር?**

ይህ ጥያቄ ከላይ ለጥያቄ 1230 ኮድ 3 ለመለሱ የሚጠየቅ ነው:: መልሱን በዘመናዊ ህክምና ተቋም በ መታከም የቆየበትን ቀናት ብዛት በተሰጠው ካርድ ኮለም ላይ ይሞላል:: 97 ቀንና ከዚያ በላይ በህክም ና ተቋም ወይም ሆስፒታል ውስጥ ከተኙ ኮድ 97 ይሞላላቸዋል::

1232 **(የማጣሪያ ጥያቄ)**

ልጆች ባለፈው ሳምንት በምርታማ ሥራ መሠማራት/አለመሠማራታቸውን ከጥያቄ 1208 ይጣራል:: በም ርታማ ሥራ ተሰማሩ የሚባሉት በጥያቄ 1208 ኮድ 1 ወይም ኮድ 2 የተሰጣቸው ሲሆን ለዚህ ጥያቄም ኮድ 1 ይከበብላቸዋል:: በምርታማ ሥራ ያልተሰማሩት በጥያቄ 1208 ከኮድ 3-5 የተሰጣቸው መሆኑን መረጃ ሰብሳቢው አጣርቶ ኮድ 2 ወደ ጥያቄ 1239 ያልፋል::

1233.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) በመስሪያ ቦታህ/ሽ ወይም በግል ስራህ/ሽ አካባቢ ማንኛውን ም የእጅ መሣሪያ/ማሽን ታንቀሳቅሳለህ/ሻለሽ?**

አንዳንድ ልጆች ጉልበታቸው ከሚጠይቀው በላይ የኤሌትሪክ መሣሪያዎች፣ የእጅ መሣሪያ (ለምሳሌ:- መ ጥረቢያ፣ ዶማ፣ ማረሻ፣ አካፋ፣ መዶሻ፣ ቢላዋ መርፌ በመጠቀም ሥራ መሥራትን ... ወዘተ) የሙያ ወይ ም የጉልበት ሥራ መሥራትን ይመለከታል:: እንዲሁም ማሽን በመጠቀም ለምሳሌ የወፍጮ ሞተር ማስነ ሳት፣ ወፍጮ ላይ መስራት የድንጋይ መፍጫ ማሽን ላይ መስራትን ... ወዘተ ይመለከታል:: ለዚህ ጥያቄ መልሱ አዎን ከሆነ ኮድ 1 የለም ከሆነ ካሉ ኮድ 2 ይከበባል::

1234.

**(የልጁ/ጅቷ ስም) በሥራ ላይ እያለህ/ሽ የሚከተሉትን የጉዳት መከላከያዎች ትጠ ቀማለህ /ትጠቀሚያለሽ? የምትጠቀም/የምትጠቀሚ ከሆነ ምን ዓይነት የአደጋ/የጉዳት መከላከያ ትጠቀማለህ/ትጠቀሚያለሽ?**

የዚህ ጥያቄ አላማ በምርታማ ሥራ ላይ የተሰማሩ ልጆች ጉዳት የአደጋ መከላከያዎችን መጠቀም አለመ ጠቀማቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን በዚህም መሠረት ከታች የተዘረዘሩትን መከላከያዎች ተጠቅመው እነደሆነ አንድ በአንድ በመጠየቅ ለተጠቀሙባቸው ኮድ 1 ላልተጠቀሙባቸው ኮድ 2 ይከበባል:: ከA-E ከተዘረዘሩት ውጪ ሌላ ዓይነት የአደጋ መከላከያ ለሚጠቀሙ የመከላከያው ዓይነት ተመዝግቦ ኮድ 1 ይከበባል:: የማይጠቀሙ ከሆነ ደግሞ የለም በሚለው ዓምድ ስር ኮድ 2 ይከበባል:: ምንም ዓይነት የጉዳ ት መከላከያ ለማይጠቀሙ G ላይ ኮድ 1 ይከበባል:: ዝርዝር ሀሳቡ በተመለከተ በቅፅ 2 ጥያቄ 912 ላይ ይመልከቱ::

A= መከላከያ መነጽር E= የእጅ ጓንት

B= መከላከያ ቆብ F= ሌላ (ይገለጽ)_________

C= የጆሮ ውታፍ/ልባስ G= ምንም አይጠቀምም

D= ልዩ የሥራ ጫማ

1235.

**<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) የምትሠራውን/ሪውን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች የአደጋ መከላከያ ያደርጋሉ/ይጠቀማሉ?</u>**

ይህ ጥያቄ ልጁ/ልጅቷ የሚሠራቸውን/የምትሠራቸውን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች የአደጋ መከላከያ መጠቀም አለመጠቀማቸውን በመጠየቅ የአደጋ መከላከያ አጠቃቀምን በተመለከተ ልጆች ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸውን ንፅፅር ለማየት የሚረዳ ሲሆን የሚጠቀሙ ከሆነ ኮድ 1፣ የማይጠቀሙ ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ተሞልቶ ወደ ጥያቄ 1237 ይታለፋል፡፡

1236.

**<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) የምትሰራውን/ሪውን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች ምን ዓይነት የጉዳት የአደጋ መከላከያ ያደርጋሉ/ይጠቀማሉ?</u>**

ልጁ/ልጅቷ የሚሠራውን የምትሠራውን የሥራ ዓይነት የሚሠሩ ሌሎች ሰዎች ከታች የተዘረዘሩትን የጉዳት /የአደጋ መከላከያዎች ይጠቀሙ እንደሆነ አንድ በአንድ በመጠየቅ ለሚጠቀሙባቸው የአደጋ መከላከያ ኮድ 1 ለማይጠቀሙባቸው ኮድ 2 ይከበባል፡፡

A= መከላከያ መነጽር D= ልዩ የሥራ ጫማ

B= መከላከያ ቆብ E= የእጅ ጓንት

C= የጆሮ ውታፍ/ልባስ F= ሌላ (ይገለጽ)________

1237.

**<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ሥራህ/ሽ ለጤና መታወክ ወይም ለአካል ጉዳት፣ ህመም ወይም ሌላ ጠንከር ላለ የጤና ችግር የሚያስከትልብህ/ሽ ይመስልሃል/ሻል?</u>**

የዚህ ጥያቄ ዓላማው አንዳንድ ልጆች የሚሠሩት ሥራ የሚያስከትልባቸውን የጉዳት/ህመም ሁኔታ ስለማይገነዘቡና ለጉዳት/አደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ልጆቹ የለሚሠሩት ሥራ ለጉዳት/አደጋ እንደሚያጋልጣቸውና እንደማያጋልጣቸው ያላቸውን ግንዛቤ የሚለካ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ መልሳቸው አዎን ከሆነ ኮድ 1፣ የለም ከሆነ ኮድ 2 የሚከበብ ሲሆን አላውቅም ካሉ ደግሞ ኮድ 3 ይከበብላቸዋል፡፡

1238. **<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ከአሁኑ ሥራህ/ሽ ጋር የተያያዘ ችግር አጋጥሞህ/ሽ ያውቃል?</u>**

ይህ ጥያቄ ልጁ/ልጅቷ አሁን ከሚሠራው/ከምትሠራው ሥራ ጋር የተያያዘ ማንኛውንም ዓይነት ችግር (የአካል ጉዳት/ህመምን፣ የገንዘብ ማጣት፣ አለመርካት ... ወዘተ) የሚመለከት ይሆናል፡፡ በዚህ ጥያቄ የቤተሰቡ አባላት የሆኑ ልጆች በሥራቸው ምክንያት ጉዳት ደርሶባቸው እንደሆነ ተጠይቆ መልሳቸው አዎን ከሆነ ኮድ 1 የለም ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 ይከበባል፡፡

1239. (<u>የማጣሪያ ጥያቄ</u>)

ይህ ጥያቄ መረጃ ሰብሳቢው መልስ ሰጪውን ሳይጠይቅ ጥያቄ 1201ን፣ 1203ን፣ 1204 እና 1208ን በማየት ልጁ/ልጅቷ ባለፈው ሳምንት የቤት ውስጥ ሥራን ጨምሮ በሥራም ሆነ በትምርት/በስልጠና ተሳትፎ/ፋ እንደ ሆነ የሚያጣራበት ነው፡፡ በጥያቄ 1203 ኮድ 1-4 ወይም በጥያቄ 1204 ከኮድ 1-3 ወይም ለጥያቄ 1208 ከኮድ 1-3 ለተከበበላቸው ለዚህ ጥያቄ ኮድ 1 በመክበብ ወደ ጥያቄ 1241 ይታለፋል፡፡ ነገር ግን በትምህርት/ሥልጠና ላይ ያልተሳተፉ እንዲሁም ምርታማም ሆነ ምርታማ ያልሆነ ሥራ ላልሠሩ ማለትም በጥያቄ 1201 ኮድ 4 ወይም 1203 ኮድ 5 ወይም 1204 ኮድ 4 ወይም 1208 ኮድ 4 ወይም 5 ለተሰጣቸው ለዚህ ጥያቄ ኮድ 2 ተከቦ ወደ ተከታዩ ጥያቄ ይኬዳል፡፡

1240.

**<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) ባለፈው ሳምንት የቤት ውስጥ ሥራን ጨምሮ ምንም ያልሠራህበት/ሽበት ወይም ትምህርት/ስልጠና ያልተከታተልክበት/ሽበት ምክንያት ምንድነው?</u>**

ባለፈው ሳምንት የቤት ውስጥ ሥራን ጨምሮ ምንም ሥራ ካልሰሩ ወይም ትምህርት ላልተማሩና ወይም ስልጠና ላልወሰዱ ማለትም በአንደኛውም እንኳን ካልተሰማሩ ያልተሠማሩበት ምክንያት ምን እንደሆነ ተጠይቆ ከታች ከኮድ 1-7 በተዘረዘሩት መሠረት መልሱ ከሰጠ ትክክለኛው መልስ ይከበባል፡፡ ከተሰጠው ምርጫ ውጭ ከመለሱ ግን «ሌላ» በሚለው ባዶ ቦታ የሰጡት መልስ ተመዝግቦ ኮድ 7 ይከበባል፡፡

1 = በህመም 5 = በጎዳና ላይ መንቀዋለል/መዞር

2 = የአካል መጎዳት
3 = ልጅ ስለሆንክ
4 = ልመና
6 = ሴተኛ አዳሪነት
7 = ሌላ (ይገለጽ)________________

1241. **<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) እንደ አንተ/ቺ ፍላጎት ቢሆን አሁን ምን ማድረግ ትፈልጋለህ/ትፈልጊያለሽ?</u>**

በዚህ ጥያቄ ልጆች እንደሚፈልጉት ቢሆን/እንደምርጫቸው ቢሆን አሁን/በቅርቡ ምን ማድረግ እንደሚ ፈልጉ ይጠየቃል:: ለዚህ ጥያቄ አንድ ዋነኛ መልስ ብቻ ስለሚፈለግ ከኮድ 01-10 ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል ዋነኛውን የፍላጎታቸውን ዓይነት የሚገለፀውን አንዱን ብቻ እንዲመልሱ ተደርጎ ይህንኑ መልስ የያዘው ኮድ ይከበባል::

01 = ሙሉ ቀን መማር
02 = ገቢ በሚያስገኝ የሙሉ ቀን ሥራ መሥራት
03 = በቤተሰብ ድርጅት ውስጥ ሙሉ ቀን ማገልገል
04 = ምርታማ ባልሆኑ የቤት ውስጥ ሥራዎች (እንደ ቤት ጥበቃ የመሣሰሉት ጨምሮ) ሙሉ ቀን ማገልገል
05 = ግማሽ ቀን እየሠራሁ ግማሽ ቀን መማር
06 = በትርፍ ጊዜ ለቤተሰብ ድርጅት ውስጥ ማገልገል
07 = ምርታማ ባልሆኑ የቤት ውስጥ ሥራዎች በትርፍ ሰዓት ብቻ መሥራት
08 = ትምህርት ወይም ሥልጠና አጠናቅቄ ሥራ መጀመር
09 = ከአሁን ካለሁበት ሥራ የተሻለ ሥራ መፈለግ
10 = ሌላ (ይገለፅ) ____________________

1242.

**<u>(የልጁ/ጅቷ ስም) እንደ አንተ/ቺ ፍላጎት ቢሆን ወደፊት ስታድግ/ጊ ምን ማድረግ ትፈልጋለ ህ/ሽ?</u>**

ይህ ጥያቄ ከላይ ከተገለፀው ጋር ተመሳሳይነት ስላለው ማብራሪያውንና አማራጭ መልሶችን ከጥያቄ 1241ን ይመልከቱ::

# እዝል 1 የዋና ዋና የታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1993 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጋራ ሙለታ ደጃዝማች ተብለው የተሾሙበት | 1897 | 96 |
| 2 | ልዑል ራስ መኮንን ያረፉበት | 1898 | 95 |
| 3 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲዳሞ የተሾሙበት | 1900 | 93 |
| 4 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረርጌ የተሾሙበት | 1902 | 91 |
| 5 | አጼ ምኒልክ ያረፉበት (ልጅ ኢያሱ የነገሱበት) | 1906 | 87 |
| 6 | ራስ ሚካኤል በወሎ፣ በትግሬና በጎጃም የነገሱበት | 1907 | 86 |
| 7 | ንግሥት ዘውዲቱ የነገሱበት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ የሆኑበት | 1909 | 84 |
| 8 | የሰገሌ ጦርነት የተካሄደበት | 1909 | 84 |
| 9 | እቴጌ ጣይቱ ያረፉበት | 1910 | 83 |
| 10 | የኅዳር በሽታ የነበረበት | 1911 | 82 |
| 11 | ልጅ ኢያሱ የተያዙበት | 1913 | 80 |
| 12 | ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል የሆነችበት | 1916 | 77 |
| 13 | የባሪያ ነጻነት ደንብ የወጣበት | 1916 | 77 |
| 14 | ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የተቋቋመበት | 1917 | 76 |
| 15 | ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ያረፉበት | 1918 | 74 |
| 16 | አቡነ ማቴዎስ ያረፉበት | 1919 | 74 |
| 17 | ንግሥት ዘውዲቱ ያረፉበት | 1922 | 71 |
| 18 | ራስ ጉግሳ ወሌ በጎንደር የሞቱበት | 1922 | 71 |
| 19 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የነገሱበት | 1923 | 70 |
| 20 | የወልወል ግጭት የተደረገበት | 1927 | 66 |
| 21 | የማይጨው ጦርነት የተካሄደበት ኢጣሊያ ወደ ኢትዮጵያ የገባችበት | 1928 | 65 |
| 22 | የኢትዮጵያ ሰማዕታት ቀን | 1929 | 64 |
| 23 | በጂማ ገነቴ ላይ የአርበኞች ውጊያ የተደረገበት | 1930 | 63 |

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1993 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 24 | እንግሊዝ ኢጣልያን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት የመጣበት | 1933 | 60 |
| 25 | ኢጣሊያን ድል የተመታችበት | 1933 | 60 |
| 26 | ለኢትዮጵያ ሰማዕታት ሀውልት የተሰራበት | 1937 | 56 |
| 27 | አቡነ ባስሊዎስ ሊቀ ጳጳስ የሆኑበት | 1943 | 50 |
| 28 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን የተዋሃደችበት | 1943 | 50 |
| 29 | የሽንቁጤ ረሀብ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የገባበት | 1950 | 43 |
| 30 | እነጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለመፈንቀል ሙከራ ያደረጉበት | 1953 | 40 |
| 31 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተዋሐደችበት | 1955 | 38 |
| 32 | የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመበት | 1955 | 38 |
| 33 | ኮሌራ በሽታ የገባበት | 1963 | 30 |
| 34 | የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳበት | 1966 | 27 |
| 35 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን የወረዱበት | 1967 | 26 |
| 36 | የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ | | |
| | በዓል የተከበረበት | 1967 | 26 |
| 37 | የገጠርን መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 26 |
| 38 | የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 26 |
| 39 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያረፉበት | 1967 | 26 |
| 40 | ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. የተመሠረተበት | 1972 | 21 |
| 41 | የመጀመሪያው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደበት | 1976 | 17 |
| 42 | የኢ.ሠ.ፓ. ምሥረታና የ10ኛው አብዮት የተከበረበት | 1977 | 16 |
| 43 | የግንቦት 8 መፈንቅለ መንግሥት | 1981 | 12 |
| 44 | ኢሕአዴግ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት | 1983 | 10 |
| 45 | ሁለተኛው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደበት | 1987 | 6 |